# ሐዋርያው ጳውሎስ
# ለቆሮንቶስ ሰዎች የጻፈው የመጀመሪያው መልእክት

## መግቢያ

ጸሐፊው ሐዋርያው ጳውሎስ ሲሆን፥የተጻፈበትም ዘመን በ55 ዓ.ም. ገደማ እንደሆነ ይገመታል። የቆሮንቶስ ምዕመናን ልዩ ልዩ ኃጢአቶችን በመሥራት ባላመኑት አሕዛብ መካከል የክርስቶስ ስም እንዲዋረድ አድርገዋል። መለያየት፥ጸብ፥ክርክር፥ዝሙት፥የሐሰት ትምህርትና ሌሎችም የተመሰቃቀሉ ሁኔታዎች በመካከላቸው ሰፍነው ነበር። የመልእክቱ መሠረተ ሐሳብ እነዚህ አስጸያፊ ድርጊቶች ከምዕመናን መካከል የሚወገዱበትን መንገድ መሻት ነው። እውነተኛ ፍቅር ማለት ምን ማለት እንደሆነ በዚሁ መጽሐፍ በ13 ኛው ምዕራፍ ላይ ሰፍሮ ይገኛል።

---

## ምዕራፍ 1

1 በእግዚአብሔር ፈቃድ የኢየሱስ ክርስ
ቶስ ሐዋርያ እንዲሆን ከተመረጠው ከጳው
ሎስና ከወንድም ሶስቴንስ የተላከ።
2 ወገኖቼ እንድትሆኑ እግዚአብሔር በክ
ርስቶስ የመረጣችሁ የቆሮንቶስ ቤተ ክርስ
ቲያን ምዕመናን፥ እንዲሁም በየሥፍራው
የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስን ስም ለምት
ጠሩ ክርስቲያኖች ሁሉ።
3 የአባታችን የእግዚአብሔር፥የጌታችንም
የኢየሱስ ክርስቶስ የተትረፈረፈ በረከቱ ይደ
ርባችሁ። ፍጹም የሆነ የሕሊናና የአእምሮ
ዕረፍትም ያድላችሁ።
4 እግዚአብሔር በኢየሱስ ክርስቶስ ጸጋ
ውን ስለሰጣችሁ እርሱን ከማመስገን ምን
ጊዜም ወደ ኋላ አልልም። 5 ጌታ ኢየሱስ
ክርስቶስ በሁሉ ነገር አበልጽጓችኋል። በእ
ውቀትና በንግግርም በስላችኋል። 6 ክርስቶስ
ያደርግላችኋል ብዬ የነገርኳችሁ ሁሉ ተፈ
ጽሟል። 7 የጌታችንን የኢየሱስ ክርስቶስን
መገለጥ ስትጠባበቁ ሳይሰጣችሁ የሚቀር
አንድም መንፈሳዊ ስጦታ የለም። 8 ጌታ
ኢየሱስ ዳግም በሚመጣበት ጊዜ ምንም
ዓይነት ነውር፥ምንም ዓይነት ነቀፋ ሳይገኝ
ባችሁ በፊቱ መቆም ትችሉ ዘንድ እስከ
መጨረሻ እንድትጸኑ ይረዳችኋል። 9 ከልጁ
ከጌታችን ከኢየሱስ ክርስቶስ ጋር አንድነት
እንዲኖራችሁ የጠራችሁ እግዚአብሔር
ተስፋ የሰጣችሁን አንዱንም ነገር አያስቀር
ባችሁም።
10 ውድ ወንድሞቼ ሆይ፥በመካከላችሁ
ያለውን መለያየት እንድታስወግዱት በጌታ
በኢየሱስ ስም እለምናችኋለሁ። ስለዚህ

ምንም ዓይነት መለያየት በመካከላችሁ እን
ዳይኖር እንደ አንድ ቃል ተናጋሪ፥እንደ
አንድ ልብ መካሪ ሆናችሁ ተስማምታችሁ
ኑሩ። 11 ወንድሞቼ ሆይ ፥ በመካከላችሁ
ጠብና ክርክር እንዳለ፥የቀሎዔ ቤተ ሰብ
ከሆኑ አንዳንድ ሰዎች ተረድቼአለሁ።
12 እርስ በርሳችሁም፥አንዱ «የጳውሎስ ተከ
ታይ ነኝ» ሲል ሌላው ፥ «የአጵሎስ ተከ
ታይ ነኝ» ይላል። ሦስተኛው ደግሞ «የጴ
ጥሮስ ተከታይ ነኝ» ይላል። ሌላው ደግሞ
የክርስቶስ ተከታይ መሆኑን ይናገራል። ይህ
በመሆኑም በመካከላችሁ መለያየት ተፈጥ
ሯል። 13 ለመሆኑ ክርስቶስ ተከፋፍሏል ያላ
ችሁ ማነው? በመስቀል ላይ የተሰቀልኩላ
ችሁስ እኔ ጳውሎስ ነኝ? የተጠመቃችሁ
ትስ በእኔ ስም ነው? 14 ከቀርስጶስና ከጋይ
ዮስ በቀር ከመካከላችሁ አንድም ሰው ስላላ
ጠመቅሁ እግዚአብሔርን አመሰግነዋለሁ።
15 ምክንያቱም ማንም ሰው፥ «ጳውሎስ ሰዎ
ችን የራሱ ተከታይ ለማድረግ አጥምቋቸ
ዋል» ብሎ ስሜን ሊያነሣው አይችልም።
16 አዎን፥የእስጢፋኖስን ቤተ ሰብ አጥምቄ
አለሁ። ከእነዚህ ሌላ ያጠመቅሁት ሰው
መኖሩን አላስታውስም። 17 ቀድሞውኑም
ክርስቶስ የላከኝ የምሥራቹን ቃል እንዳስተ
ምር እንጂ እንዳጠምቅ አይደለም። የምሥ
ራቹንም ቃል የምሰብከው፥የክርስቶስን የመ
ስቀሉን ምሥጢር ለመረዳት በሚያዳግት
በዚህ ዓለም የጥበብና የፍልስፍና ቋንቋ
አይደለም። እንዲህ ባለው ባዶ ንግግር ማሳ
መር ለመራቀቅ ብሞክር፥ታላቅ ኃይል ያለ
ውን የክርስቶስን መስቀል ከንቱ አደረግሁት
ማለት ነው።

18 የጥፋትን ጐዳና የተከተሉ፥ክርስቶስ
ሰዎችን ለማዳን በመስቀል ላይ የመሞቱን
የምሥራች ቃል ሲሰሙ፥እንደ ሞኝነት
ይቆጥሩታል። እኛ የዳነው ግን የእግዚአብ
ሔር ኃይል መሆኑን እናውቃለን። 19 በቅዱ
ሳት መጻሕፍት፥ «የጥበበኞችን ጥበብ አጠ
ፋለሁ፤የሊቃውንትንም ማስተዋል እንዳልነ
በር አደርጋለሁ» ተብሎ ተጽፎአልና።

20 ታዲያ ነገሩ እንዲህ ከሆነ ጥበበኞ
ችም ሆኑ ምሁራን፥የት አሉ? የዚህ ዓለም
ፈላስፎችስ የት ደረሱ? እግዚአብሔር እነዚ
ህን እንደ ሞኝ አድርጎ ይመለከታቸዋል፥
ጥበባቸውንም የማይረባና የማይጠቅም አድ
ርጎ ይቆጥረዋል። 21 ዓለም በራሷ እውቀት፥
በራሷ ጥበብ እግዚአብሔርን ለማወቅ እንዳ
ትችል በረቀቀ ጥበቡ ሰውሮባታል። እንደ
ሞኝ ፈሊጥ በተቆጠረው በዚህ እኛ በምንሰ
ብከው የወንጌል ቃል ግን፥ሰዎች ሁሉ እን
ዲድኑ ፈቃዱ ሆኗል። 22 መቼም ይህ ነገር
ለአይሁድ የሞኝ ፈሊጥ ይመስላቸዋል።
ምክንያቱም የተሰበከው እውነት መሆኑን
የሚያረጋግጥ አንድ ዓይነት ተአምር ይፈል
ጋሉና። ግሪኮችም የፍልስፍና ትምህርታቸ
ውን በመከተል ዋጋ እንደሌለው ነገር ይቆ
ጥሩታል። 23 እኛ ግን የተሰቀለውን ኢየሱስ
ክርስቶስን እንሰብካለን። ይህ መልእክት
አይሁድ የሚሰናከሉበት ሲሆን፥ግሪኮችም
ደግሞ እንደ ሞኝነት ይቆጥሩታል። 24 ነገር
ግን፥ለአይሁዶችም ሆነ ለግሪኮች እግዚአብ
ሔር ለጠራቸው ሁሉ፥ክርስቶስ ደኅንነትን
የሚሰጥ የእግዚአብሔር ኃይልና ጥበብ
ነው። 25 ምክንያቱም ይህ እንደ ሞኝነት
የተቆጠረው የእግዚአብሔር ጥበብና ዓላማ
ከሰዎች ጥበብና ዓላማ የበለጠ ነው። ደካማ
ነው ተብሎ የሚታሰበው የእግዚአብሔርም
ነገር፥ከሰዎች ጥንካሬ ይልቅ ይበረታል።

26 ወንድሞቼ ሆይ፥እግዚአብሔር በጠራ
ችሁ ጊዜ ምን ዓይነት ሰዎች እንደነበራ
ችሁ አስታውሱ። እንደ ሰው አስተሳሰብ
ከእናንተ መካከል ብዙዎቻችሁ ጥበበኞች፥
ወይም ኃያላን፥ወይም የታላላቅ ሰዎች
ልጆች ወይም ሀብታሞች አልነበራችሁም።
27 እግዚአብሔር፥ «አዋቂዎች ነን» ብለው
የሚመኩትን የዚህን ዓለም ጥበበኞች ለማሳ
ፈር፥በዚች ምድር ላይ እንደ ሞኝ የሚቆጠ
ረውን ነገር መረጠ። «ብርቱ ነን» የሚሉት
ንም ሰዎች ለማሳፈር በዓለም ደካሞች መስ
ለው የሚታዩትን መረጠ። 28 ዓለም እንደ
ትልቅ ነገር አድርጎ የሚመካበትን ነገር
እንዳልነበር ለማድረግ በሰዎች ዘንድ የተና
ቀውን፥የማይረባና፥የማይጠቅም መስሎ የታ
የውን መንገድ መረጠ። 29 ይህን ያደረገው
ማንም ሰው በራሱ እንዳይመካ ነው።

30 እኛን ግን፥እግዚአብሔር ከክርስቶስ
ኢየሱስ ጋር አንድነት እንዲኖረን አደረገ።
ከዚህ የተነሣም ክርስቶስ ጥበባችን፥ጽድቃ
ችን፥ቅድስናችንና ቤዛችንም ነው። 31 ስለ
ዚህ በቅዱሳት መጻሕፍት እንደ ተጻፈ፥
«የሚመካ ቢኖር በእግዚአብሔር ብቻ
ይመካ።»

## ምዕራፍ 2

1 ወንድሞቼ ሆይ፥የወንጌልን ቃል ለመ
ስበክ መጀመሪያ ወደ እናንተ በመጣሁ
ጊዜ፥ሆን ብዬ የንግግር ችሎታዬን ለማሳየት
በመራቀቅና በመፈላሰፍ አላስተማርኳች
ሁም። 2 ምክንያቱም በመስቀል ላይ ከተሰቀ

ለው ከኢየሱስ ክርስቶስ ሌላ ስለ ምንም
ነገር እንዳልናገር ቁርጥ ውሳኔ አድርጌ ስለ
ነበር ነው። 3 ስለዚህ ወደ እናንተ የመጣ
ሁት ደካማ ሆኜ በፍርሃትና በመንቀጥቀጥ
ነበር። 4 ትምህርቴም በመንፈስ ቅዱስ
ኃይል የተደገፈ እንጂ፥ ንግግር በማሳመርና
በመራቀቅ ላይ የተመሠረተ አልነበረም።
5 ይህን ማድረጌም፥ እምነታችሁ በሰው
ጥበብ ላይ የተመሠረተ ሳይሆን በእግዚአብ
ሔር ኃይል ላይ የተደገፈ እንዲሆን ስለፈለ
ግሁ ነው።

6 በመንፈሳዊ ሕይወታቸው ከበሰሉ ክርስ
ቲያኖች ጋር በምሆንበት ጊዜ ግን በጥበብ
እናገራለሁ። በጥበብ እናገራለሁ ስልም፥
ከንቱ የሆነውን የዚህን ዓለም ጥበብ ማለቴ
አይደለም። 7 እኔ የምናገረው ጥበብ፥እግዚአ
ብሔር ከዘመናት በፊት ለእኛ ጥቅም እንዲ
ሆን ያዘጋጀውንና ከሰዎች ተሰውሮ የነበረ
ውን የራሱን ጥበብ ነው። 8 ይህንንም የእግ
ዚአብሔር ጥበብ የዚህ ዓለም ገዢዎች አላ
ወቁትም። አውቀውት ቢሆንማ ኖሮ የክብ
ርን ጌታ ባልሰቀሉት ነበር።

9 ቅዱሳት መጻሕፍት፥ «ዓይን ያላየ
ውን፥ጆሮ ያልሰማውን፥ልቦናም ያላሰበውን
ድንቅ ነገር እግዚአብሔር ለሚወዱት አዘጋ
ጅቶላቸዋል» ብለዋል። 10 እኛ ግን እግዚአ
ብሔር መንፈሱን ልኮ ስለገለጠልን ስለ እነ
ዚህ ነገሮች እናውቃለን። የእግዚአብሔር
መንፈስ ጥልቅ የሆነውን የእግዚአብሔርን
ምሥጢር ሁሉ እየመረመረ ለእኛ ይገልጥ
ልናል። 11 አንድ ሰው ምን እንደሚያስብ
ወይም ምን እንደሚፈልግ ከራሱ በስተቀር
ሌላ ማንም ሊያውቅለት አይችልም። እንደ
ዚሁም ከእግዚአብሔር መንፈስ በቀር የእግ
ዚአብሔርን አሳብ ሊያውቅ የሚችል
ማንም የለም። 12 እኛ የተቀበልነው የዚህ
ችን ዓለም መንፈስ ሳይሆን የእግዚአብሔ
ርን መንፈስ ነው። ስለዚህ እግዚአብሔር
በነፃ የሰጠንን አስደናቂ ስጦታዎች ሁሉ
እንረዳለን።

13 እኛ መንፈሳዊ ነገሮችን የምናስተም
ረው፥ መንፈስ ቅዱስ የሚነግረንን እውነት
ተቀብለን በእግዚአብሔር ጥበብ እንጂ፥
ሰዎች በነገሩንና ባስተማሩን ጥበብ አይደ
ለም። 14 የእግዚአብሔር መንፈስ የሌለበት
ሰው ከመንፈስ ቅዱስ የሚገኙትን መንፈሳዊ
ስጦታዎች ሊቀበል አይችልም። እንዲህ
ያለው መንፈሳዊ ነገር ሊገባው ስለማይች
ልም እነዚህን ስጦታዎች የሚመለከታቸው
ጥቅም እንደሌላቸው ነገሮች አድርጎ ነው።
ምክንያቱም የመንፈሳዊ ስጦታዎች ጥቅም
ሊታወቅ የሚችለው በመንፈስ ቅዱስ አማካ
ይነት ብቻ ነው። 15 መንፈሳዊ ሰው ግን
ማናቸውንም ነገር መመርመርና ማወቅ
ይችላል። እርሱ ራሱ ግን በማንም አይመረ
መርም።

16 በቅዱሳት መጻሕፍት፥ «የእግዚአብሔ
ርን ልብ ማን ሊያውቅ ይችላል? ሊመክረ
ውስ የሚችል ማን ነው?» ተብሎ ተጽፎ
አል። እኛ ክርስቲያኖች ግን የክርስቶስ
አሳብ በልቦናችን መሣሉን እናውቃለን።

## ምዕራፍ 3

1 ወንድሞቼ ሆይ፥ መንፈሳውያን ለሆኑ
ሰዎች እንደምናገር አድርጌ ልናገራችሁ
አልቻልም። የምነግራችሁ ሥጋውያን በመ
ሆናችሁ፥ ገና ለሚጠቡ ሕፃናት እንደምና
ገር ነው። 2 በመንፈሳዊ ሕይወት ገና ስላላ
ደጋችሁና ጠንካራ ምግብ መብላት ስለማት
ችሉም እንደሕፃን ወተት ጋትኳችሁ። 3 ገና
አሁንም በመካከላችሁ ቅናትና ክርክር እን
ዳለ ይሰማኛል። ይህ ሁኔታ አሁንም ገና
ሕፃን መሆናችሁንና የምትሠሩት በእግዚአ
ብሔር ሳይሆን፥በገዛ ፍላጐታችሁ እየተመ
ራችሁ መሆኑን ያሳያል። 4 አንዱ፥ «እኔ የጳ
ውሎስ ነኝ» ሌላው ደግሞ፥ «እኔ የአጵሎስ
ነኝ» እያላችሁ እንዲህ ያለውን መለያየት
መፍጠራችሁ ምን ይባላል? ይህም ገና
በሥጋዊ ባሕርያችሁ እንደምትመሩ ያሳ
ያል።

5 እረ ለመሆኑ እኔ ማን ነኝ? አጵሎስስ
ማን ነው? እኛ የእግዚአብሔር አገልጋዮች
እንጂ ሌላ ምንም አይደለንም። እግዚአብ
ሔር ለያንዳንዳችን በሰጠን ልዩ ልዩ
ችሎታ ስላገለገልናችሁ እናንተም በክርስ
ቶስ ለማመን በቅታችኋል። ታዲያ በኛ ምክ
ንያት ምን ያለያያችኋል? 6 እኔ ተከልኩ፤
አጵሎስ ደግሞ ውኃ አጠጣ፤ነገር ግን ያን
ተክል ያሳደገው እግዚአብሔር ነው። 7 ያን
ተክል የተከለውም ሆነ ውኃ ያጠጣው
ይህን ያህል ግምት የሚሰጠው አይደለም።
ዋናው ያሳደገው እግዚአብሔር ነው።
8 እከሌ ተከለ፤እከሌ ውኃ አጠጣ፤በሁለቱ
መካከል ልዩነት የለም። እግዚአብሔር ለሁ
ለቱም እንደ ድካማቸው መጠን ዋጋቸውን
ይከፍላቸዋል። 9 እኛ ከእግዚአብሔር ጋር
አብረን እንሠራለን። እናንተም የእኛ ሳት
ሆኑ የእግዚአብሔር እርሻ ናችሁ። እንዲ
ሁም የእኛ ሳትሆኑ የእግዚአብሔር ሕንፃ
ናችሁ።

10 እግዚአብሔር በቸርነቱ ባደለኝ መን
ፈሳዊ ስጦታ የተዋጣለት ጥሩ ግንበኛ ሆኛ
ለሁ። ስለዚህም እኔ መሠረትን ጣልኩ።
አጵሎስ ግንቡን አወጣ። ሌላ ሰው ደግሞ
እኔ በጣልኩት መሠረት ላይ ይገነባል።
ነገር ግን በዚህ መሠረት ላይ ግንቡን የሚገ
ነባው ሰው ሁሉ በጥንቃቄና በማስተዋል
መገንባት አለበት። 11 አስቀድሞ ከተመሠረ
ተው ከኢየሱስ ክርስቶስ በስተቀር ማንም
ሌላ መሠረት ሊጥል አይችልም። 12 ሕንፃ
ውን በመሠረቱ ላይ ለማቆም ለሥራው የሚ
ውሉ ልዩ ልዩ ዓይነት ዕቃዎች ይቀርባሉ።
አንዳንድ ሰዎች ሕንፃውን በወርቅ፥በብር፥
በከበረ ድንጋይ ሲሠሩ፥ሌሎች ደግሞ በእን
ጨት ፥ በሣር ወይም በገለባ ይገነባሉ።
13 እያንዳንዱ በምን እንደ ሠራ የሚገለጥ
በት የፍርድ ቀን ይመጣል። የእያንዳንዱም
ሰው የሥራ ጥራት በእሳት ተፈትኖ ይታ
ያል። 14 ማንም ሰው በመሠረቱ ላይ የሠ
ራው ሥራ በእሳት ተፈትኖ ካለፈለት ዋጋ
ውን ከእግዚአብሔር ይቀበላል። 15 ነገር
ግን ሥራው ሲፈተን በእሳት ከተቃጠለበት
ምንም ዋጋ አያገኝበትም። እርሱ ራሱ ይድ
ናል። የሚድነው ግን እንደ ግድግዳ ከቆመ
የእሳት ወላፈን ውስጥ እንደሚወጣ ሰው
ሆኖ ነው።

16 እናንተ ሁላችሁ የእግዚአብሔር ቤተ
መቅደስ መሆናችሁንና የእግዚአብሔርም
መንፈስ በውስጣችሁ አድሮ እንደሚኖር
አታውቁምን? 17 ማንም የእግዚአብሔርን
ቤተ መቅደስ ቢያረክስ ወይም ቢያፈርስ፥
ያን ሰው እግዚአብሔር ያፈርሰዋል። የእግ
ዚአብሔር ቤተ መቅደስ ክቡርና ንጹሕ
ነው። የእግዚአብሔር መቅደስ የተባላችሁ
ትም እናንተው ናችሁ።

18 ከእንግዲህ ራሳችሁን አታታልሉት።
ከእናንተ ማንም ሰው በዚህ ዓለም በሚገ
ኘው የእውቀት ደረጃ ሲመዘን ራሱን የላቀ
አድርጎ ከገመተ ፥ እርሱ ራሱን አታሏል።
ስለዚህ የእግዚአብሔርን እውነተኛ ጥበብ
እንዲታደል ራሱን እንደ አላዋቂ ይቁጠ
ረው። 19 ምክንያቱም የዚህ ዓለም ጥበብ
በእግዚአብሔር ፊት እንደ ሞኝነት ስለሚቆ
ጠር ነው። በመጽሐፈ ኢዮብ፥ «እግዚአብ
ሔር ጥበበኞችን በተንኰላቸው ያጠምዳቸ
ዋል» ተብሎ ተጽፎአል። 20 በመዝሙ
ርም ፥ «እግዚአብሔር የጥበበኞች አሳብ
ከንቱ እንደሆነ ያውቃል» ተብሎ ተጽፎ
አል። 21 ስለዚህ፥ «ጥበበኞች ነን» የሚሉ
ትን የዚች ዓለም ሰዎች በመከተል ማንም
ሰው አይመካ። ምክንያቱም እግዚአብሔር
የሚያስፈልጋችሁን ማናቸውንም ነገር ሁሉ
ሰጥቶአችኋልና። 22 እንዲሁም ጳውሎስ ፥
አጵሎስና ጴጥሮስም ቢሆኑ ሁሉም የናን
ተው ናቸው። ደግሞም ዓለም ፥ ሕይወትና
ሞት ፥ አሁን ያለውና ወደፊት የሚመጣው
ሁሉ እንዲገዛላችሁ አድርጓል። 23 እናንተ
የክርስቶስ ናችሁ ፤ ክርስቶስም የእግዚአብ
ሔር ነው።

## ምዕራፍ 4

1 እንግዲህ ሰው ሁሉ እኔና አጵሎስን
እንደ ክርስቶስ አገልጋዮችና የእግዚአብሔ
ርን ምሥጢር በመግለጽ እንደምናስተምር
መምህራን እንጂ ፥ በሌላ ዓይን እንዲመለከ
ተን አያስፈልግም። 2 ከአንድ አገልጋይም
የሚጠበቀው ፥ ጌታው የሚነግረውን ሁሉ
በታማኝነት መፈጸም ነው። 3 ስለ አገልግ
ሎቴ እናንተም ሆናችሁ ሌላ ሰው የመሰለ
ውን ዓይነት ፍርድ ቢሰጥ ግድ የለኝም።
እኔ ራሴም ብሆን በዚህ ጉዳይ ላይ ስለ
ራሴ ፥ 'እንደዚህ ነኝ' ብዬ ፍርድ ለመስ
ጠት የምችል አይደለሁም። 4 እኔ እስከማው
ቀው ድረስ ግን ከሕሊና ወቀሳ ንጹሕ ነኝ።
ሆኖም ከሕሊና ወቀሳ 'ንጹሕ ነኝ' ማለቴ
ይህንኑ ያረጋግጥልኛል ማለት አይደለም።
የእኔን በታማኝነት ማገልገል ወይም አለማገ
ልገል የሚፈርደው ራሱ ጌታ ብቻ ነው።

5 ስለዚህ፥ «እከሌ ጥሩ አገልጋይ ነው ፤
ወይም አይደለም» ብላችሁ ጌታ ከመገለጡ
በፊት ያለ ጊዜው በሰው ላይ ለመፍረድ
አትቸኩሉ። ማናቸውንም በጨለማ የተሰወ
ረውን ቁልጭ አድርጎ የሚያሳይ፥የልብንም
አሳብ የሚገልጥ ጌታ በሚመጣበት ጊዜ
እያንዳንዳችን ምስጋናችንን ከእግዚአብሔር
እንቀበላለን።

6 ወንድሞቼ ሆይ ፥ አጵሎስንና እኔን
እንደ ምሳሌ አድርጌ እዚህ ላይ ያቀረብ
ኩት እከሌ ከእከሌ ይበልጣል የሚል አስተ
ሳሰብ እንዳይኖራችሁ እንድትጠነቀቁበት
ለማለት ነው። በወንጌል መምህራን መካ
ከል አንዱን ከሌላው አስበልጣችሁ መመል
ከት የለባችሁም። 7 ይህን ያህል በራሳችሁ
የሚያስመካችሁ ምንድን ነው? ይህን ያህል
የሚያስመካስ ከእግዚአብሔር ያላገኛች
ሁት፥እናንተ በገዛ ራሳችሁ ያከናወናችሁት
ምን ነገር አለ? ታዲያ የእኛ ነው የምት
ሉት ሁሉ የተገኘው ከእግዚአብሔር ከሆነ፥
ከሌሎቹ እንበልጣለን ብላችሁ መመካታ
ችሁ ለምንድን ነው?

8 ሲያዩአችሁ የሚያስፈልገውን መንፈ
ሳዊ ምግብ ሁሉ አግኝታችሁ እንደበቃው
ሰው አድርጋችሁ የምታስቡ ትመስላላ
ችሁ። ማለትም ማናቸውም ነገር ተሟልቶ
ላችኋል፤በመንፈሳዊ ረገድም በቅተችኋል፤
እኛን ትታችሁ በየዙፋናችሁ ላይ የተቀመ
ጣችሁ ነገሥታት ሆናችኋል። እኛም ከእና
ንተ ጋር አብረን ዙፋን ላይ እንድንቀመጥ
መንገሣችሁ እውነት ቢሆን እንዴት ደስ
ባለኝ ነበር! 9 ለዓለም፥ለመላእክትና ለሰዎ
ችም ሁሉ መሳለቂያ በመሆናችን እግዚአብ
ሔር እኛን ሐዋርያቱን ሞት እንደተፈረደባ
ቸው ሰዎች ዝቅ ያለ ቦታ የሰጠን ይመስለ
ኛል።

10 እኛ ስለ ክርስቶስ ብለን ሞኞች ሆነ
ናል፤እንዳላዋቂም ተቆጥረናል። እናንተ ግን
ጥበበኞች ሆናችኋል። እንዲሁም እኛ ደካ
ሞች ስንሆን እናንተ ኃይለኞች፥እኛ የተዋ
ረድን ስንሆን፥እናንተ የተከበራችሁ ሆናች
ኋል። 11 እስከዚች እስከ አሁኗ ሰዓት ድረስ
እየተራብን፥እየተራቆትን፥እየተደበደብንና
መጠለያ በማጣት እየተንከራተትን ኑሮን
እንገፋዋለን። 12 ኑሮን ለማሸነፍም እስኪደ
ክመን ድረስ በገዛ እጃችን እንሠራለን። የሚ
ረግሙንን እንመርቃለን፤ሲያሳድዱን እንታገ
ሣለን። 13 ክፉ ሲናገሩን ደግ ደጉን እንመል
ስላቸዋለን፤ እስከዚች ሰዓት ድረስ ለዓለም
የምንታየው እንደ እግር እጣቢና እንደ
ቆሻሻ ጥራጊ መስለን ነው።

14 ይህንን የምጽፍላችሁም እንድታፍሩ
በት ሳይሆን፥የምወዳችሁ ልጆቼ ስለሆና
ችሁ እንዲህ ያለ ነገር መኖሩን እንድታው
ቁት ለመምከር ነው። 15 ምንም እንኳ ዛሬ
በብዙ የሚቆጠሩ ስለ ክርስቶስ የሚያስተም
ሩአችሁ ሌሎች ቢኖሩም፥መንፈሳዊ አባታ
ችሁ እኔ ብቻ መሆኔን መዘንጋት የለባች
ሁም። ከማንም በፊት የወንጌሉን ቃል አስ
ተምሬ ወደ ክርስቶስ እንድትቀርቡ ያደረግ
ኋችሁ እኔ ነኝና። 16 ስለዚህ የእኔን ምሳሌ
ነት ተከትላችሁ እኔ ያደረግሁትን እንድታ
ደርጉ እለምናችኋለሁ።

17 የተወደደውንና የታመነውን መንፈ
ሳዊ ልጄን ጢሞቴዎስን ወደ እናንተ የላክ
ሁበት ዋና ምክንያት፥ ይህንኑ እንዴት
በሥራ እንደምታውሉት እንዲረዳችሁ በማ
ለት ነው። እርሱም በየደረስኩበት ሥፍራ
በሚገኙ አብያተ ክርስቲያን ከማስተምረው
ትምህርት ጋር አብሮ የሚሄደውን በክርስ
ቶስ ያለኝን አካሄዴን ይነግራችኋል።

18 ከመካከላችሁ ጥቂት ሰዎች ወደ እና
ንተ የማልመጣ መስሎአቸው መኩራራታቸ
ውን አውቃለሁ። 19 ግን የእግዚአብሔር
ፈቃዱ ቢሆን በቅርቡ ወደ እናንተ ለመም
ጣት ወስኛለሁ። እንግዲህ እነዚህ ትዕቢተ
ኞች አገር የሚፈቱበትን ንግግራቸውንና
የሚመኩበትን ኃይላቸውን ምንነት የምደር
ስበት በዚያን ጊዜ ነው። 20 የእግዚአብሔር
መንግሥት በወሬ ሳይሆን በሥራ የሚገለጽ
ኃይል ነው። 21 የትኛውን ትመርጣላችሁ?
ዱላና በትር ይዤ በቁጣ መምጣቴን?
ወይስ በየዋህነትና በፍቅር መምጣቴን?

## ምዕራፍ 5

1 በመካከላችሁ አሳፋሪ የሆነ የዝሙት
ተግባር እንደሚፈጸም ይወራል። እንደዚህ
ዓይነቱ አሳፋሪ የዝሙት ሥራ፥በክርስቲያ
ኖች ይቅርና ክርስቲያን ባልሆኑት ሰዎች
መካከል እንኳ ተደርጎ የማያውቅ ነው።
የአባቱን ሚስት፥ ይኸውም የእንጀራ እና
ቱን፥ አግብቶ በመካከላችሁ የሚኖር ሰው
እንዳለ ሰምቻለሁ። 2 ታዲያ እንዲህ ያለ አሳ
ፋሪ ነገር በመካከላችሁ እያለ፥ «መንፈሳው
ያን ነን» ብላችሁ መታበያችሁ በጣም ያስ
ደንቃል። ሲሆን ሲሆን እንዲህ ባለው አሳ
ፋሪ ድርጊት ማዘን ይገባችሁ ነበር። እንዲህ
ያለውንም ሰው አውግዛችሁ ከመካከላችሁ
ልትለዩት በተገባ ነበር።

3 ምንም እንኳ እኔ የምገኘው በአካል
ከእናንተ ርቄ ቢሆንም፥በመንፈስ ከእናንተ
ያልተለየሁ ስለሆነ ከእናንተው ጋር ሆኜ
በዚህ ሰው ላይ በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ
ስም ፈርጄበታለሁ። 4 ስለዚህ ጉዳይ የሚከ
ተለውን ላሳስባችሁ። መጀመሪያ፥የቤተ ክር
ስቲያን አባሎችን ሁሉ ሰብስቡ። በምትሰበ
ሰቡበትም ጊዜ የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ
ኃይል ከእናንተ ጋር ይሆናል። እኔም ከእና
ንተ ጋር በመንፈስ ሆኜ፥ 5 ይህን በደል በፈ
ጸመው ሰው ላይ በሥጋው እንዲቀጣ ከቤተ
ክርስቲያን አባልነት በማስወገድ ለሰይጣን
አሳልፋችሁ እንድትሰጡት ፈርጄበታለሁ።
ይህንንም የምለው ጌታ በሚመለስበት ጊዜ
ነፍሱ እንድትድን ነው።

6 እንዲህ ያለው ነገር ሲደርስ ዝም ብላ
ችሁ እያያችሁ በራሳችሁ ንጽሕና መመጻደ
ቃችሁ በእውነቱ አሳፋሪ ነው። ጥቂት
እርሾ ሊጡን ሁሉ እንደሚያቦካ፥እንደዚ
ሁም አንድ ሰው ኃጢአት ሲሠራ ዝም ከተ
ባለ፥ የቀሩትም ሁሉ ኃጢአት እንዲሠሩ
የሚገፋፉቸውና የሚያደፋፍራቸው መሆ
ኑን አታውቁም? 7 እርሾ የሌለበትን ሊጥ

እንድትመስሉና ንጹሕ እንድትሆኑ ኃጢአ
ትን ከእናንተ አስወግዱ። ምክንያቱም የእግ
ዚአብሔር በግ ክርስቶስ ስለ እኛ መሥዋ
ዕት ሆኖልናልና። 8 ስለዚህ ከፋሲካችን ክር
ስቶስ ማዕድ እየተመገብን በክርስትና ሕይ
ወታችን እንበርታ። ያንን በቆየ እርሾ የተ
መሰለውን የቀድሞ ክፋታችንና አመፃችንን
ትተን፥ ቅንነትና እውነት የሞላበትን ንጹ
ሕና ክቡር የሆነውን የፋሲካ ቂጣ እንመ
ገብ።
9 ከዚህ በፊት ከአመንዝራዎች ጋር እንዳ
ትተባበሩ ጽፌላችኋለሁ። 10 ይህን ማለ
ቴም፥ ክርስቲያኖች ካልሆኑ አመንዝራዎ
ችና ስግብግብ ሰዎች፥ ከሌቦችና ከጣዖት
አምላኪዎች ጋር፥ምንም ዓይነት ግንኙነት
አይኑራችሁ ለማለት አይደለም። ከእነርሱ
ራቁ ማለትማ የግድ ከዓለም መውጣት ያስ
ፈልጋችኋል ማለት ነው። 11 እንደዚያ
ማለቴ ግን፥ በስመ ክርስቲያን በድፍረት
ከሚያመነዝርና ከሚስገበገብ፥ጣዖት ከሚያ
መልክና ከሚሳደብ፥ ከሰካራምና ከቀማኛ
ጋር አትተባበሩ ለማለት ነው። ከእንዲህ
ዓይነቱ ሰው ጋር በአንድ ማዕድ እንኳ አብ
ራችሁ አትቀመጡ።
12 በማያምኑት ላይ ፍርድ ለመስጠት
ጉዳዩ መች እኛን ይመለከተናል? አይመለከ
ተንም። የቤተ ክርስቲያን አባሎች ሆነው
እንዲህ ያለውን ኃጢአት ልማድ አድርገው
በሚሠሩ ሰዎች ላይ ለመፍረድ ግን መብት
አለን። 13 ከቤተ ክርስቲያን ውጭ በሆኑት
በማያምኑት ላይ የሚፈርድ እግዚአብሔር
ብቻ ስለሆነ፥ይህን ለእርሱ እንተዋለን። እና
ንተ ግን ያን የአባቱን ሚስት ያገባውን ሰው
አውግዛችሁ ከቤተ ክርስቲያን ለዩት።

## ምዕራፍ 6

1 ከመካከላችሁ አንዱ ከክርስቲያን ወን
ድሙ ጋር ቢጣላ፥ፈሪሃ እግዚአብሔር ያደ
ረባቸው ሰዎች ጉዳዩን በሽምግልና እንዲያ
ዩት ማድረግ ሲገባ፥ ጉዳዩን ወደ ፍርድ
ሸንጎ አድርሶ ክስ በማቅረብ ወንድሙን ክር
ስቲያኖች ባልሆኑ ዳኞች ፊት ሊያሳጣው
ይገባል? 2 እስቲ ይታያችሁ! ፈሪሃ እግዚአ
ብሔር ያደረባቸው ሰዎች በዓለም ላይ ላይ
ቀር እንደሚፈርዱ አታውቁም? 3 ታዲያ
በዓለም ላይ መፍረድ ከቻሉ፥በክርስቲያኖች
መካከል በሚነሡ ጥቃቅን ጉዳዮች ላይ
መፍረድ ሊያቅታቸው አይገባም። እኛ ክር
ስቲያኖች በመላእክት ላይ እንኳ ለመፍረድ
እንደምንችል አታውቁም? ይህ ከታወቀም
በምድር ላይ ለሚያጋጥሙን ችግሮች እን
ዴት መፍትሔ እናጣለን? 4 ይህን የመሳ
ሰሉ ችግሮች ሲያጋጥሙን ክርስቲያን ያል
ሆኑ ዳኞች እንዲመለከቱት ጉዳዩን አንጠል
ጥለን ለክስ የምንሮጠው ታዲያ ለምንድን
ነው? 5 ለመሆኑ እንደዚህ ያለውን ጉዳይ
መርምሮ በግልግል መወሰን የሚችል ሰው
ከእናንተ መካከል እንዴት ይታጣል? የሚ
ያሳፍር ነገር ነው! 6 እንዴት ወንድም ወን
ድሙን ክርስቲያኖች ባልሆኑ ዳኞች ላይ
ይከሰዋል?
7-8 ክርስቲያን ሆኖ እርስ በርስ መካሰስ
ራሱ ውርደት ነው። እንደ ተበደላችሁ
አውቃችሁ ነገሩን ብትተዉት ይቀላል።
ሰዎች ሲያታልሏችሁ ይቅር ለእግዚአብሔር
ብላችሁ ብትተዉት እኮ ክብር ነው። እን
ዴት አድርጋችሁ ክርስቲያን ወንድሞቻች
ሁን እናንተው መልሳችሁ ትበድላላችሁ?
9 ወይስ አመፀኞች የእግዚአብሔርን
መንግሥት እንደማይወርሱ አታውቁም?
በዚህ ነገር ራሳችሁን አታታልሉት። ምክን
ያቱም አመንዝራዎችና ጣዖት የሚያመልኩ
ወይም ግብረ ሰዶም የሚፈጽሙ፥ 10 ሌቦች
ወይም ስግብግቦች፥ሰካራሞች ወይም ተሳዳ
ቢዎች እንዲሁም ቀማኞች፥ወደ እግዚአብ
ሔር መንግሥት ሊገቡ አይችሉም። 11 ከመ
ካከላችሁ ጥቂቶቻችሁ ቀድሞ እንደነዚህ
ሰዎች ነበራችሁ። አሁን ግን የእግዚአብ
ሔር ወገኖች ሆናችኋል። በጌታ በኢየሱስ
ክርስቶስና በራሱ በእግዚአብሔር መንፈስ
ከኃጢአታችሁ ስለ ታጠባችሁ ተቀድሳች
ኋል፤ጸድቃችኋልም። 12 አንድ ሰው፥ «አታ
ድርግ» ተብሎ በጌታ ያልተከለከለ እስከ
ሆነ ድረስ፥ማናቸውንም ነገር ለማድረግ እን
ደተፈቀደልኝ ይቆጠራል ሊል ይችላል።
«ተፈቅዶልኛል» የተባለው ነገር ሁሉ ግን
መልካም እንዳልሆነ ላሳስባችሁ እወዳለሁ።
ሁሉ ነገር ተፈቅዶልኛል፥ነገር ግን ልማድ
ሆኖ እንደ ባሪያ እንዲገዛኝ መንገድ አልከ
ፍትለትም።
13 'እግዚአብሔር ምግብን ለሆድ፥ሆድ
ንም ለምግብ ፈጥሮአል' ትሉ ይሆናል።
ይሁን እንጂ፥እግዚአብሔር አንድ ቀን መብ
ልንም ሆድንም የሚያጠፋበት ጊዜ ይመ
ጣል። ምክንያቱም ሰውነታችን ጥንቱንም
የተፈጠረው የእግዚአብሔር ማደሪያ እንዲ
ሆን እንጂ ለዝሙት ሥራ አይደለም።
14 እግዚአብሔር ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስን
በኃይሉ ከሞት እንዳስነሣ፥እኛንም ደግሞ
በኃይሉ ከሞት ያስነሣናል። 15 ሰውነታችሁ

የክርስቶስ የአካል ክፍል መሆኑን ታውቁ
የለ? ታዲያ አንድ ሰው የክርስቶስ የአካሉ
ክፍል የሆነውን ሰውነቱን ወስዶ ከአንዲት
አመንዝራ ሴት አካል ጋር ሊያገናኘው ይገ
ባል? እንዴት ተደርጎ! 16 አንድ ሰው ከአን
ዲት አመንዝራ ሴት ጋር የግብረ ሥጋ ግን
ኙነት ካደረገ፥ በቅዱሳት መጻሕፍት፥
«ሁለቱ አንድ አካል ይሆናሉ» ስለተባለ
ከሴትዮዋ ጋር አንድ እንደሚሆን አታውቁ
ምን? 17 ነገር ግን አካሉን ክርስቶስ እንዲያ
ዝበት ለእርሱ ፈቃድ የሚያስገዛለት ሰው፥
አካሉን ከክርስቶስ አካል ጋር አንድ አድር
ጎታል።
18 ስለዚህ ከዝሙት ሽሹ። ሰው የሚፈጽ
ማቸው ሌሎች ኃጢአቶች ሁሉ ከአካሉ
ውጪ ናቸው። ዝሙትን የሚፈጽም ሁሉ
ግን የገዛ አካሉን ይጐዳል። እንደ ዝሙት
ኃጢአት የሰውን አካል የሚያረክስና የሚ
ጐዳ ነገር የለም። 19-20 ለመሆኑ ሰውነታ
ችሁ ከእግዚአብሔር የተቀበላችሁትና የመ
ንፈስ ቅዱስ ማደሪያ መሆኑን አታውቁም?
እግዚአብሔር ሰውነታችሁን ከፍ ባለ ዋጋ
የገዛው ስለሆነ፥ ሰውነታችሁ የእርሱ እንጂ
የእናንተ አይደለም። ስለዚህ በሰውነታችሁ
እግዚአብሔርን አክብሩት።

## ምዕራፍ 7

1 ከዚህ በፊት በደብዳቤ ለጠየቃችሁኝ
ጥያቄ የሚከተለውን መልስ እሰጣችኋለሁ።
አንድ ሰው ቀደም አድርጎ ሚስት አላገባ
እንደሆነ ኑሮውን በዚያው ቢገፋበት መል
ካም ነው። 2 ነገር ግን በዝሙት ኃጢአት
ከመውደቅ ለመዳን ሲባል ማግባትን የመሰለ
ነገር የለም። ስለዚህ አንድ ወንድ ካንዲት
ሴት፥ አንዲት ሴት ካንድ ወንድ ጋር በጋ
ብቻ ሕግ ጸንተው መኖር ይገባቸዋል።
3 ባል ለሚስቱ የሚገባትን ሁሉ ያድርግ
ላት። ሚስትም እንዲሁ ለባልዋ ማድረግ
የሚገባትን ሁሉ ታድርግለት። ባጭሩ የወን
ዱን ፈቃድ ሴት ትፈጽም፤ የሴቷን ፈቃድ
ወንድ ይፈጽምላት፤ 4 ምክንያቱም ሴት ካገ
ባች በኋላ በራሷ ሰውነት ላይ ሥልጣን የላ
ትም፤ ሥልጣን ያለው ባልዋ ነው። ወንድም
ካገባ በኋላ በራሱ ሰውነት ላይ ሥልጣን የለ
ውም፤ ሥልጣን ያላት ሚስቱ ናት።
5-6 ስለዚህ ባልና ሚስት ለተወሰነ ጊዜ
በጸሎት ለመጠመድ ስትሉ በስምምነት ራሳ
ችሁን ከምትገቱበት ጊዜ በስተቀር፥ አንዱ
የሌላውን የጋብቻ መብት አይከልክለው።
በጸሎት ለመጠመድ ስትሉ ራሳችሁን ለመ
ግታት የወሰናችሁት ጊዜ ካለፈ በኋላ፥ ራሳ
ችሁን መቆጣጠር ተስኗችሁ ሰይጣን እንዳ
ይፈታተናችሁ መኝታችሁን በአንድ ላይ
አድርጉት። ይህንንም የምላችሁ እንደምክር
አድርጌ እንጂ እንደትእዛዝ አይደለም።
7 ማንም ሰው እንደ እኔ፥ ያለ ሚስት ቢኖር
የቱን ያህል ደስ ባለኝ ነበር። ነገር ግን እግ
ዚአብሔር ለእያንዳንዳችን የተለየ ስጦታ
አድሎናል። ይህም አንዳንዶቹን ትዳር
ይዘው እንዲኖሩ ሲያደርግ፥ ሳያገቡ ለመኖር
የሚያስችል ጸጋውን የሰጣቸውም አሉ።
8 ላላገቡና ባሎቻቸው ለሞቱባቸው ሴቶች
ደግሞ ይህን ምክር እሰጣቸዋለሁ። የምት
ችሉ ቢሆን እንደ እኔ ሳታገቡ ብትኖሩ
መልካም ነው። 9 ነገር ግን ራሳችሁን መግ
ዛት ካቃታችሁ ልታገቡ ትችላላችሁ። በፍ
ትወት ከመቃጠል ማግባት ይሻላልና።
10 ላገባችሁት ግን የሚከተለውን ትእዛዝ
እሰጣችኋለሁ። ይህም ትእዛዝ የእኔ ሳይሆን
የጌታ ትእዛዝ ነው። ሚስት ከባልዋ ጋር
አብራ መኖር አለባት። 11 ተለይታው ብት
ሄድ እንኳ ወይ ብቻዋን መኖር፥ አልያም
ተመልሳ ከባልዋ ጋር መታረቅ እንጂ ሌላ
ባል ማግባት አይገባትም። እንዲሁም ባል
ሚስቱን መፍታት የለበትም።
12 እዚህ ላይ ከጌታ የተሰጠ ትእዛዝ ሳይ
ሆን ከእኔ ከራሴ ልጨምር የምፈልገው
አሳብ አለኝ። የማታምን ሚስት ያለችው
ክርስቲያን ቢኖር፥ አብራው ለመኖር ከፈለ
ገች አይፍታት። 13 ያላመነ ባል ያላትም
ክርስቲያን ሴት ብትኖር፥ ባልዋ አብሯት
ለመኖር ከፈለገ ጥላው አትሂድ። 14 ምክንያ
ቱም ያላመነ ባል በአማኝ ሚስቱ ይቀደ
ሳል፤ ያላመነች ሚስትም በአማኝ ባልዋ
ትቀደሳለች። ይህ ባይሆን ኖሮ እንዲህ
ካለው ጋብቻ የሚወለዱ ልጆች እንደ ርኩ
ሳን በተቆጠሩ ነበር። እንዲህ በመሆኑ ግን
የተቀደሱ ናቸው።
15 ነገር ግን በጌታ የማያምን ባል ክርስ
ቲያን ከሆነች ሚስቱ መለየት ከፈለገ
ይለይ። የማታምንም ሴት ክርስቲያን ከሆ
ነው ባሏ መለየት ከፈለገች ትለይ። በዚህ
ጊዜ ክርስቲያን የሆነችው ሚስትም ትሁን፥
ወይም ክርስቲያን የሆነው ባል፥ እንዴት
አድርገን እንለያያለን በማለት መጨነቅ የለ
ባቸውም። ምክንያቱም እግዚአብሔር የጠ
ራችሁ በሰላም እንድትኖሩ ነው። 16 አንቺ
በሚስትነት አብረሽ በመኖርሽ፥ ባልሽ እንዲ
ድን ታደርጊ እንደሆን ምን ታውቂያለሽ?

አንተስ በባልነት አብረህ በመኖርህ፥የማታ
ምነው ሚስትህ በጌታ እንድታምንና እንድ
ትድን ታደርግ እንደሆን ምን ታውቃለህ?
17 እያንዳንዱ ሰው እግዚአብሔር እንደ
ፈቀደለትና በጠራው ጊዜ እንደ ወሰነለት
መኖር ይገባዋል። ለአብያተ ክርስቲያን
ሁሉ የምደነግገውም ሕግ ይህንኑ ነው።
18 አንድ ሰው ክርስቲያን ከመሆኑ በፊት
በኦሪት ሥርዓት መሠረት ተገርዞ ከሆነ
በመገረዙ አይጨነቅበት። ቀድሞ አልተገረ
ዘም እንደሆን ክርስቲያን ከሆነ በኋላ መገ
ረዝ አለብኝ አይበል። 19 ቁም ነገሩ የእግዚ
አብሔርን ትእዛዝ መፈጸም እንጂ፥መገረዝ
ወይም አለመገረዝ አይደለም።
20 እያንዳንዱ ሰው በጌታ ባመነ ጊዜ በነ
በረበት ሁኔታ ይኑር። 21 በጌታ ባመንክበት
ጊዜ የሰው ባሪያ ነበርክን? ከነበርክ ምንም
አትጨነቅ። ሆኖም ከባርነት ነፃ የመውጣት
ዕድል ካጋጠመህ ተጠቀምበት። 22 በጌታ
በተጠራህ ጊዜ የሰው ባሪያ የነበርክ ቢሆ
ንም፥ከሚያስፈራው የኃጢአት ባርነት ክር
ስቶስ ነፃ ያወጣህ መሆኑን አስታውስ። በሌ
ላም በኩል፥ነፃ ሆነህ ሳለ በጌታ ያመንክ
ከሆንክ፥አንተም የክርስቶስ ባርያ መሆንክን
መዘንጋት የለብህም። 23 ክርስቶስ ውድ ዋጋ
ከፍሎ የገዛችሁ ስለሆናችሁ ከእንግዲህ
ወዲህ ለማንም ሰው ባሮች አትሁኑ። 24 ወን
ድሞቼ ሆይ፥እያንዳንዱ ሰው በተጠራበት
ጊዜ በነበረበት ሁኔታ በጌታ ይኑር።
25 ስለ ልጃገረዶች ለጠየቃችሁኝ የምሰ
ጣችሁ መልስ ይህ ነው። ስለዚህ ጉዳይ
ከጌታ የተቀበልኩት ትእዛዝ የለም። ነገር
ግን ጌታ በቸርነቱ የሰጠኝ ጥበብ እምነት
የሚጣልበት በመሆኑ፥የምሰጣችሁ የራሴን
አሳብ ነው። 26 እኛ ክርስቲያኖች ይህ ያለን
በት ጊዜ ለሕይወታችን የሚያስጨንቁ ነገ
ሮች የሚያንዣብቡበት በመሆኑ ተዝናንተን
የምንቀመጥበት አይደለም። ታዲያ እንዲህ
ባለው ጊዜ ማግባቱ ችግሩን ጣምራ ስለሚያ
ደርገው በብቸኝነት መኖር ይመረጣል።
27 ሆኖም ቀደም ብለህ ሚስት አግብተህ፥
ትዳር መሥርተህ የምትኖር ከሆነ የጊዜውን
ችግር በመፍራት ሚስትህን አትፍታት።
ያላገባህም ከሆነ ለማግባት አትቸኩል።
28 ለማግባት ብትፈልጉ ግን ኃጢአት አይደ
ለምና ከማግባት ወደ ኋላ አትበሉ። ማግ
ባት የምትፈልግ ልጃገረድም ካለች ማግባቱ
ኃጢአት አይሆንባትም። የሆነ ሆኖ እንዲህ
ባለው ጊዜ ትዳር ልያዝ ማለቱ፥ችግሩን
ተደራራቢ ስለሚያደርገው በጉዳዩ አትቸኩ
ሉበት እላለሁ። 29 እዚህ ላይ ማስተዋል
የሚገባን አንድ ነገር አለ። ጊዜው አጭር
ነው። ስለዚህ ሚስት ያለው ራሱን ሚስት
እንደሌለው አድርጎ ይቁጠረው። ይህንንም
የሚያደርገው ጌታን ለማገልገል እንዲያስች
ለው ነው። 30 ደስታም ሆነ ኀዘን ወይም
የሀብት ብዛት አንድ ሰው እግዚአብሔርን
እንዳያገለግል እንቅፋት እንዲሆነው አይገ
ባም። 31 የዚህ ዓለም ተድላና ደስታ እንደ
ጥላ የሚያልፍ በመሆኑ በብልሃትና በዘዴ
ልንጠቀምበት እንጂ፥ይህን ያህል ልንጨነቅ
ለት አይገባንም።
32 ያለ ምንም አሳብና ጭንቀት ብትኖሩ
እወዳለሁ። ትዳር የሌለው ሰው ጌታን እን
ዴት አድርጎ ደስ እንደሚያሰኘው በማሰብ
ጊዜውን በአገልግሎት ያሳልፋል። 33 ባለት
ዳር ግን ጊዜውን በሙሉ በዚህ ዓይነቱ ተግ
ባር ለማዋል ያዳግተዋል። ትዳሩን ለማቃ
ናት፥ሚስቱን ለማስደሰት፥መውጣት መው
ረድ አለበት። 34 ስለዚህ ያገባ ሰው አሳቡ
በሁለት የተከፈለ ይሆናል። የባለትዳሯም
ሴት ችግር ከዚሁ የተለየ አይደለም። ያላገ
ባች ልጃገረድ ግን፥በሥጋም ሆነ በመንፈስ
በሁለንተናዋ፥ጌታን ከማገልገል በቀር ሌላ
አሳብ የላትም። በሌላ በኩል ደግሞ ባለ
ትዳር የሆነች ሴት ባሏን ለማስደሰት ደፋ
ቀና ስለምትል የምታስበው የትዳሯን መሟ
ላት ነው።
35 ይህንንም እዚህ ላይ ማንሣቴ ስለ እና
ንተው ጥቅም እንጂ አትጋቡ ለማለት አይደ
ለም። ዓላማዬም አሳባችሁ በትዳር ጣጣ
ሳይጠመድ ጌታን በበለጠ ልታገለግሉ በም
ትችሉበት ተግባር ላይ እንድትጠመዱ
ነው።
36 አንድ ሰው ፍትወተ ሥጋውን መቆጣ
ጠር አቅቶት ያጫትን ልጃገረድ ለማግባት
ቢፈልግ የሚከለክለው ነገር የለም፤ኃጢአ
ትም አይሆንበትም፤ ሊያገባ ይችላል።
37 ነገር ግን ላለማግባት ከወሰነና ራሱን
መቆጣጠር የሚያስችል ጽኑ ፈቃድ ካለው፥
በውሳኔው ሊገፋበት ይችላል፤ አለማግባቱ
መልካም ነው። 38 ስለዚህ ያገባ መልካም
አደረገ። ያላገባም ደግሞ የበለጠ አደረገ።
39 ያገባች ሴት ባሏ በሕይወተ ሥጋ እስ
ካለ ድረስ በጋብቻ ሕግ የታሠረች ናት።
ባሏ ከሞተ በኋላ ግን ሌላ ባል ማግባት
ትችላለች። ይሁን እንጂ የምታገባው ባል
ክርስቲያን መሆን አለበት። 40 እንደኔ ከሆነ
ግን ሳታገባ እንዲሁ ብቻዋን ብትኖር የበ
ለጠ ደስተኛ ሆና ትኖራለች ብዬ አስባ

ለሁ። ይህን በምልበትም ጊዜ በጌታ መን
ፈስ ተመርቼ መሆኑ ይሰማኛል።

## ምዕራፍ 8

1 ለጣዖት የተሠዋ ሥጋ ስለ መብላት
ለጠየቃችሁኝ የምሰጠው መልስ የሚከተ
ለው ይሆናል። ስለዚህ ጉዳይ እያንዳንዱ
ሰው የራሱ አስተሳሰብና እውቀት እንዳለው
መቼም የታወቀ ነው። ነገር ግን «ሁሉን
አዋቂ ነኝ» ባይነት ትዕቢት ሲያሳድር፥የእ
ግዚአብሔርን ቤተ ክርስቲያን ሊያንጽ የሚ
ችለው ፍቅር ብቻ ነው። 2 «ከእኔ በቀር
አዋቂ ላሣር ነው» የሚል ሰው አላዋቂነቱን
ይገልጣል። 3 እግዚአብሔርን ከልቡ የሚ
ወድ ሰው ግን፥በራሱ በእግዚአብሔር ዘንድ
የታወቀ ነው።
4 ለጣዖት መሥዋዕት ሆኖ የቀረበ ሥጋ
መብላት ይገባል? ወይስ አይገባም? ጣዖት
ሕይወትና ኃይል የሌለው በድን ነገር እንደ
ሆነና ፥ ከአንዱ ከእግዚአብሔር በስተቀር
ሌላ አምላክ እንደሌለ እናውቃለን። 5 አንዳ
ንድ ሰዎች በሰማይና በምድር ብዙ አማል
ክት እንዳሉ ይናገራሉ። 6 እኛ ግን ሁሉን
የፈጠረና እኛንም ገንዘቡ ያደረገን፥አንድ
አምላክ ብቻ መኖሩን እናውቃለን። እር
ሱም እግዚአብሔር አብ ነው። እንዲሁም
ሁሉ ነገር በእርሱ የተፈጠረና ሕይወትንም
የሚሰጠን አንድ ጌታ ብቻ መኖሩን እናምና
ለን። እርሱም ኢየሱስ ክርስቶስ ነው።
7 ነገር ግን አንዳንድ ክርስቲያኖች ይህን
እውነት አይገነዘቡትም። ለዘመናት ጣዖትን
ሲያመልኩ ስለኖሩ ፥ የክርስትናን እምነት
ከተቀበሉም በኋላ፥ለጣዖት መሥዋዕት ሆኖ
የቀረበ ሥጋ ሲበሉ፥ሕሊናቸው ደካማ ስለ
ሆነ በቀላሉ ይረክሳል። 8 እንደ እውነቱ
ከሆነ ምግብ ወደ እግዚአብሔር አያቀርበ
ንም ወይም አያርቀንም። ባንበላ መንፈሳዊ
ሕይወታችንን የምንጐዳ አይደለንም፥በልተ
ንም የምንጠቀመው አንዳች ነገር የለም።
9 ይህ ከሆነ፥ «ብንበላ ምን አለበት?» በማ
ለት የምታደርጉት ነገር በእምነት ደካሞች
ለሆኑት እንቅፋት እንዳይሆንባቸው መጠን
ቀቅ ይገባችኋል።
10 ለጣዖት የተሠዋ ሥጋ ቢበላ ጉዳት
የማያመጣ መሆኑን አውቀህ በቤተ ጣዖት
ተገኝተህ ስትበላ፥ይህ አድራጎትህ ትክክል
አለመሆኑ የሚሰማው ደካማ ሕሊና ያለው
አንድ ሌላ ሰው ካየህ፥አንተ ያደረግኸውን
ለማድረግ ይደፋፈራል። 11 ስለዚህ በአንተ
«አዋቂ ነኝ» ባይነት ክርስቶስ የሞተለት
እምነተ ፅኑ ያልሆነ ወንድምህ መንፈሳዊ
ሕይወቱ ትጐዳበታለች። 12 በዚህ ሁኔታ
ወንድሞቻችሁን በመጉዳታችሁና ደካማ
ሕሊናቸውን በማቁሰላችሁ የምትበድሉት
ክርስቶስንም ጭምር ነው። 13 ስለዚህ የም
መገበው ምግብ መመገብ ወንድሜን የሚያ
ሰናክለው ከሆነ፥ለወንድሜ እንቅፋት እንዳ
ልሆን በማለት እርሱን የሚያሰናክለውን
ምግብ ከመብላት እቆጠባለሁ።

## ምዕራፍ 9

1 ወንጌሉን ለማስተማር የተሾምኩት
በሰው ሳይሆን በራሱ በጌታ መሆኑን ልገል
ጽላችሁ እወዳለሁ። ጌታን ኢየሱስ ክርስቶስ
ንም፥በዓይኔ አይቼዋለሁ። እናንተም እራሳ
ችሁ ለጌታ ያበረከትኩት እውነተኛ አገልግ
ሎት ውጤት ናችሁ። ታዲያ እኔ ነፃ ሰው
አይደለሁምን? 2 ለሌሎቹ ሐዋርያ መስዬ
ባልታያቸው፥ለእናንተ ግን ቀድሞም አሁ
ንም ሐዋርያችሁ እኔው ነኝ። ይህን ማንም
ሊፍቀው አይችልም። ክርስቶስን ለማወቅና
በስሙ ለማመን የበቃችሁት በእኔ ሐዋርያ
ነት ነውና።
3 የሐዋርያነት መብት እንደሌለኝ አድር
ገው ለሚያወሩ የምሰጠው መልስ ይህ
ነው።
4 እንደ ሌሎቹ ሐዋርያትስ፥እቤታችሁ
በእንግድነት መጥቼ ለመብላትና ለመጠ
ጣት መብት የለኝም? 5 እንደ ሌሎቹ ሐዋ
ርያት፥እንደ ጌታ ወንድሞችና እንደ ጴጥ
ሮስ፥ክርስቲያን ሚስት ብትኖረኝ ኖሮ፥እር
ሷን ይዤ ለመዞር መብት የሌለኝ እኔ ብቻ
ነኝ? 6 ለሌሎቹ ሐዋርያት የሚያስፈልጋቸ
ውን ስታደርጉላቸው፥ለኑሮ የሚያስፈልገ
ንን በእጃችን ሠርተን ማግኘት የሚገባን፥
በርናባስና እኔ ብቻ ነን? 7 ራሱን ችሎ ያለ
ደመወዝ በወታደርነት የሚያገለግል ማን
አለ? ወይን ተክሎ ፍሬውን የማይበላስ፥የት
ኛው ገበሬ ነው? ወይስ ከብት አርቢ ሆኖ
ጥገቶቹ የሚታለቡትን ወተት የማይጠጣ
ይገኛል? 8 ይህን የምለው በሰው አስተሳሰብ
ብቻ ተመርኩዤ አይደለም። ይህን የሚደ
ግፍ ከኦሪቱ ሕግ ማስረጃ ማቅረብ ይቻላል።
9 ሕጉ፥ «የሚያበራየውን በሬ እንዳይበላ
አፉን አትሠረው» ይላል። እግዚአብሔር
ስለ በሬዎች በማሰብ ብቻ ይህን ያለ ይመስ
ላችኋል? 10 ይህን ማለቱ ስለ እኛም ለማስረ
ዳት ጭምር አይደለም? አዎን፥ስለ እኛም
ነው። የሚያርሰውም ሆነ የሚያበራየው
ከእህሉ ድርሻውን እንደሚያገኝ ተስፋ

በማድረግ ይሠራልና።
11 እንደምታውቁት እኛ በእናንተ ሕይ
ወት ውስጥ መንፈሳዊ ዘር ዘርተናል።
ታዲያ በምትሰጡን ሥጋዊ ነገሮች ብንጠ
ቀም፥ይህ ይብዛብን? 12 ለሌሎች ሰዎች እር
ዳታ የምታደርጉ ከሆነ ከእነርሱ የበለጠ
ነገር ከእናንተ እኛ የመቀበል መብት የለ
ንም? ነገር ግን የክርስቶስ ወንጌል እንዳይስ
ፋፋ የሚያግድ እንቅፋት እንዳይኖር ስለፈ
ለግን ፥ ሁሉን ነገር በትዕግሥት አለፍን
እንጂ እንደሚገባ በመብታችን አልተጠቀም
ንበትም።
13 እግዚአብሔርን በቤተ መቅደሱ የሚ
ያገለግሉ ለእግዚአብሔር ከቀረበው መባ
ለራሳቸው እንሥተው እንዲወስዱ፥በመሠዊ
ያው ላይ መሥዋዕት በማቅረብ የሚያገለግ
ሉትም ከሚቀርበው መሥዋዕት እንዲበሉ፥
ሕጉ እንደሚፈቅድላቸው አታውቁም?
14 እንደዚሁም የወንጌልን ቃል የሚያስተ
ምሩ መምህራንም፥ለኑሮአቸው የሚያስፈል
ጋቸውን ነገር ከምዕመናን እንዲቀበሉ ጌታ
ፈቅዶላቸዋል። 15 እኔ በበኩሌ ግን በዚህ
መብቴ አልተጠቀምኩበትም። አሁንም
ይህን መጻፌ በዚሁ መብት ለመጠቀም ፍላ
ጎት ኖሮኝ አይደለም። ወንጌልን ያለምንም
ዋጋ ስለሰበክሁላችሁ ያገኘሁት ደስታ ይህ
ነው አይባልም። ስለዚህ ይህን ከማጣ በረ
ሃብ ብሞት ይሻለኛል። 16 ወንጌልን በመስበ
ኬም ልመካበት አልችልም። ልመካበት
የማልችለውም የምሰብከው ጌታ ኢየሱስ
ስላዘዘኝ በመሆኑ ነው። ጌታ እንዳዘዘኝ የወ
ንጌሉን ቃል ሳልሰብክ ብቀር ግን ወዮልኝ።
17 ይህን ወንጌል በፍቃደኝነትና በው
ዴታ ብሰብክ ለድካሜ ዋጋ አለኝ። ነገር
ግን ያለፈቃደኝነት ባደርገው ኃላፊነቴንና
ግዴታዬን ብቻ መወጣቴ ይሆናል። 18 እን
ዲህ ከሆነ ታዲያ ደመወዜ ምንድን ነው?
የእኔስ ደመወዝ ወንጌልን በነፃ እየሰበክሁ፥
ላገኝ የሚገባኝን ጥቅም በሞተው የማገ
ኘው ደስታ ብቻ ነው።
19 ነፃ ሰው ሆኜ ሳለሁ ፥ ብዙ ሰዎችን
ወደ ጌታ ኢየሱስ ለመመለስ ስል ራሴን
የሁሉም አገልጋይ አደርጋለሁ። 20 በአይ
ሁድ መካከል በምገኝበት ጊዜ የወንጌልን
ቃል ሰምተው እንዲድኑ በማለት እንደ አይ
ሁዳዊ ሆኜ እቀርባቸዋለሁ። የአይሁድን
ልማድና ሥርዓት በሚከተሉ አሕዛብ መካ
ከል በምገኝበትም ጊዜ ምንም እንኳ በዚህ
አድራጎታቸው ባልስማማም፥ጥረቴ እንዲድ
ኑልኝ ብቻ ስለሆነ «ይህን መተው አለባ
ችሁ» ብዬ ንትርክ ውስጥ ለመግባት አልፈ
ልግም። 21 በባዕድ አምልኮና ሥርዓት ጸን
ተው በሚኖሩ አሕዛብ መካከል በምገኝበ
ትም ጊዜ፥ ከክርስትና እምነት መሠረታዊ
አሣቦች ጋር የሚቃረኑትን ጉዳዮች ሁሉ
ለጊዜው ወደ ጎን በመተው እነርሱን መስዬ
እታያቸዋለሁ። ወደ እግዚአብሔር ተመል
ሰው እንዲድኑ በማለት ሁሉንም በዚህ ዓይ
ነት እቀርባቸዋለሁ።
22 ሕሊናቸው በቀላሉ ሊደፈርስባቸው
ከሚችል ደካሞች ጋር እንደ ደካማ ሆንኩ።
በተቻለኝ መጠን ሰዎችን ሁሉ ወደ ክርስ
ቶስ እንዲመለሱ ለማድረግ እችል ዘንድ
ሁሉንም እንደጠባያቸው መቅረብ ነበረ
ብኝ። 23 ይህንንም ሁሉ የማደርገው የወን
ጌሉ ቃል እንዲደርሳቸውና በእነርሱ መዳን
ከጌታ በረከት እንዳገኝ ነው።
24 በሩጫ ውድድር ላይ እያንዳንዱ ተወ
ዳዳሪ የሚሮጠው መቼም ለማሸነፍ መሆኑ
ግልጽ ነው። በአሸናፊነት የሚሸለመው ግን
ከሯጮቹ መካከል አንዱ ነው። ስለዚህ አሸ
ንፋችሁ ሽልማት ለመቀበል ተሽቀዳደሙ።
25 እንደምታውቁት እያንዳንዱ ተወዳዳሪ
አሸናፊ ለመሆን አስቀድሞ ተገቢ የሆነ
ልምምድ ማድረግ ያስፈልገዋል። ይህን
ያህል የሚደክመውም አላፊ ጠፊ የሆነ የዋ
ንጫ ሽልማት ለማግኘት ሲል ነው። እኛ
ግን የምንጥረውና የምንግረው፥በዚህ ዓለም
ላይ ቀሪ ለሚሆን ነገር ሳይሆን ፥ ዘላለማዊ
ዋጋ ለማግኘት ነው። 26 ስለዚህ እኔ ያለ
ምንም ዓላማ አልሮጥም። የምሮጠው ለማሸ
ነፍ ነው። ወይም ደግሞ ከጥላው ጋር እን
ደሚታገል ሰው፥ያለ የሌለ ኃይሌን በከንቱ
አላባክንም። 27 አንድ ተወዳዳሪ ድል ለማድ
ረግ ሲል በየጊዜው ከባድ ልምምድ እንደ
ሚያደርግ ሁሉ ፥ ለሌሎች ሰዎች ከሰበክሁ
በኋላ እኔ ራሴ ውድቅ ሆኜ እንዳልቀር ሰው
ነቴን እየተቆጣጠርሁ የተነሣሁበትን ሩጫ
ከግቡ ለማድረስ አጥብቄ እጥራለሁ።

## ምዕራፍ 10

1 ወንድሞቼ ሆይ ፥ አባቶቻችን በሙሴ
መሪነት ወደ ምድረ በዳ በሚጓዙበት
ጊዜ፥እግዚአብሔር ደመና ከበላያቸው ሆኖ
እንዲመራቸው እንዳደረገና ቀይ ባሕርን
በደህና አቋርጠው ለመሻገር እንደበቁ ላስታ
ውሳችሁ እወዳለሁ። 2 በዚህም የሙሴ ተከ
ታዮች ለመሆን፥ሁሉም በደመናና በባሕር
ተጠመቁ። 3 በምድረ በዳም ሳሉ ሁሉም
አንድ ዓይነት መንፈሳዊ ምግብ ተመገቡ።

4 ይከተላቸው ከነበረውም መንፈሳዊ ዓለት
ሁሉም አንድ ዓይነት መንፈሳዊ መጠጥ
ጠጡ። ያም ዓለት ራሱ ክርስቶስ ነበር።
5 ይህም ሆኖ እግዚአብሔር በብዙዎቹ ስላ
ልተደሰተባቸው ሬሳቸው በበረሃ ወድቆ
ቀረ።
6 ይህ ሁሉ እነርሱ ክፉ ነገር እንደተ
መኙ፥ እኛም እንዳንመኝ፥ እነርሱ ጣዖት
እንዳመለኩ እኛም እንዳናመልክ እንድንጠ
ነቀቅ ይረዳናል። 7 በቅዱሳት መጻሕፍት፥
«ሙሴ እየመራቸው በበረሃ ይጓዙ የነበሩት
ሰዎች ሊበሉና ሊጠጡ ተቀመጡ። ከወርቅ
የሠሩትንም የጥጃ ጣዖት ለማምለክ ሊዘፍኑ
ተነሡ» ተብሎ ስለ እነርሱ ተጽፏል።
8 ከእነርሱ ጥቂቶቹ የዝሙት ተግባር
ሲፈጽሙ በመገኘታቸው፥ ሃያ ሦስት ሺህ
የሚሆኑ ሰዎች በአንድ ቀን ሞተዋል። ይህ
ደግሞ ሌላው ማስጠንቀቂያ ነው። 9 ጥቂ
ቶች ደግሞ የጌታን ትዕግሥት በመፈታተና
ቸው እባብ ነድፎ እንዳጠፋቸው፥ እኛም
ጌታን ተፈታትነን እንዳንጠፋ ያስጠነቅቀ
ናል። 10 ከእነርሱ ጥቂቶቹ በጌታ ላይ በማ
ጉረምረማቸው መልአኩን ልኮ በሞት ቀጥ
ቷቸዋል። ይህም፥ እኛም በጌታ ላይ እንዳና
ጉረመርምና በእነርሱ ላይ የደረሰው እንዳይ
ደርስብን ያስጠነቅቀናል።
11 ይህ ሁሉ የተጻፈው በእነርሱ ላይ የደ
ረሰው በእኛም ላይ እንዳይደርስ ለማስጠን
ቀቅ ምሳሌ እንዲሆነን ነው። እኛ በዘመናት
መጨረሻ የምንኖር ሰዎች በእነርሱ ላይ
ከደረሰው ነገር ትምህርት አግኝተን እንደ
እነርሱ እንዳንጠፋ መጠንቀቅ ይገባናል።
12 ስለዚህ፥ «እኔ እንደ እነርሱ በኃጢ
አት አልወድቅም» ብሎ የሚታበይ ሰው
ቢኖር እንዳይወድቅ ይጠንቀቅ። 13 በሌሎች
ሰዎች ላይ ከደረሰባቸው የተለየ ፈተና በእ
ናንተ ላይ አልደረሰባችሁም። እግዚአብሔር
ታማኝ ነው። ምክንያቱም ከምትችሉት
በላይ እንድትፈተኑ አይተዋችሁም። ነገር
ግን በምትፈተኑበት ጊዜ ፈተናውን በትዕግ
ሥት እንድትሸከሙት ኃይል እንደሚሰጣች
ሁና ከፈተናውም የምትወጡበትን መንገድ
እንደሚያዘጋጅላችሁ አስታውሱ። 14 ስለዚህ
ወንድሞቼ ሆይ፥ ከማንኛውም ዓይነት የጣ
ዖት አምልኮ ራቁ።
15 አስተዋዮች እንደመሆናችሁ መጠን፥
የምነግራችሁ ነገር እውነት መሆኑን እናን
ተው መገመት ትችላላችሁ። 16 ከበረከቱ
ጽዋ አመስግነን የምንካፈለው ወይን፥ከክርስ
ቶስ ደም ጋር ያለንን ሕብረት የሚያሳይ
አይደለምን? ከበረከቱ እንጀራ አብረን የም
ንቆርሰውስ ኅብስት፥ ከክርስቶስ ሥጋ ጋር
ያለንን ሕብረት የሚያሳይ አይደለምን?
17 እኛ ቍጥራችን ቢበዛም፥ከአንዱ ኅብስት
ተካፍለን ስለምንበላ ሁላችንም የክርስቶስ
አንድ አካል መሆናችንን እናሳያለን። 18 የእ
ሥራኤልን ሕዝብ ምሳሌ ብናደርጋቸው፥
በመሠዊያው ላይ የተሠዋውን የሚበሉ
ሁሉ፥ ከመሠዊያው ጋር አንድነት ነበራ
ቸው።
19 ይህን ስል ለጣዖት የተሠዋ መሥዋ
ዕት ዋጋ አለው ማለቴ ነውን? ጣዖትስ
እውነተኛ አምላክ ነውን? 20 እንዲህ ማለ
ቴስ አይደለም። አሕዛብ ለጣዖት ሲሠዉ፥
የሚያቀርቡት መሥዋዕት ለአጋንንት የቀረበ
እንጂ ለእግዚአብሔር የተሠዋ አይደለም።
ስለዚህ ከማያምኑ ሰዎች ጋር ተቀምጣችሁ
ለጣዖት የቀረበውን መሥዋዕት በመብላት
ከአጋንንት ጋር አንድነት እንዲኖራችሁ
አልፈልግም። 21 የጌታን ጽዋና የአጋንንትን
ጽዋ በአንድ ላይ ልትጠጡ አይገባችሁም።
ከጌታ እራት እየተሳተፋችሁ ከአጋንንት
ማዕድ ተካፋዮች ልትሆኑም አትችሉም።
22 ታዲያ ይህን በማድረግ ጌታን ታስቆ
ጡታላችሁ? ከእርሱ ይበልጥስ የምትበረቱ
ይመስላችኋል? 23 «ማንኛውም ነገር ተፈቅ
ዶልኛል» የሚሉ ሰዎች ይኖሩ ይሆናል።
ነገር ግን ማንኛውም ነገር ጠቃሚ አይደ
ለም። ደግሞም ማንኛውም ነገር የሚያን
ጽና የሚቀድስ አይደለም። 24 በሌላ በኩል
ደግሞ የራሳችንን ጥቅም ብቻ ሳይሆን ባልን
ጀራችንም የሚጠቀምበትን ማሰብ ይኖርብ
ናል።
25 ‘ይህ ለጣዖት የተሠዋ ይሆን?’ እያላ
ችሁ ሳትጠራጠሩና ሕሊናችሁን ሳታስጨ
ንቁ በየሉካንዳው ቤት የሚሸጠውን ሥጋ
ገዝታችሁ ልትመገቡ ትችላላችሁ። 26 ምክ
ንያቱም ምድርና በውስጥዋ ያሉት ነገሮች
ሁሉ፥ ለሰው ጥቅም የተፈጠሩ የእግዚአብ
ሔር ሀብት ናቸውና።
27 የማያምን ሰው ግብዣ ጠርቷችሁ
ለመሄድ ከወሰናችሁ፥ሕሊናችሁን ሳታስጨ
ንቁትና ሳትጠራጠሩ የሚቀርብላችሁን
ሁሉ መብላት ትችላላችሁ። 28 ነገር ግን
አንድ ሰው፥ «ይህ ሥጋ ለጣዖት የተሠዋ
ነው» ብሎ ከነገራችሁ፥ለጣዖት መሥዋዕት
ሆኖ የቀረበውን ሥጋ ባትበሉ ይሻላል።
29 ምክንያቱም ያንን ሥጋ ስትበሉት ሕሊና
ችሁ ባይወቅሳችሁም እንኳ፥ የዚያን ሰው
ሕሊና ስለሚጐዳው ለእርሱ ስትሉ ከመብ

ላት መቆጠቡ አስተዋይነት ነው። በሌላው
ሰው ሕሊና ደካማነት ምክንያት እኔ ለመብ
ላት ያለኝ ነፃነት ለምን ይነካ? 30 እኔ በበ
ኩሉ እግዚአብሔርን አመስግኜ በምበላው
ምግብ ሌላው ሰው ለምን ይውቀሰኝ?
31 እንግዲህ ስትበሉም ሆነ ስትጠጡ ወይም
ማንኛውንም ነገር ስታደርጉ ይህን ሁሉ
ለእግዚአብሔር ክብር ብላችሁ አድርጉት።
32 አይሁድን፥ አሕዛብንም ሆነ ክርስቲያኖ
ችን፥ማናቸውንም የሚያሰናክል ነገር አታ
ድርጉ። 33 እኔ በበኩሌ የማደርገው ነገር
በግሌ የሚጠቅመኝን ሳይሆን፥ሌሎችን የሚ
ጠቅመውንና እንዲድኑ የሚረዳቸውን
ነው።

## ምዕራፍ 11

1 እኔ የክርስቶስን ምሳሌ እንደምከተል
እናንተም የእኔን ተከተሉ። 2 ዘወትር ስለም
ታስቡኝና ያስተማርኳችሁን ትምህርት
በሥራ ላይ ስላዋላችሁት ደስታዬ የበዛ
ነው። 3 ነገር ግን ላስታውሳችሁ የምወደው
አንድ ነገር አለ። ክርስቶስ በወንዶች ላይ
ሥልጣን አለው። ባሎች በሚስቶቻቸው
ላይ ሥልጣን አላቸው። እግዚአብሔርም
በክርስቶስ ላይ ሥልጣን አለው። 4 ራሱን
ተከናንቦ ወይም ባርኔጣ አድርጎ የሚጸልይ
ወይም የሚሰብክ ወንድ፥በእርሱ ላይ ሥል
ጣን ያለውን ክርስቶስን እንዳዋረደው ይቆ
ጠራል። 5 እንደዚሁም ጠጉሯን ሳትሸፍን
ወይም ሳትከናነብ በሕዝብ ፊት የምትጸልይ
ወይም ትንቢት የምትናገር ሴት፥በእርሷ
ላይ ሥልጣን ያለውን ባሏን ታዋርደዋለች።
ምክንያቱም እራሷን ሳትከናነብ የምትጸልይ
ሴት ጠጉሯን እንደተላጨች ሴት ናትና።
6 ሴት ራስዋን የማትከናነብ ወይም ጠጉሯን
የማትሸፍን ከሆነች አሳጥራ ትቆረጠው።
ጠጉርዋን መቆረጥ የሚያሳፍር መስሎ ከታ
ያት ግን፥ራስዋን መከናነብ አለባት።
7 ወንድ የእግዚአብሔር ምሳሌ ስለሆነና የእ
ግዚአብሔር ክብር ስለሚገለጥበት ራሱን
መከናነብ አያስፈልገውም። ሴት ግን የወ
ንድ ክብር ናት። 8 ምክንያቱም የመጀመሪ
ያይቱ ሴት ከወንድ አጥንት ተፈጠረች
እንጂ ወንድ ከሴት አልተፈጠረም። 9 እንዲ
ሁም ሔዋን ለአዳም ተፈጠረችለት እንጂ
አዳም ለሔዋን አልተፈጠረላትም። 10 ስለ
ዚህ ሴት በባሏ ሥልጣን የምትተዳደር
መሆንዋን ለማሳወቅ ራስዋን መከናነብ ይገ
ባታል። ይህን በማድረጓም መላእክት ሳይ
ቀሩ ደስ ይሰኙባታል።

11 በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ ባለን ሕይ
ወት፥ወንድ ያለ ሴት ሴትም ያለ ወንድ
መኖር አይችሉም። 12 ምንም እንኳ የመጀ
መሪያይቱ ሴት ከወንድ የተገኘች ብትሆ
ንም፥ከዚያ በኋላ ወንዶች ሁሉ የሚወለ
ዱት ከሴት ሆኗል። ዞሮ ዞሮ የሁሉም
ፈጣሪ እግዚአብሔር ነው።

13 እስቲ ይህን ነገር ራሳችሁ ፍረዱት።
ሴት ራስዋን ሳትከናነብ በሕዝብ ፊት ወደ
እግዚአብሔር መጠለይ ይገባታል?
14 ወንድ ጠጉሩን ቢያስረዝም ነውር የመሆ
ኑን ያህል፥ 15 ሴት ጠጉሯን ብታስረዝም
ክብር እንደሚሆናት ተፈጥሮ እንኳን አያስ
ተምራችሁም? ለሴት ጠጉርዋ ራሷን እንድ
ትሸፍንበት ተሰጥቶአታል። 16 ነገር ግን
መከራከር የሚወድ ሰው ቢኖር የምሰጠው
መልስ ይህ ነው። እኛም ሆንን የእግዚአብ
ሔር አብያተ ክርስቲያን ከዚህ ከተናገር
ኩት የተለየ ሌላ ልማድ የለንም።

17 በጣም ቅር ስለተሰኘሁባቸው አንዳ
ንድ ነገሮች ምክሬን እሰጣችኋለሁ። የቅ
ዱስ ቁርባንን ሥርዓት ለመፈጸም በምትሰበ
ሰቡበት ጊዜ የምታደርጉት ነገር ከጥቅሙ
ጉዳቱ የሚያመዝን መሆኑን ተገንዝቤአ
ለሁ። 18 እንደምሰማው ከሆነ በምትሰበሰቡ
በት ጊዜ በመካከላችሁ መለያየት አለ። የሰ
ማሁትንም ነገር ሙሉ በሙሉ እውነት
ነው ብዬ ለመቀበል ምንም አልቀረኝም።
19 በእርግጥ ትክክለኞቹና እውነተኞቹ እነ
ማን እንደሆኑ ጉልተው መታየት እንዲ
ችሉ፥በመካከላችሁ ልዩነት መኖሩ አስፈ
ላጊ ነው።

20 የጌታን ራት በአንድነት ለመካፈል
ለይስሙላ ትሰበሰባላችሁ እንጂ የምትካፈ
ሉት የጌታን ራት አይደለም። 21 ምክንያ
ቱም በጌታ ራት ጊዜ ከፍቅር ማዕዳችሁ
በምትካፈሉበት ሰዓት፥እያንዳንዱ የራሱን
ምግብ እንደሚበላና ጥቂቶች ደግሞ ምንም
ሳያገኙ እንደሚሄዱ፥ሌሎች ግን እንደሚጠ
ግቡና እንደሚሰክሩ ሰምቻለሁ። 22 እረ
ለመሆኑ እንዲህ ያለውን ነገር ከየት አገኛች
ሁት? የምትበሉበትና የምትጠጡበት ቤት
የላችሁም? ወይስ የሚበሉትን ይዘው መም
ጣት የማይችሉትን ድሆች በማሳፈር የእግ
ዚአብሔርን ቤተ ክርስቲያን ለማቃለል
ነው? ስለዚህ አድራጎታችሁ ምን እንድላ
ችሁ ትፈልጋላችሁ? እንዳመሰግናችሁ ትፈ
ልጋላችሁ? በፍጹም አላደርገውም!

23 ስለዚሁ ጉዳይ ለእናንተ የማስተላል
ፈው ከጌታ የተቀበልኩት ትእዛዝ አለኝ።

ጌታ ኢየሱስ በተያዘበት በዚያች ሌሊት እን
ጀራ አንሥቶ አመሰገነ። 24 ከዚያም እንጀራ
ውን ቆርሶ፥ «ይህ ስለ እናንተ መሥዋዕት
አድርጌ የማቀርበው ሥጋዬ ነውና እንካ
ችሁ ብሉ፥ ለመታሰቢያዬም አድርጉት»
ብሎ ለደቀመዛሙርቱ ሰጣቸው። 25 እንደዚ
ሁም ደግሞ ከራት በኋላ ወይን ያለበትን
ጽዋ አንሥቶ ካመሰገነ በኋላ፥ «ይህ ጽዋ
በደሜ የምመሠርተው አዲስ ኪዳን ነው።
ስለዚህ ከዚህ ጽዋ በምትጠጡበት ጊዜ
ሁሉ እኔን አስታውሱኝ» ሲል ሰጣቸው።
26 ከዚህ እንጀራ በምትበሉበት፥ ከዚህም
ወይን በምትጠጡበት ጊዜ ሁሉ፥ጌታ ተመ
ልሶ እስኪመጣ ድረስ ስለ ጌታ ሞት ትመሰ
ክራላችሁ።

27 ከዚህ እንጀራ ለመብላትና ከጽዋውም
ለመጠጣት እንደሚገባው ሆኖ ሳይገኝ የሚ
በላና የሚጠጣ የጌታን ሥጋና ደም ንቋል፤
አቃሏልና ይፈረድበታል። 28 እንዲህ ካለው
ፍርድ ለመዳንም አንድ ሰው ከዚህ እንጀራ
ከመብላቱና ከዚህ ጽዋ ከመጠጣቱ በፊት
ሕይወቱን መመርመር ይገባዋል። 29 የጌታ
የኢየሱስ ሥጋ ምን እንደሆነ ሳያውቅ በድ
ፍረት የሚበላና ደሙን የሚጠጣ በራሱ
ላይ ፍርድ ያመጣል። 30 ከእናንተ ብዙዎቹ
በመንፈሳዊ ሕይወታቸው እስከ መድከምና
ብዙዎቹም እስከ መታመም፥ ጥቂቶቹም
እስከ መሞት የደረሱት ከዚሁ የተነሣ
ነው።

31 አስቀድመን ራሳችንን መርምረነው
ቢሆን ኖሮ ግን አይፈረድብንም ነበር።
32 ይሁን እንጂ ከማያምኑ የዓለም ሕዝብ
ጋር የዘላለም ሞት ፍርድ እንዳይፈረድብን
ጌታ ኢየሱስ አሁን ይገሥጸናል። 33 ስለዚህ
ወንድሞቼ ሆይ፥በጌታ ራት ጊዜ ከፍቅር
ማዕዳችሁ ለመብላት ስትሰበሰቡ በእርሳችሁ
ተጠባበቁ። 34 ከመካከላችሁ የተራበ ቢኖር
ግን፥ በተሰበሰባችሁበት ሥፍራ እንዳለ
ቅጣት በራሱ ላይ እንዳያመጣ እቤቱ
ይብላ። ስለቀረው ጉዳይ ደግሞ፥በምመጣ
በት ጊዜ አስፈላጊውን ሁሉ እነግራችኋ
ለሁ።

## ምዕራፍ 12

1 ወንድሞቼ ሆይ፥ ስለ መንፈስ ቅዱስ
ስጦታዎች የሚከተለውን እንድታውቁ እፈ
ልጋለሁ። 2 በክርስቶስ ከማመናችሁ በፊት፥
አፍ እያላቸው መናገር የማይችሉ ልዩ ልዩ
ጣዖታትን ለማምለክ ከአንዱ ቦታ ወደ
አንዱ ቦታ ትንከራተቱ እንደነበር ታስታው
ሳላችሁ። 3 አሁን ግን በመንፈስ ቅዱስ
ኃይል ተመርተው መልእክቱን የሚናገሩ
ሰዎች በመካከላችሁ ይገኛሉ። የዚህ ዓይ
ነቱ ስጦታ የታደላቸው ሰዎች የሚናገሩት
በመንፈስ ቅዱስ ተመርተው መሆን አለመ
ሆኑ እንዴት ይታወቃል? መልሱ አጭር
ነው። በመንፈስ ቅዱስ ተመርቶ ኢየሱስን
የሚራገም ሰው ሊኖር አይችልም። እንዲ
ሁም በመንፈስ ቅዱስ ካልተመራ በቀር
«ኢየሱስ ጌታ ነው» ብሎ መናገር አይች
ልም።

4 ልዩ ልዩ የመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎች
አሉ። ስጦታዎቹን ሁሉ የሚያድለው ግን
አንዱ መንፈስ ቅዱስ ነው። 5 ሁላችንም
ልዩ ልዩ በሆነ መንገድ እግዚአብሔርን
እናገለግለዋለን። አገልግሎታችን የተለያየ
መልክ ቢኖረውም፥ የምናገለግለው ጌታ
አንድ ነው። 6 እግዚአብሔር ሥራውን የሚ
ሠራው በልዩ ልዩ መንገድ ሲሆን፥ይህንም
በእኛ በልጆቹ አማካይነት እንዲከናወን
የሚያደርገው እግዚአብሔር ራሱ ነው።
7 መላዋን ቤተ ክርስቲያን እንድናገለግልበት
መንፈስ ቅዱስ፥ በእያንዳንዳችን ሕይወት
ውስጥ የእግዚአብሔር ኃይል እንዲገለጥ
ያደርጋል።

8 መንፈስ ቅዱስ ለአንዱ በጥበብ የመና
ገር ስጦታ ሲያድለው፥ለሌላው ደግሞ በእ
ውቀት የመናገር ስጦታ ይሰጠዋል። 9 ለሌ
ላው በዚያው መንፈስ የእምነት ስጦታ ሲሰ
ጠው፥ለአንዱ ደግሞ የመፈወስ ስጦታ ያድ
ለዋል። 10 ለአንዱ ተአምራት የማድረግ
ኃይል ሲሰጠው፥ ለሌላው ደግሞ ትንቢት
የመናገር ስጦታ ያድለዋል። ሌሎችም፥መን
ፈስን ሁሉ መርምረው፥ ቅዱስ የሆነውን
እርኩስ ከሆነው ለይቶ የማወቅ ስጦታ የሚ
ያገኙ አሉ። ይህ ብቻም አይደለም። ለአ
ንዱ በልዩ ልዩ ልሳኖች የመናገር ስጦታ
ሲሰጠው፥ለሌሎች ደግሞ በልሳኖች የተነገረ
ውን መልእክት የመተርጐም ስጦታ ይሰጣ
ቸዋል። 11 እንግዲህ የእያንዳንዱ ሰው
ስጦታ ምን ምን መሆን እንዳለበት የሚወስ
ንና ይህንንም ሁሉ ስጦታ የሚያድል፥ያው
አንዱ መንፈስ ቅዱስ ብቻ ነው።

12 የሰው አካል አንድ ሆኖ ሳለ ያው
አንዱ አካል ልዩ ልዩ ብልቶች እንዳሉት
የታወቀ ነው። ስለ ክርስቶስ አካል የምንና
ገረውም ከዚህ የተለየ አይደለም። እኛ ሁላ
ችን ብዙ ብልቶች ያሉት የክርስቶስ አካል
አባላት ነን። 13 አንዳንዶቻችን አይሁድ፥
ሌሎቻችን አሕዛብ ነን። አንዳንዶቻችንም

የሰው ተገዢዎች ስንሆን፥ሌሎቻችን ደግሞ
ነፃ ዜጎች ነን። ነገር ግን ሁላችንም የክርስ
ቶስ አንድ አካል ብልቶች እንድንሆን፥በአ
ንዱ መንፈስ ተጠምቀናል። አንዱንም መን
ፈስ ጠጥተናል።
[14]የሰው አካል ከተለያዩ ብልቶች የተ
ሠራ እንጂ ከአንድ ብልት ብቻ የተሠራ
አይደለም። [15]ስለዚህ እግር ፥ «እኔ እጅ
አይደለሁምና የአካል ክፍል አይደለሁም»
ቢል ፥ እንደዚህ በማለቱ የዚያ አካል ክፍል
አይደለም ማለት አይቻልም። [16]ጆሮስ ፥
«እኔ ዓይን ስላይደለሁ የአካል ክፍል አይደ
ለሁም» ቢል እንደዚህ በማለቱ የአካል
ክፍል አይደለም ማለት ይቻላል? [17]አያ
ችሁ፥አንድ አካል በሙሉ ዓይን ቢሆን ኖሮ
መስማት አይቻልም ፤ ጆሮም ብቻ ቢሆን
ኖሮ ማሽተት፥አይቻልም ነበር።
[18]እግዚአብሔር አካልን ሲፈጥር የተለ
ያዩ ብልቶች እንዲኖሩትና እያንዳንዱም
ተገቢ ሥፍራውን እንዲይዝ ማድረጉ፥የተለ
ያየ አገልግሎት እንዲሰጡ በማለት ነው።
[19]አንድ አካል የተለያዩ ክፍሎች ሳይኖሩት
አንድ ብልት ብቻ ቢሆን ኖሮ ፥ እንዲህ
ያለው አካል «ሙሉ አካል» ተብሎ የሚጠ
ራው ከምኑ ላይ ነው? [20]እግዚአብሔር
አካልን ልዩ ልዩ ብልቶች እንዲኖሩት አድ
ርጎ ቢፈጥረውም ፥ ዞሮ ዞሮ ያው አንድ
አካል ቢባል እንጂ ብዙ አካሎች አይባ
ልም። [21]ስለዚህ ዓይን እጅን፥ራስ እግርን፥
«አንተ አታስፈልገኝም» ለማለት አይች
ልም።
[22]ደካሞች መስለው የሚታዩ አንዳንድ
የአካል ብልቶች እንዲያውም ይበልጥ አስፈ
ላጊዎች ናቸው። [23]አነስተኛ ክብር ያላ
ቸው መስለው ለሚታዩን የአካል ብልቶች
የተለየ ክብር እንሰጣቸዋለን። [24]እምብዛም
ክብር የሌላቸው መስለው ለማይታዩን ብል
ቶች የተለየ እንክብካቤ ስናደርግ፥ለሌሎች
ብልቶች ግን ያንን ያህል ክብር አንሰጣቸ
ውም። እግዚአብሔር እንደነዚህ ያሉ እም
ብዛም ክብር ያላቸው መስለው የማይታዩ
ንን ብልቶቻችንን በጥንቃቄ እንድንይዛቸው
አድርጎ ፈጥሮአቸዋል። [25]ይህንንም ያደረ
ገው ብልቶች በመካከላቸው መለያየት ሳይ
ኖር እርስ በርሳቸው በመተሳሰብና በመረዳ
ዳት እንዲኖሩ ለማድረግ ነው። [26]አንዱ
ብልት ቢሠቃይ ሥቃዩ ለሁሉም ይተርፋል
እንጂ በአንዱ ላይ ብቻ ተወስኖ የሚቀር
አይደለም። አንድ ብልት ክብር በሚያገኝበ
ትም ጊዜ ደስታው የሌሎቹም ብልቶች
ጭምር እንጂ የዚያኛው ብቻ አይደለም።
[27]እናንተ ሁላችሁም የክርስቶስ አንድ
አካል መሆናችሁንና በተናጠልም፥እያንዳን
ዳችሁ ልዩ ልዩ አገልግሎት የምትፈጽሙ
የአካሉ ብልቶች መሆናችሁን መግለጽ እወ
ዳለሁ። [28]እግዚአብሔር በቤተ ክርስቲያን
ውስጥ ለእያንዳንዱ ሰው የተለያየ አገልግ
ሎት በመስጠት ሐዋርያት፥ነቢያት፥መምህ
ራን፥ተአምራት የማድረግ ስጦታ ያላቸው፥
የመፈወስ ስጦታ ያላቸው፥ሌሎችን የመር
ዳት ስጦታ ያላቸው፥ምዕመናንን የመምራ
ትና የማስተዳደር ችሎታ ያላቸውና በልዩ
ልዩ ልሳኖች የመናገር ስጦታ ያላቸው፥አድ
ርጎ መድቦአቸዋል። [29]እንደምታዩት
ሁሉም ሐዋርያት፥ሁሉም ነቢያት፥ሁሉም
አስተማሪዎች ወይም ተአምራት አድራጊ
ዎች አይደሉም። [30]እንደዚሁም ሁሉም
በሽተኞችን የመፈወስ ስጦታ፥ወይም በልዩ
ልዩ ልሳኖች የመናገር ስጦታ፥ወይም በልዩ
ልዩ ልሳኖች የተነገሩትን የመተርጐም
ስጦታ ያላቸው አይደሉም። [31]ነገር ግን፥
ከሁሉም እጅግ በጣም ብልጫ ያላቸውን
ስጦታዎች ለማግኘት ተጣጣሩ።
ከዚህ ቀጥዬም ከሁሉ ብልጫ ስላለው
መንገድ ልነግራችሁ እወዳለሁ።

## ምዕራፍ 13

[1]በሰዎችና በመላእክት ልሳን የመናገር
ችሎታ ቢኖረኝ፥ፍቅር ግን ከሌለኝ እንደሚ
ጮህ የናስ መረዋ ወይም እንደሚንሿሿ
ጽናጽል ነኝ። [2]ትንቢት የመናገር ስጦታ
ቢኖረኝ፥ወደፊት የሚሆነው ነገር ሁሉ ቢገ
ለጥልኝ፥ስለማናቸውም ነገር መታወቅ ያለ
በትን ሁሉ ባውቅ ፥ ፍቅር ግን ከሌለኝ
ጥቅሙ እምኑ ላይ ነው? አንዱ ተራራ ከነ
በረበት ተነሥቶ ወደ ሌላ ቦታ እንዲሄድ
ለማድረግ የሚያስችል እምነት ቢኖረኝ ፥
ፍቅር ግን ከሌለኝ ጥቅሙ ምንድን ነው?
[3]ያለ የሌለኝን ሁሉ ለድሆች ብመፀውት፥
ሰውነቴንም በእሳት እንዲያቃጥሉት አሳ
ልፌ ብሰጥ፥ፍቅር ግን ከሌለኝ ምንም አይ
ጠቅመኝም።
[4]ፍቅር ያስታግሣል፥በጎ ሥራ ያሠራል
እንጂ አያስመቀኝም፤ጉራ አያስነዛም፤ትም
ክህተኛም አያደርግም። [5]ፍቅር በሰው ላይ
ንቀት አያሳድርም፤የራስን ጥቅም ብቻ አይ
ፈልግም፤ፍቅር ባለበት ቂም መያዝ በቀል
ማትረፍ አይኖርም። [6]ፍቅር በሰው በደልና
ውድቀት ደስ አይለውም፤እውነት ስትወጣ
ግን ይደሰታል። [7]ፍቅር ሁሉንም ያምናል፤

ሁሉን ተስፋ ያደርጋል ፤ ሁሉንም ይታገ
ሣል።
8 ከእግዚአብሔር የምናገኛቸው የመን
ፈስ ቅዱስ ስጦታዎች ሁሉ የሚያበቁበት
ጊዜ አለ። ፍቅር ግን ዘላለማዊ ነው። ትን
ቢት የመናገሩ ስጦታ ያልፋል። በልሳኖች
የመናገሩ ችሎታም ቢሆን እንደዚሁ አንድ
ቀን ይቀራል። እውቀትም ቢሆን ያልፋል።
9 የምናውቀው በከፊል ነው። ትንቢት የምን
ናገረውም በከፊል ነው። 10 ከፍጹምነት
ደረጃ ላይ በምንደርስበት ጊዜ እነዚህ በከ
ፊል የነበሩን ነገሮች ያበቃሉ።
11 ሕፃን በነበርኩበት ጊዜ እንደ ሕፃን
አስብ፥እንደ ሕፃን እናገር፥እንደ ሕፃን እመ
ራመር ነበር። በዕድሜ እየገፋሁ ሄጄ
ከሙሉ ሰውነት ደረጃ ላይ በደረስኩ ጊዜ
ግን ፥ የሕፃንነት አስተሳሰቤን ትቼዋለሁ።
12 አሁን የማየው፥ንጹሕ ባልሆነ መስታወት
ፊቱን እንደሚያይ ሰው ነው። አንድ ቀን
ግን ፊት ለፊት እንተያያለን። አሁን ያለኝ
እውቀት ፍጹም አይደለም። በዚያን ጊዜ
ግን እግዚአብሔር ልቦናዬን ግልጥልጥ አድ
ርጎ እንደሚያየው ሁሉ፥ማናቸውንም ነገር
ጥርት አድርጌ አውቃለሁ።
13 እምነት ፥ ተስፋ ፥ ፍቅር እነዚህ ሦስቱ
ጸንተው ይኖራሉ፤ፍቅር ግን ከእነዚህ ሁሉ
የላቀ ነው።

## ምዕራፍ 14

1 ከማናቸውም ነገር አብልጣችሁ ፍቅ
ርን ፈልጉ። የመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎችን፥
በተለይም ትንቢት የመናገርን ስጦታ ለማግ
ኘት አጥብቃችሁ ፈልጉ።
2 ከመንፈስ ቅዱስ ያገኛችሁት ስጦታ
ከዚህ በፊት በማታውቁት ልሳን መናገር
ከሆነ፥የምትናገሩት ለሰው ሳይሆን ለእግዚአ
ብሔር ነው። እናንተ የምትናገሩት በመን
ፈስ ቅዱስ ኃይል ቢሆንም፥ሰዎች ሊረዱት
ስለማይችሉ ነገሩ ምሥጢር እንደሆነ ይቀ
ራል። 3 ትንቢት እየተናገረ የእግዚአብሔ
ርን መልእክት የሚያስተላልፍ ግን፥ምዕመ
ናን በመንፈሳዊ ሕይወታቸው እንዲያድጉ፥
እንዲጸኑና እንዲጽናኑ ያደርጋል። 4 በልሳን
የሚናገር የራሱን መንፈሳዊ ሕይወት እንዲ
ዳብር ሲያደርግ ፥ ትንቢት የሚናገረው ግን
የምዕመናን መንፈሳዊ ሕይወት እንዲዳብር
ያደርጋል።
5 በልሳን የመናገር ስጦታ ለሁላችሁም
ቢሰጣችሁ በወደድኩ ነበር። በበለጠ ግን
ሁላችሁም ትንቢት በመናገር የእግዚአብሔ
ርን መልእክት ብታስተላልፉ ደስ ይለኛል።
ምክንያቱም በልሳን የሚናገር ሰው ትር
ጉሙ ምን ማለት እንደሆነ ካላስረዳ በቀር፥
ምዕመናን የሚያገኙት አንዳችም ጥቅም
ሊኖር አይችልም። ትንቢት የሚናገር ግን
ምዕመናን ሊረዱት በሚችሉት ቋንቋ ስለሚ
ናገር ፥ የምዕመናን መንፈሳዊ ሕይወት የበ
ለጠ እንዲዳብር ያደርጋል።
6 ወንድሞቼ ሆይ ፥ ወደ እናንተ መጥቼ
በልሳን ብናገር ምን እጠቅማችኋለሁ? ነገር
ግን እግዚአብሔር የገለጠልኝን ምሥጢር፥
እውቀትን፥እንዲሁም ለወደፊቱ የሚሆነው
ንና ታላቅ ቁም ነገር ያለውን የእግዚአብ
ሔር ቃል ፥ ባስተላልፍላችሁና ባስተምራ
ችሁ የበለጠ እጠቅማችኋለሁ። 7 ዋሽንትና
ክራር የመሳሰሉት የሙዚቃ መሣሪያዎች
ቅኝታቸው ያማረና የተስተካከለ ካልሆነ
በስተቀር፥አንዱ ዜማ ከሌላው ዜማ ተለይቶ
ሊታወቅ አይችልም። 8 ክተት ሠራዊት ፥
በሚባልበት ጊዜ የሚነፋው የመለከት
ድምፅ ትክክለኛውን የጥሪ ድምፅ ካላሰማ
የጦር ሠራዊቱ በምን አውቆ ለጦርነት ይዘ
ጋጃል? 9 እናንተም ሰው ሊገባው የማይችል
ቋንቋ ብትናገሩ ማን ሊያስተውልላችሁ
ይችላል?
10 በዓለም ላይ ሰዎች አሳባቸውን የሚለ
ዋወጡባቸው በብዙ መቶ የሚቆጠሩ ልዩ
ልዩ ቋንቋዎች አሉ። 11 አንድ ሰው በቋን
ቋው በሚናገርበት ጊዜ እኔ ቋንቋውን ካላ
ወቅሁት ልንግባባ አንችልም። 12 እንደዚ
ሁም እናንተ የመንፈስ ቅዱስ ስጦታን አጥ
ብቃችሁ የምትፈልጉ ስለሆነ ፥ በቅድሚያ
የምዕመናንን መንፈሳዊ ሕይወት ለማዳበር
የምትችሉበትን ስጦታ ለማግኘት ተጣጣሩ።
13 ስለዚህ በልሳን የመናገር ስጦታ ያለው
ሰው፥የተናገረውን ምዕመናን እንዲረዱለት፥
የመተርጐም ስጦታ እንዲታደለው ይጸ
ልይ። 14 ምክንያቱም በልሳን በምጸልይበት
ጊዜ በመንፈስ ስለምጸልይ ምን ብዬ እንደ
ምጸልይ አእምሮዬ አይረዳውም። 15 ታዲያ
ለዚህ መፍትሔው ምንድነው? በመንፈስ
ብቻ ሳይሆን በአእምሮም ጭምር እጸልያ
ለሁ። በመንፈስ ብቻ ሳይሆን በአእምሮም
ጭምር እዘምራለሁ። 16 ነገር ግን አንተ
እግዚአብሔርን በልሳን ስታመሰግን፥ለነገሩ
እንግዳ የሆነ ሰው ፥ በጸሎትህ ሊተባበርህ
እንዴት ይችላል? የጸሎትህን ትርጉም ሳይ
ረዳው እንዴት አድርጎ አሜን ማለት ይቻለ
ዋል? 17 አንተ ተገቢውን የምስጋና ጸሎት
ለእግዚአብሔር ብታቀርብም ፥ አብረውህ

ያሉት ግን ሊታነጹበት አይችሉም።
18 ከሁላችሁ የበለጠ በልሳኖች የመናገር
ስጦታ ስለተሰጠኝ እግዚአብሔርን አመሰግን
ዋለሁ። 19 ይሁን እንጂ በቤተ ክርስቲያን
ለሥርዓተ አምልኮ በምንሰበሰብበት ጊዜ
ሌሎች ሊረዱዋቸው በማይችሉ ልሳናት
አሥር ሺህ ቃላት ከመናገር፥በሚያውቁት
ቋንቋ አምስት ቃላትን ብናገር እወዳለሁ።
ምክንያቱም የምናገረው ስለሚገባቸው ትም
ህርት ሊያገኙበት ይችላሉና ነው።
20 ወንድሞቼ ሆይ፥ለክፉ ነገር እንደ
ሕፃናት ሁኑ እንጂ በአስተሳሰባችሁስ እንደ
ሕፃናት አትሁኑ። ምን ጊዜም በአስተሳሰብ
የበሰላችሁ ሆናችሁ መገኘት አለባችሁ።
21 በቅዱሳት መጻሕፍት ውስጥ፥ «ባልተለ
መዱ ቋንቋዎች በሚናገሩና እንግዳ በሆኑ
ሰዎች አንደበት ለዚህ ሕዝብ እናገራለሁ፤
ይህም ሆኖ እንኳ አይሰሙኝም» የሚል
ቃል ተጽፎ ይገኛል። 22 ስለዚህ በልሳን
መናገር የእግዚአብሔርን ኃይል እንዲያዩ፥
ምልክትነቱ ለማያምኑ ሰዎች እንጂ ለክርስ
ቲያኖች አይደለም። ትንቢት የመናገር
ስጦታ ግን ምልክት የሚሆነው ለክርስቲያ
ኖች እንጂ ለማያምኑ ሰዎች አይደለም።
23 ስለዚህ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ከማያ
ምኑ ሰዎች ጋር በምትሰበሰቡበት ጊዜ እያ
ንዳንዱ ክርስቲያን ለአድማጮች በልሳን
ቢናገር፥የማያምኑት፥ «እነዚህ ሰዎች አብደ
ዋል እንዴ የሚለፈልፉት?» ሊሏችሁ
ይችላሉ። 24 ነገር ግን ትንቢት በመናገር
መልእክትን ከእግዚአብሔር በምታስተላል
ፉበት ጊዜ፥የማያምን ወይም ለነገሩ እንግዳ
የሆነ ሰው በስብሰባችሁ ላይ ቢገኝ፥ከተነገ
ረው የትንቢት ቃል የተነሣ ኃጢአተኛ
መሆኑን ይረዳል፤የሚሰማውም ቃል ይወቅ
ሰዋል። 25 በልቡ የደበቀውም ምሥጢር
ወለል ብሎ ስለሚታየው፥በፊቱ ተደፍቶ
እግዚአብሔርን ያመልካል። «በእውነት
እግዚአብሔር ከእናንተ ጋር ነው» በማለት
ይመሰክራል።
26 የተወደዳችሁ ወንድሞች ሆይ፥ከዚህ
ምን መረዳት የምንችል ይመስላችኋል?
በምትሰበሰቡበት ጊዜ የምዕመናን መንፈሳዊ
ሕይወት እንዲዳብር፥እያንዳንዱ ምዕመን፥
መዝሙር፥ስብከት፥ወይም የትንቢት ቃል
ለማሰማት፥በልሳን ለመናገር ወይም በልሳን
የተነገረውን ለመተርጐም ዝግጁ ይሁን።
27 በልሳን የሚናገሩ ቢኖሩ በየተራ ይናገሩ።
ሆኖም ቍጥራቸው ከሁለት ወይም ከሦስት
መብለጥ የለበትም። የመተርጐም ስጦታ
ያለው ምዕመን የተነገረውን ይተርጉም።
28 ይሁን እንጂ የመተርጐም ስጦታ ያለው
ሰው ከሌለ በልሳን የመናገር ስጦታ ያለው
ሰው ድምፁን ሳያሰማ በጸጥታ ከእግዚአብ
ሔር ጋር ይነጋገር።
29 ትንቢት የሚናገሩ ሁለት ወይም
ሦስት ሆነው ተራ በተራ ይናገሩ። ሌሎ
ችም የሚነገረውን በጥንቃቄ አድምጠው
ትንቢቱ ትክክል መሆን አለመሆኑን ይመር
ምሩ። 30 በጉባኤው ላይ ከሚገኙት ምዕመ
ናን መካከል አንዱ ከእግዚአብሔር መልእ
ክት ቢቀበል፥በመናገር ላይ ያለው ምዕመን
ንግግሩን አቋርጦ መልእክቱን እንዲያሰማ
ለዚያኛው ተራ ይስጠው። 31 በዚህ ዓይነት
እያንዳንዱ ሰው መንፈሳዊ በረከትንና መታ
ነጽን እንዲያገኝ፥ሁላችሁ ተራ በተራ ትን
ቢት መናገር ትችላላችሁ። 32 የነቢያት
መንፈስ ለነቢያት ይታዘዛል። 33 ምክንያ
ቱም እግዚአብሔር የሰላምና የሥርዓት
እንጂ የሁከት አምላክ አይደለም።
34 ሴቶች፥በሁሉም አብያተ ክርስቲያን
እንደ ተለመደው፥በምዕመናን ስብሰባ ላይ
ዝም ይበሉ። በኦሪት ሕግ እንደ ተጻፈ
ሴቶች እንዲታዘዙ እንጂ በጉባኤ ላይ እንዲ
ናገሩ አልተፈቀደላቸውም። 35 ለማወቅ
የሚፈልጉት ነገር ካለ፥ባሎቻቸውን እዚ
ያው ቤታቸው ይጠይቁ። ሴት ስብሰባ ላይ
መናገር አይገባትም።
36 የእግዚአብሔርን ቃል የምታውቁ እና
ንተ ብቻ ናችሁን? ወይስ የእግዚአብሔር
ቃል የተሰጠው ለእናንተ ብቻ ነው?
37 ‹እኔ ነቢይ ነኝ› ወይም ‹መንፈሳዊ
ስጦታ አለኝ› የሚል ሰው ቢኖር ይህ የጻፍ
ኩላችሁ የጌታ ትእዛዝ እንደሆነ ማወቅ አለ
በት። 38 «ይህን ትእዛዝ አልቀበልም»
የሚል ቢኖር፥እናንተም አትቀበሉት።
39 ስለዚህ ወንድሞቼ ሆይ፥ትንቢት የመ
ናገር ስጦታ እንድታገኙ በብርቱ ተጣጣሩ።
በልሳን መናገርንም አታቋርጡ። 40 ነገር
ግን፥ማናቸውም ነገር በአግባብና በሥርዓት
ይከናወን።

## ምዕራፍ 15

1 ወንድሞች ሆይ፥ስላስተማርኳችሁ የወ
ንጌል ቃል ላስታውሳችሁ እፈልጋለሁ።
ይህን የወንጌል ቃል ተቀብላችሁና በእር
ሱም ጸንታችሁ ከኖራችሁ ትድናላችሁ።
2 አለበለዚያ ግን፥እምነታችሁ ከንቱ ነው
ማለት ነው። 3 እኔ የተቀበልኩትን የጌታ
ቃል ለእናንተ አስተላልፌላችኋለሁ። ይህም

ቃል ፥ በቅዱሳት መጻሕፍት እንደተጻፈው
«ክርስቶስ ስለ ኃጢአታችን ሞተ፥ ተቀበረ።
4 በሦስተኛውም ቀን ከሞት ተነሣ» የሚል
ነው። 5 ክርስቶስ ከሞት ከተነሣ በኋላ ለጴ
ጥሮስ፥ቀጥሎም 'ለአሥራ ሁለቱ' ሐዋርያት
ተገልጾላቸዋል። 6 ቀጥሎም በአንድ ጊዜ
ከአምስት መቶ ለሚበልጡ ተከታዮቹ ታይ
ቷቸዋል። ከእነዚህም ሰዎች መካከል አብዛ
ኞቹ ዛሬም በሕይወት አሉ። አንዳንዶቹ
ግን ከዚህ ዓለም በሞት ተለይተዋል። 7 በተ
ጨማሪም ጌታ ፥ ለያዕቆብ ቀጥሎም ለሐዋር
ያት በሙሉ ታይቷል። 8-9 በመጨረሻም
ከሐዋርያት ሁሉ ለማንሰውና እንደ ጭን
ጋፍ ለምቆጠረው ለእኔ ተገለጠልኝ። እኔ
ሐዋርያ ተብዬ መጠራት የሚገባኝ አይደለ
ሁም። ምክንያቱም እኔ የእግዚአብሔርን
ቤተ ክርስቲያን አሳድድ ነበር።

10 ነገር ግን በእግዚአብሔር ጸጋና ቸር
ነት ይኸው ዛሬ እዚህ ደርሻለሁ። የተሰጠ
ኝም ጸጋ ከንቱ አልሆነም። ጌታን ከሌሎቹ
ሐዋርያት ሁሉ በበለጠ በማገልገል ደክሜአ
ለሁ። ይህን ሁሉ አገልግሎት ላበረክት የቻ
ልሁትም እግዚአብሔር በሰጠኝ ጸጋ እንጂ
በእኔ ብርታት አይደለም። 11 እንግዲህ በበ
ለጠ የለፋነው እኔም ልሁን ወይም እነርሱ፥
የምንሰብከው የወንጌል ቃል ዞሮ ዞሮ ያው
አንድ ነው። እናንተም ያመናችሁት ይህንኑ
ነው።

12 ታዲያ እኛ «ክርስቶስ ከሞት ተነሥ
ቷል» ብለን ስናስተምር ከእናንተ መካከል
አንዳንድ ሰዎች «ሙታን አይነሡም»
ብለው የሚያስተምሩት ለምንድን ነው?
13 የሞቱት ከሞት የማይነሡ ከሆነማ ክርስ
ቶስም ከሞት አልተነሣም ማለት ነዋ!
14 ክርስቶስ ከሞት ካልተነሣማ የእኛም
ማስተማር ሆነ የእናንተም ማመን ምን
ጥቅም አለው? 15 እንዲህ ከሆነ ደግሞ ፥
«እግዚአብሔር ክርስቶስን ከሞት አስነሥቶ
ታል» ብለን በመናገራችን እግዚአብሔር
ያላደረገውን አደረገ ብለን ዋሽተናላ!
እኛም በደለኞች ነን ማለት ነዋ! የሞቱት
ሰዎች ከሞት የማይነሡ ከሆነም፥እግዚአብ
ሔር ክርስቶስን ከሞት አላስነሣውም ማለት
ነው። 16 የሞቱት ከሞት ካልተነሡ ደግሞ፥
ክርስቶስም ከሞት አልተነሣም ማለት
ነው። 17 ክርስቶስ ከሞት ካልተነሣ በእርሱ
ማመናችሁ እንዲያው በከንቱ ነው። ይህም
እስከ አሁን ድረስ ከኃጢአታችሁ ያልተገላ
ገላችሁ መሆኑን ያሳያል። 18 እንደዚሁም
በጌታ አምነው የሞቱት ክርስቲያኖች ሁሉ
ጠፍተዋል ማለት አይደለምን? 19 አያችሁ፥
ክርስቶስን ተስፋ የምናደርገው ለዚች ምድ
ራዊ ሕይወት ብቻ ከሆነ ፥ ከሰዎች ሁሉ
ይልቅ ያልታደልን ምስኪኖች እኛ ክርስቲ
ያኖች ነን ማለት ይቻላል።

20 እውነቱ ግን ፥ ክርስቶስ ገና ወደፊት
ከሞት ለሚነሡት ሁሉ ቀዳሚ ሆኖ መነ
ሣቱ ነው።

21 በአንድ ሰው ምክንያት ሞት በሰው
ልጆች ላይ እንደመጣ ሁሉ፥ከሰው ዘር በተ
ወለደው በክርስቶስ ደግሞ ከሞት ለመነሣት
ተችሎአል። 22 ሰው ሁሉ በአዳም ምክን
ያት እንደሚሞት በክርስቶስ ምክንያት ሕይ
ወት ያገኛል። 23 ነገር ግን ሁሉም ከሞት
የሚነሡት በየተራ ነው። በመጀመሪያ ክር
ስቶስ የሁሉም ቀዳሚ ሆኖ ተነሥቶአል።
ቀጥሎም እርሱ ዳግም በሚመጣበት ጊዜ
የእርሱ ተከታዮች በሙሉ ከሞት ይነሣሉ።

24 ከዚያም ክርስቶስ የዲያብሎስን ኃይ
ልና ሥልጣን ካፈራረሰ በኋላ፥መንግሥትን
ለእግዚአብሔር አብ በሚያስረክብበት ጊዜ
የዓለም መጨረሻ ይሆናል። 25 እግዚአብ
ሔር ጠላቶቹን ከእግሩ ሥር እስኪያውላ
ቸው ድረስ ክርስቶስ መንገሥ ይገባዋል።
26 በመጨረሻም የሚሸነፈው ጠላት ፥ ሞት
ነው። 27 ምክንያቱም በቅዱሳት መጻሕ
ፍት ፥ «እግዚአብሔር ማናቸውንም ነገር
ከእግሩ በታች አስገዝቶለታል» ተብሎ ተጽ
ፎአል። «ማናቸውም ነገር ተገዝቶለታል»
የሚለው ቃል ማናቸውንም ነገር እንዲገዛ
ለት ያደረገውን እግዚአብሔርን አይጨም
ርም። 28 ክርስቶስ ጠላቶቹን ሁሉ አሸንፎ
ከእግሩ ሥር ካደረገ በኋላ፥ማናቸውም ነገር
እንዲገዛለት ያደረገው እግዚአብሔር አብ
በሁሉም ነገር ላይ ሥልጣን እንዲኖረው
ወልድ ራሱ በአብ ሥልጣን ሥር ይሆናል።

29 እንግዲህ ሙታን ከሞት የማይነሡ
ከሆነ ታዲያ ደለ ሙታን የሚጠመቁት
ሰዎች ትርፋቸው ምንድነው? ሙታን
አንድ ቀን እንደሚነሡ ካላመኑስ ለምን
ይህን ያደርጉታል?

30 ሙታን ከሞት የማይነሡ ከሆነ እኛስ
በየጊዜው ለሞት አደጋ ተጋልጠን የምንኖ
ረው ለምንድን ነው? 31 ወንድሞች ሆይ፥
በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ በእናንተ
ትልቅ ትምክህት ስላለኝ፥በድፍረት የሚሰ
ማኝን እነግራችኋለሁ። እኔ በየቀኑ ሞት
ያጋጥመኛል። 32 ሙታን የማይነሡ ከሆነ፥
እንደ «አውሬ» ከሚቆጠሩ ሰዎች ጋር በኤ
ፌሶን ያን ያህል ምን አታገለኝ? ያን ያህል

የታገልኩት ለዚች ምድራዊ ሕይወት
ጥቅም ብቻ ከሆነ፥ታዲያ የማተርፈው ምን
ድነው? ከሙታን መነሣት ከሌለማ ሁሉን
እርግፍ አድርገን ትተን፥ «ሞት ላይቀር
ምን አስጨነቀን? ነገ ስለምንሞት ዛሬ እን
ብላ፥ እንጠጣ፥ እንጨፍርም» እንደሚሉት
ሰዎች መሆን ይገባን ነበር።
33 በዚህ ጉዳይ እንዳትሳሳቱ። «መጥፎ
ጓደኛ መልካሙን ጠባይ ያበላሻል» ይባላ
ልና እንዳትታለሉ ተጠንቀቁ። 34 ተጨ፥ወደ
ልቦናችሁ ተመለሱ! ኑሯችሁ ሥርዓት ይኑ
ረው፤ ኃጢአትን መሥራት ተዉ። አንዳንዶ
ቻችሁ ስለ እግዚአብሔር ነገር ግድ የላች
ሁም። እንደ እውነቱ ከሆነ በዚህ ሁኔታ
ችሁ ልታፍሩበት ይገባል።
35 «ሙታን ሊነሡ የሚችሉት እንዴት
ነው? በሚነሡበትስ ጊዜ የሚኖራቸው
አካል ምን ዓይነት ነው?» የሚል ይኖር
ይሆናል። 36 አንተ ሞኝ! የምትዘራው
እህል ካልሞተና አፈር ውስጥ ገብቶ ካልበ
ሰበሰ በስተቀር፥ሕይወት ሊኖረውና ሊበቅል
አይችልም። 37 የምትዘራት አንዲት የስንዴ
ቅንጣት፥ወይም የሌላ እህል ዘር ነች እንጂ
ዋናውን የአትክልት አካል አይደለም። በበ
ቀለችና ባደገች ጊዜ ግን አንተ ከዘራኸው
ዘር የተለየ መልክና አካል ይኖራታል።
38 እግዚአብሔር ለዚያች ዘር የሚሰጣት
የወደደውን አካል ነው። ለእያንዳንዱ የእ
ህል ዘር ራሱን የቻለ የየራሱ የሆነ መልክና
አካል እንዳለው ሁሉ፥ 39 ሥጋ የለበሱ ፍጥ
ረታትም አካል አንድ ዓይነት አይደለም፤
ይለያያል። የሰው ሥጋ አንድ ዓይነት
ሲሆን፥የእንስሳት ሥጋ ደግሞ ሌላ ዓይነት
ነው። የወፎችም ሥጋ እንደዚሁ የተለየ
ነው። የዓሣም ሥጋ ከሌሎቹ እንስሳት ሥጋ
ጋር አንድ አይደለም።
40 እንደዚሁም በሰማይ ያሉት መላእክት
ያላቸው አካል እኛ ሰዎች ካለን አካል የተ
ለየ ነው። ክብራቸው ከክብራችን፥ግርማ
ቸው ከግርማችን ይለያል። 41 ፀሐይ የራሷ
የሆነ ውበት ሲኖራት ጨረቃም እንደዚሁ
የራሷ የሆነ ውበት አላት። ከዋክብትም የየ
ራሳቸው የሆነና የተለያየ ውበት አላቸው።
በከዋክብት መካከል እንኳ የአንዱ ኮከብ
ውበትና ብሩኅነት ከሌላው ኮከብ ውበትና
ብሩኅነት ጋር አይመሳሰልም፤ይለያያል።
42 የሙታን ትንሣኤም እንደዚሁ ነው።
ይህ የሚሞተው ምድራዊ አካላችን ተቀ
ብሮ ይፈርሳል፤በስብሶ የነበረውም በአዲስ
አካል የማይበሰብስ ሆኖ ይነሣል። 43 ሲቀ
በር የተዋረደና ደካማ የነበረው፥ክብርና
ኃይልን ተጎናጽፎ ይነሣል። 44 በሚቀበር
በት ጊዜ ሥጋዊ አካል የነበረው፥በሚነሣ
በት ጊዜ መንፈሳዊ አካል ይሆናል። ሥጋዊ
አካል እንዳለ ሁሉ መንፈሳዊ አካልም አለ።
45 በቅዱሳት መጻሕፍት፥ «የመጀመሪ
ያው ሰው አዳም ሕይወት ያለው ፍጥረት
ሆነ» ተብሎ ተጽፎአል። ዳግማዊው አዳም
ክርስቶስ ግን ሕይወት የሚሰጥ መንፈስ
ነው።
46 በመጀመሪያ የመጣው ሥጋዊው
እንጂ መንፈሳዊው አልነበረም። መንፈሳ
ዊው የመጣው ከሥጋዊው በኋላ ነው።
47 አዳም የተፈጠረው ከመሬት ነበር። ዳግ
ማዊው አዳም ክርስቶስ ግን የመጣው ከሰ
ማይ ነው። 48 ሰዎች ሁሉ እንደ አዳም
ከመሬት የተፈጠረ አካል አላቸው። ነገር
ግን በሰማይ ደግሞ እንደ ክርስቶስ ሰማያዊ
አካል ይኖራቸዋል። 49 ከመሬት የተፈጠረ
ውን የአዳምን አካል እንደ ተቀበልንና እር
ሱን እንደ መሰልን ሁሉ፥በትንሣኤ ጊዜ
ደግሞ ከሰማይ የመጣውን ክርስቶስን እንመ
ስለዋለን።
50 እንግዲህ ከሥጋና ከደም የተፈጠረ
አካል ወደ እግዚአብሔር መንግሥት ሊገባ
አይችልም። ሚች ፈራሽና በስባሽ የሆነ አካ
ልም የማይሞተውንና የማያልፈውን መንግ
ሥት ሊወርስ አይችልም። 51 እነሆ ላይ
አንድ ምሥጢር እነግራችኋለሁ። እኛ ሁላ
ችን አንሞትም፤ 52 የመጨረሻው መለከት
በሚነፋበት ጊዜ በቅጽበት ሁላችን እንለወ
ጣለን። መለከቱ ሲነፋ የሞቱት ክርስቲያ
ኖች ሁሉ በማይሞትና በማይበሰብስ ሕያው
አካል ይነሣሉ። እኛ በሕይወት ያለነውም
ደግሞ እንለወጣለን። 53 ይህ የሚሞተው፥
የሚበሰብሰውና የሚፈርሰው አካላችን የማ
ይሞተውን፥የማይበሰብሰውንና የማይፈርሰ
ውን አካል ይለብሳል።
54 ይህ የሚሞተው፥የሚበሰብሰውና የሚ
ፈርሰው አካል፥የማይሞተውን የማይበሰብስ
ውንና የማይፈርሰውን አካል በሚለብስበት
ጊዜ በቅዱሳት መጻሕፍት፥ «ሞት ድል
በመነሣት ተዋጠ» ተብሎ የተጻፈው ቃል
ይፈጸማል። 55 እንዲሁም፥ «ሞት ሆይ፥
ያንተ ድል መንሣት የታለ? የምትጐዳበት
መውጊያህስ የት አለ?» ተብሎ እንደ ተጻ
ፈው ይሆናል። 56 የሞት መውጊያው ኃጢ
አት ነው። የኃጢአትም ኃይል ሕገ ኦሪት
ናት። 57 ነገር ግን በጌታችን በኢየሱስ ክርስ
ቶስ ድል እንድንነሣ ላደረገን ለእግዚ

አብሔር ምስጋና ይድረሰው።
58አሁንም ወንድሞቼ ሆይ፣ በምንም
ነገር ሳትናወጡ ጸንታችሁ ቁሙ። የጌታን
ሥራ ለማከናወን የምትደክሙት ድካም
ሁሉ በከንቱ የሚቀር አለመሆኑን ተረድታ
ችሁም ያለማቋረጥና ያለመሰልቸት ግፉ
በት።

## ምዕራፍ 16

1በኢየሩሳሌም የሚኖሩትን ክርስቲያ
ኖች ለመርዳት የምታዋጡትን የገንዘብ
መዋጮ ለገላትያ አብያተ ክርስቲያን በሰጠ
ሁት ትእዛዝ መሠረት አድርጉት። 2የገን
ዘብ መዋጮው እኔ በምመጣበት ጊዜ እንዳ
ይሆን፣እያንዳንዳችሁ ጥራችሁ ግራችሁ ካገ
ኛችሁት ገቢ ላይ የተቻላችሁን ያህል እን
ሥታችሁ በየሳምንቱ እሑድ እሑድ እንዲ
ጠራቀም አድርጉ። 3በምመጣበትም ጊዜ
ለዚህ ለተቀደሰ ተግባር ያዋጣችሁትን ገን
ዘብ ራሳችሁ የምትመርጧቸው ታማኝ
ሰዎች፣ ወደ ኢየሩሳሌም ይዘው እንዲሄዱ
ከመሸኛ ደብዳቤ ጋር እልካቸዋለሁ። 4የእ
ኔም መሄድ አስፈላጊ ሆኖ ከተገኘ አብሬአ
ቸው እሄዳለሁ።
5ወደ እናንተ የምመጣው በመቄዶንያ
በኩል ሳልፍ ነው። እዚያም ብዙ ጊዜ አል
ቆይም። 6ረዘም ላለ ጊዜ፣ምናልባትም ክረ
ምቱን በሙሉ፣ እናንተ ዘንድ እቆይ ይሆ
ናል። እናንተ ዘንድ ከቆየሁ በኋላ፣ ከዚያ
ለመንገዶ የሚያስፈልገኝን አሰናድታችሁ
የምትሸኙኝ እናንተው ናችሁ። 7ወደ እና
ንተ የምመጣው በችኰላ አይቻችሁ ለመ
ሄድ ሳይሆን፣ ረዘም ላለ ጊዜ አብሬአችሁ
ለመቆየት ስለሆነ፣እስቲ የጌታ ፈቃድ ይጨ
መርበት። 8እስከ ጴንጤቆስጤ በዓል ድረስ
ግን እዚሁ ኤፌሶን ለመቆየት ወስኛለሁ።
9የምቆየውም ለሌላ ሳይሆን፣እዚህ የእግዚ
አብሔርን ቃል ለማስተማር ታላቅ ዕድል
ስላገኘሁ ነው። ሆኖም ብዙ ተቃዋሚዎች
አሉብኝ።
10ጢሞቴዎስ ወደ እናንተ የመጣ እንደ
ሆነ እንግድነት እንዳይሰማው አድርጋችሁ
በሚገባ ተቀበሉት። እርሱም እንደ እኔ የጌ
ታን ሥራ የሚሠራ ነውና። 11ወጣትነቱን
በማየት እንዳትንቁት አደራ። ከሌሎች ወን
ድሞች ጋር በቶሎ ወደ እኔ እንዲመጣ ስለ
ምጠብቀው ለጉዞው በሚያስፈልገው ነገር
ሁሉ ረድታችሁ ሸኙልኝ። 12ወንድማችን
አጵሎስ ከሌሎች ወንድሞች ጋር ሆኖ ወደ
እናንተ እንዲመጣ ለምኜው ነበር። ነገር
ግን በአሁኑ ጊዜ ወደ እናንተ መምጣቱን
እግዚአብሔር የፈቀደለት ሆኖ ስላላገኘው
ለመምጣት አልፈለገም። ወደፊት ግን ሲመ
ቸው መምጣቱ እንደማይቀር ነግሮኛል።
13ንቁ፤በእምነታችሁ ጸንታችሁ ቁሙ፤
በርቱ ጠንክሩም። 14የምታደርጉትንም
ሁሉ በበጎነትና በፍቅር አድርጉት።
15ወንድሞቼ ሆይ፣እስጢፋኖስንና ቤተ
ሰቡን ታስታውሱ የለ? በደቡባዊ ግሪክ የመ
ጀመሪያዎቹ ክርስቲያኖች እነርሱ ሲሆኑ፣
በየሥፍራው የሚገኙትን ክርስቲያኖች ለማ
ገልገል የቱን ያህል ራሳቸውን እንደሰጡ
አትዘነጉትም። 16ስለዚህ እነርሱንና እንደ
እነርሱ ተግተው፣ነቅተው እናንተን በማገል
ገል የሚደክሙትን ሁሉ እንድትታዘዙአ
ቸው አደራ። 17እስጢፋኖስ፣ ፈርዶናጥስና
አካይቆስ ሊያዩኝ በመምጣታቸው ደስ
ብሎኛል። እናንተ እዚህ ባለመኖራችሁ
የጐደለኝን ሁሉ አሟልተውልኛል። 18የእ
ናንተን መንፈስ እንዳሳረፉት ሁሉ የእኔንም
መንፈስ አሳርፈውልኛል። እንደ እነዚህ
ያሉትን ሰዎች በሚገባ እንደምትረዱአቸው
አልጠራጠርም።
19በዚህ በታናሹ እስያ የሚገኙ አብያተ
ክርስቲያን ሰላምታ ያቀርቡላችኋል። አቂ
ላና ጵርስቅላ፣ በቤታቸው ለጸሎት የሚሰበ
ሰቡ ምዕመናን ሁሉ የናፍቆት ሰላምታ ያቀ
ርቡላችኋል። 20እዚህ ያሉ ወንድሞች
ሁሉ ሰላምታቸውን እንዳቀርብላችሁ አደራ
ብለውኛል። በምትገናኙበትም ጊዜ በተቀ
ደሰ የወንድማማች ፍቅር እየተሳሳማችሁ
ሰላም ተባባሉ።
21እነዚህን የመጨረሻዎቹን ቃሎች
በገዛ እጄ የጻፍኩላችሁ እኔው ራሴ ጳው
ሎስ ነኝ። 22ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስን የማይ
ወድ የተረገመ ይሁን። ጌታችን ሆይ፣ ቶሎ
ና! 23የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ጸጋ ከእ
ናንተ ጋር ይሁን። 24የእኔም ፍቅር በጌታ
በኢየሱስ ክርስቶስ ከሁላችሁ ጋር ነው።

የናንተው
ጳውሎስ

## ሐዋርያው ጳውሎስ
# ለቆሮንቶስ ሰዎች የጻፈው ሁለተኛው መልእክት

### መግቢያ

ጸሐፊው ሐዋርያው ጳውሎስ ሲሆን፥የተጻፈበት ዘመን ደግሞ በ56 ዓ.ም. መሆኑ ይገመታል። መልእክቱ ያቀፋቸው አርዕስተ ጉዳዮች የተለያዩ ቢሆኑም፥መሠረተ አሳቡ የክርስቶስ ሐዋርያ የሆነውን የጳውሎስን ሐዋርያዊ ተልእኮ አጉልቶ ማሳየት ነው። አንዳንድ የሐሰት መምህራን ቆሮንቶስ በሚገኙ ማኅበረ ምዕመናን መካከል ሠርገው በመግባት፥ 'እውነተኞቹ መምህራን እኛ ነን እንጂ መቼ ጳውሎስ ነው?' በማለት በሐሰት ትምህርታቸው በክለው ምዕመናንን ከእውነተኛው ትምህርት ለማራቅ የተቻላቸውን ሁሉ አድርገዋል። ጳውሎስ በእግዚአብሔር የተመረጠ እውነተኛ ሐዋርያ መሆኑን ለቆሮንቶስ ሰዎች በዚህ መልእክቱ ያረጋግጥላቸዋል። የሐሰተኞቹ መምህራን ሙከራም በቆሮንቶስ ክርስቲያኖች ዘንድ ተቀባይነት እንዳይኖረው ጳውሎስ፥ ሐዋርያነትን የተሾመው በሰው ሳይሆን በራሱ በእግዚአብሔር መሆኑን በማያሻማ ሁኔታ ግልጥልጥ አድርጎ ያስረዳቸዋል።

---

## ምዕራፍ 1

1 በእግዚአብሔር ፈቃድ የኢየሱስ ክርስ
ቶስ ሐዋርያ ከሆነው ከጳውሎስና ከወንድም
ጢሞቴዎስ፥ በቆሮንቶስ ከተማና በመላው
አካይያ ለምትገኙ ክርስቲያኖች የተላከ።
2 የአባታችን የእግዚአብሔር፥የጌታችንም
የኢየሱስ ክርስቶስ ጸጋና ሰላም ከሁላችሁ
ጋር ይሁን።
3 የምሕረትና የመጽናናት ሁሉ ምንጭ
ለሆነው፥ ለጌታችን ለኢየሱስ ክርስቶስ አባ
ትና አምላክ፥ለእግዚአብሔር ምስጋና ይድ
ረሰው። 4 እግዚአብሔር በመከራችንና በፈተ
ናችን ጊዜ ሁሉ ያጽናናናል። ይህንንም
የሚያደርገው፥እኛም በበኩላችን በመከራና
በፈተና ላይ የሚገኙትን እንድናጽናናቸው
ነው። 5 ስለ ክርስቶስ ብዙ መከራ በምንቀበ
ልበት ጊዜ በዚያው መጠን ከእርሱ ታላቅ
መጽናናትን እናገኛለን። 6 እኛ መከራን
የምንቀበለው እናንተ መጽናናትና ደኅንነት
እንድታገኙ ነው፤እኛ ብንጽናናም መከራን
በትዕግሥት መቀበል የሚያስችላችሁን
መጽናናት እንድታገኙ ነው። 7 የእኛን
መከራ እንደተካፈላችሁ ሁሉ፥ የእኛንም
መጽናናት እንደምትካፈሉ እርግጠኞች ስለ
ሆንን ስለ እናንተ ያለን ተስፋ ጽኑ ነው።
8-9 በታናሽ እስያ የደረሰብን መከራ ምን
ያህል ከባድ እንደነበር እንድታውቁልን እን
ወዳለን። የደረሰብን መከራ እጅግ ጽኑ ከመ
ሆኑ የተነሣ በሕይወት ለመኖር ተስፋ አል
ነበረንም። ይህም በመሆኑ፥ የሞት ፍርድ
እንደ ተፈረደብን ያህል ተሰማን። ከመከራ
ሊያወጣን እንደሚችል በማመን ሙታንን
ለሚያስነሣው አምላክ ሕይወታችንን አደራ
ሰጠነው። 10 አሰቃቂ ከሆነው ሞትም አዳ
ነን። ወደ ፊትም እንደዚህ ካለው መከራ
እንደሚጠብቀንና እንደሚያድነን አንጠራጠ
ርም። 11 እናንተም እኛን በጸሎታችሁ ልት
ረዱን ይገባል። ስለ እኛ በምትጸልዩበትም
ጊዜ፥ እግዚአብሔር ጸሎታችሁን ሰምቶ
የሚያደርግልንን ድንቅ ሥራ በማየት ብዙ
ሰዎች እግዚአብሔርን ያመሰግኑታልና።
12 ከሌሎች ሰዎችና በተለይም ከእናንተ
ጋር የነበረን ግንኙነት ቅድስናና ቅንነትን
የተሞላበት እንደነበር አፋችንን ሞልተን
እንናገራለን። ይህም በእኛ ጥበብ ሳይሆን፥
በእግዚአብሔር እርዳታ የተገኘ በመሆኑ
እንመካበታለን። 13 በደብዳቤዎቻችን ውስጥ
ግልጽ ያልሆነና የተድበሰበሰ ምንም ነገር
የለም። 14 አሁን ይህን ያህል ባታውቁኝም፥
ወደፊት በሚገባ እንደምታውቁኝ ተስፋ
አደርጋለሁ። ስለዚህ ጌታ ተመልሶ በሚመ
ጣበት በዚያች ዕለት በእናንተ የምመካውን
ያህል እናንተም በእኔ እንደምትመኩብኝ
አልጠራጠርም። 15-16 እኔም በዚህ ጉዳይ
እርግጠኛ በመሆኔና የምታገኙትም በረከት
እጥፍ ድርብ እንዲሆን በማለት ወደ መቄ
ዶንያ ስሄድ ልጐበኛችሁ አቅጄ ነበር።
ከዚያም ወደ ይሁዳ በማደርገው ጉዞዬ
በሚገባ ተንከባክባችሁ ትሸኙኛላችሁ

የሚል ተስፋ ነበረኝ።
17 «ታዲያ ለምን ቀረህ? ለምንስ አሳብ
ህን ለወጥህ?» ትሉኝ ይሆናል። መጀመሪያ
ውኑ ስለዚሁ ጉዳይ አላሰብኩበትም ነበር
ማለት ነው? ወይስ እንደ ዓለማውያን ዛሬ
አንዱን፥ ነገ ደግሞ ሌላውን በመናገር፥
ቃሌን አላከብርም ማለት ነው? 18 ፈጽሞ!
«ይሆናል» ካልኩ ይሆናል። «አይሆንም»
ካልኩ አይሆንም። ቃሌ ይህችው ናት። ለዚ
ሁም ምስክሬ እግዚአብሔር ነው።
19 ጢሞቴዎስ፥ ሲላስና እኔም ራሴ የሰበ
ክንላችሁ የአብ ልጅ ኢየሱስ ክርስቶስ ቃሉ
አንዲት ናት። «ነው» ካለ ነው፤ «አይደ
ለም» ካለም አይደለም ነው። ቃሉ አይታ
ጠፍም። 20 ከእግዚአብሔር የተቀበልነው
ተስፋ ሁሉ የሚፈጸመው በእርሱ ነው።
እኛም በቃሉ የሚጸና መሆኑን ስለምናውቅ
ለስሙ ክብር እየሰጠን ስለ ታማኝነቱ ለሰ
ዎች ሁሉ መስክረንለታል። 21 እናንተም
እኛም በክርስቲያንነታችን እንድንጸናና ወን
ጌሉን በማስተማር የሐዋርያነት ተልእኮዋች
ንን እንድናከናውን የመረጠን እግዚአብሔር
ራሱ ነው። 22 የእርሱ ለመሆናችን ማረጋ
ገጫ የሚሆን ማኅተሙን ያተመብንና ለሚ
ያደርግልንም በጎ ነገር ሁሉ የመንፈስ ቅዱ
ስን ዋስትና የሰጠን እርሱ ነው።
23 ወደ እናንተ ያልመጣሁበት ምክን
ያት እንዳላሳዝናችሁ ፈርቼላችሁ ነው።
ለዚሁም እግዚአብሔር ምስክሬ ነው።
24 ብመጣም እንኳ በእምነታችሁ ጽኑ ስለ
ሆናችሁ፥ 'እንዲህ አድርጉ' በማለት እናን
ተን ለማዘዝ አይደለም። ምን ጊዜም ቢሆን
ደስ እንዲላችሁ እንጂ እንድታዝኑ ምኞቴ
አይደለምና።

## ምዕራፍ 2

1 ላሳዝናችሁ ስለማልፈልግ ወደ እናንተ
ተመልሼ ላለመምጣት ወሰንኩ። 2 በበኩሌ
እናንተን በማሳዘን የማገኘው ጥቅም የለም።
ምክንያቱም ከእናንተ ሌላ እኔን የሚያስደ
ስት ማንም የለምና። 3 ባለፈው ደብዳቤዬ
ወደ እናንተ ከመምጣቴ በፊት አንዳንድ
የሚቃኑ ነገሮች መኖራቸውን ገልጬ የጻፍ
ኩላችሁም ስለዚሁ ነው። የደስታዬ ምክን
ያት በሆናችሁት በእናንተ ላይ ማዘንና
መቀየምም አይገባኝም። እኔን ደስ ሲለኝ
እናንተም ደስ እንደሚላችሁ ተረድቻለሁ።
4 ያንን ደብዳቤ የጻፍኩት ልቤ በኀዘን
እየተጨነቀና እንባዬም እየፈሰሰ ነው። ዓላ
ማዬም ልጐዳችሁ ሳይሆን በጣም እንደማ
ፈቅራችሁ እንድታውቁ ነው።
5 ለዚህ ሁሉ ኀዘን ምክንያት የሆነው
ሰው ያሳዘነው እኔን ብቻ ሳይሆን እናንተ
ንም ጭምር ነው። ይህንን ስል ነገር ለማጋ
ነን አይደለም። 6 ለዚህ ሰው እስካሁን በኅብ
ረት የሰጣችሁት ቅጣት ይበቃዋል። 7 ደግ
ሞም ከልክ በላይ አዝኖ ተስፋ እንዳይቆርጥ
ይቅር ልትሉትና ልታጽናኑት ይገባል።
8 የምትወዱትና የምታስቡለት መሆኑን እን
ዲረዳው አድርጉ።
9 እንደዚያ አድርጌ የጻፍኩላችሁም፥ የም
ትታዘዙኝ ምን ያህል መሆኑን ለማወቅ ስለ
ፈለግሁ ነው። 10 ይህን ሰው እናንተ ይቅር
ካላችሁት እኔም ይቅር እለዋለሁ። በበኩሌ
ይቅር የምለው በደል ካለም፥ ለእናንተ
ስልና ጌታ ባዘዘው መሠረት ይቅር ብያ
ለሁ። 11 ይቅር የምንልበት ሌላው ምክን
ያት ደግሞ ሰይጣን ተንኰለኛ ስለሆነ፥
በዚህ ጉዳይ መግቢያ ቀዳዳ አግኝቶ በደለኛ
ውን ወንድም ተስፋ ወደ መቁረጥ እንዳያደ
ርሰው ነው።
12 የክርስቶስን ወንጌል ለመስበክ ወደ
ጢሮአዳ በመጣሁ ጊዜ የአገልግሎት በር
በሰፊው ተከፍቶልኝ ነበር። 13 ይሁን እንጂ
ወንድሜ ቲቶን አለማግኘቴ የመንፈስ ዕረ
ፍት ስለነሣኝ፥ ምዕመናንን ተሰናብቼ ወደ
መቄዶንያ አመራሁ።
14 ነገር ግን በክርስቶስ ሁልጊዜ ድል
እያደረግን መዓዛው እንደ ሽቶ የሆነውን
የወንጌል ትምህርት በየሥፍራው እንድናዳ
ርስ ለሚያደርግ አምላክ ምስጋና ይድረ
ሰው። 15 ለሚድኑትም ሆነ ለሚጠፉት ክር
ስቶስ መልካም መዓዛ ያለው ሽታ አድርጎ
ለእግዚአብሔር አቅርቦናል። 16 ለሚጠፉት
አስፈሪ የሞትና የጥፋት ሽታ እንመስላቸዋ
ለን። ክርስቶስን ለተቀበሉት ግን ሕይወትን
የሚሰጥ ሽታ ነን። ታዲያ እንዲህ ላለው
አገልግሎት ብቁ ሆኖ የሚገኝ ማን ነው?
17 እኛ እኮ የእግዚአብሔርን ቃል ከውሸት
ጋር ቀላቅለው በማቅረብ ኑሮአቸውን ለማደ
ላደልና ትርፍ ለማግኘት እንደሚፈልጉ
ሰዎች አይደለንም። ከእግዚአብሔር የተላ
ክን የክርስቶስ አገልጋዮች ስለሆንን በፊቱ
በቅንነት እንናገራለን።

## ምዕራፍ 3

1 ይህን በማለታችን ደግሞ እነዚያ የሐ
ሰት መምህሮቻችሁ እንደሚያደርጉት፥ እኛ
ራሳችንን ስለ ራሳችን የምስጋና ቃል የምንደ
ረድር፥ እንዲሁም ስለ እኛ የተጻፈ የምስጋና

ደብዳቤ ይዘን በየደረስንበት የምናሳይ አይደ
ለንም። እናንተም ብትሆኑ የእኛን ማንነት
ለማወቅ ከሌላ የተጻፈ የምስጋና ደብዳቤ
የሚያስፈልጋችሁ አይመስለኝም። እኛም
እናንተን የምስጋና ደብዳቤ እንድትጽፉልን
የምንፈልግ አይደለንም። 2 ምክንያቱም
ማንም ሰው ሊያነበው የሚችል በልባችን
ላይ የተጻፈ መልእክታችን እናንተ ናችሁ።
3 እናንተ በቀለም ሳይሆን በሕያው እግዚአ
ብሔር መንፈስ፥በድንጋይ ጽላት ላይ ሳይ
ሆን በልብ ጽላት ላይ የተቀረጻችሁና
ማንም ሰው በግልጽ የሚያነባችሁ የክርስ
ቶስ ግልጽ ደብዳቤዎች ናችሁ።
4 ይህን መልካም ነገር ስለ ራሳችን የምን
ናገረው በክርስቶስ ኢየሱስ፥በእግዚአብሔር
ላይ ያለን እምነት ከፍተኛ ስለሆነ ነው።
5 በራሳችን ጥረት ዘላቂነት ያለው ሥራ ለማ
ከናወን ብቁዎች ነን አንልም። ለዚህ ሁሉ
ብቁ ያደረገን እግዚአብሔር ብቻ ነው።
6 የኦሪትን ሕግ ሳይሆን የመንፈስ ቅዱስ
ሕግ የሆነውን አዲሱን ቃል ኪዳን እንድናገ
ለግል አብቅቶናል። የኦሪት ሕግ መጨረ
ሻው ሞት ሲሆን፥የመንፈስ ቅዱስ ሕግ ግን
ሕይወትን የሚያድል ነው። ይህንንም የም
ሥራች ቃል ለሰዎች ሁሉ እንድናውጅ የረ
ዳን እግዚአብሔር ራሱ ነው።
7 የኦሪት ሕግ የተጻፈው በድንጋይ ጽላት
ላይ ነው። ይህ ሕግ በተሰጠበት ጊዜ የእግ
ዚአብሔር ክብር በይፋ ተገልጦአል። የክ
ብሩ ነጸብራቅ እየከሰመ የሚሄድ ቢሆንም
እንኳን፥ ሙሴ ሕጉን ተቀብሎ ሲወርድ
እሥራኤላውያን በፊቱ ላይ የተሣለውን ብር
ሃን ለማየት እስኪሳናቸው ድረስ አንጸባርቆ
ባቸዋል። ያ ሞትን የሚያስከትለው የሕግ
አገልግሎት በተሰጠበት ጊዜ ይህን የሚያ
ህል የእግዚአብሔር ክብር የተገለጠ ከሆነ፥
8 ሕይወት የሚሰጠው የመንፈስ አገልግሎት
ደግሞ፥ክብሩ ተወዳዳሪ የለውም። 9 በሰዎች
ላይ ፍርድ ያስከተለው ያ ሥርዓት ይህን
ያህል ክብር ያለው ከሆነስ፥ሰዎችን የሚያጸ
ድቀው አዲሱ ሥርዓት የቱን ያህል ይበ
ልጥ? 10 ስለዚህ የአሁኑ የመንፈስ አገልግ
ሎት ከበፊቱ የሕግ አገልግሎት ጋር ሲወዳ
ደር፥ በክብር የበፊቱ ከአሁኑ እጅግ በጣም
ያነሰ ነው። 11 ያ የተሻረው ሕግ ያን ያህል
ክብር ከነበረው፥ የሕይወት መገኛና ለዘላ
ለም የሚጸናው አዲሱ ቃል ኪዳን ክብር
እንደሚበልጥ ጥርጥር የለውም።
12 ያለን ተስፋ የሚያስመካ በመሆኑ
በድፍረት እንናገራለን። 13 እኛ፥አንጸባራቂ
ነቱ እየከሰመ የሚሄደውን ፊቱን ሰዎች እን
ዳያዩት እንደ ሸፈነው እንደ ሙሴ አይደለ
ንም።
14 እርግጥ ነው፥ እነዚያ የተሸፈነውን
የሙሴን ፊት ያዩ ሰዎች እስከ ዛሬ ድረስ
አእምሮአቸው ደንዝዞ እውነትን ሊያዩ አል
ቻሉም። ብሉይ ኪዳን በተነበበ ቁጥር ያ
ፊታቸውን የከለለው ሽፋን እስከ ዛሬ ድረስ
እውነትን እንዳይረዱ ዓይናቸውን ጋርዶት
ይኖራል። እንግዲህ ያን ሽፋን የሚያስወግ
ደው ማን ይመስላችኋል? ክርስቶስ ብቻ
ነው። 15 ዛሬም እንኳ ለሙሴ የተሰጠውን
ሕግ በሚያነቡበት ጊዜ፥ሽፋኑ አእምሮአቸ
ውን ስለሚጋርደው ደኅንነት የሚገኘው
የኦሪትን ሕግ በመጠበቅ ይመስላቸዋል።
16 ነገር ግን አንድ ሰው ወደ ጌታ በሚ
መለስበት ጊዜ ፊቱን የጋረደው ሽፋን ይገለ
ጥለታል። 17 ጌታ ሕይወትን የሚሰጥ መን
ፈስ ነው። የጌታ መንፈስ ባለበት ሁሉ ነፃ
ነት አለ። 18 ስለዚህም እኛ ክርስቲያኖች
ፊታችንን ምንም ነገር አይሸፍነውም። ከዚ
ህም የተነሣ የጌታን ክብር እንደ መስተዋት
ማንጸባረቅ እንችላለን። የጌታ መንፈስ በእኛ
ውስጥ ስለሚኖር ክርስቶስን ለመምሰል፥ከክ
ብር ወደ ክብር እንለወጣለን።

## ምዕራፍ 4

1 የወንጌሉን ቃል ለሰዎች እናስተምራ
ቸው ዘንድ በዚህ ድንቅ በሆነው አገልግ
ሎት እንድንሰማራ ያደረገን ራሱ እግዚአብ
ሔር ስለሆነ፥ ከዚህ ጥሪ በምንም ዓይነት
መንገድ ወደ ኋላ አናፈገፍግም። 2 ሰዎችን
በማታለል እንዲያምኑ አናደርጋቸውም፤ማን
ንም ለማታለል ፍላጐት የለንምና። በቅዱ
ሳት መጻሕፍት ውስጥ የሌለውን፥እንዳለ
አድርገን በሐሰት አስመስለን የምናቀርብም
አይደለንም። እንደዚህ ያለው አሳፋሪ ድር
ጊት ፈጽሞ አይቃጣንም። በእግዚአብሔ
ርም ፊት አንዋሽም። እውነቱን ብቻ በግ
ልጽ የምንናገር መሆናችንንም የሚያውቁ
ሰዎች ሁሉ ይመሰክሩልናል።
3 የምንሰብከው ወንጌል የተሰወረበት
ሰው ካለ፥እርሱ ወደ ዘላለም ሞት የሚያ
መራ ሰው ነው። 4 የዚህ ክፉ ዓለም ገዢ
የሆነው ዲያብሎስ የወንጌሉን ብርሃን እንዳ
ያዩ፥የእግዚአብሔር አምሳል ስለሆነው ስለ
ክርስቶስ ክብር የምንሰብከውን ዕፁብ ድንቅ
የሆነውን የምሥራች ቃል እንዳያስተውሉ
ልቦናቸውን ደፍኖባቸዋል። 5 እየዞርን የም
ናስተምረው ኢየሱስ ክርስቶስ ጌታ መሆኑን

እንጂ ስለ ራሳችን አይደለም። ስለ ራሳችን
የምንለው ነገር ቢኖር፥ጌታ ኢየሱስ ካደረገ
ልን በጎ ነገር የተነሣ ራሳችንን ለእናንተ
አገልጋዮች አድርገን ማቅረባችንን ማሳወቅ
ነው። 6 «ብርሃን ከጨለማ ውስጥ ይታይ»
ብሎ የተናገረው አምላክ፥በክርስቶስ መልክ
በፈሰሰው ብርሃን፥ የእግዚአብሔር የክብሩ
እውቀት እንዲገለጥልን፥ ልባችንን በብርሃኑ
አጥለቅልቆታል።
7 ነገር ግን ይህን ክቡር ነገር፥ ማለት
በውስጣችን የሚበራውን ብርሃንና ኃይል
እንደ ሸክላ ዕቃ ተሰባሪ በሆነው ደካማ
ሰውነታችን ውስጥ ይዘነዋል። ይህም ከኛ
ሳይሆን ከእግዚአብሔር የተሰጠ ነው።
8 በዚህም በዚያም መከራ ይደርስብናል።
ነገር ግን ተንኮታኩተን አንወድቅም። ለችግ
ራችን መፍትሔ ለማግኘት ውሉ የሚጠፋ
ብን ጊዜ አለ። ይህ ሆኖ ብለን ግን ተስፋ
አንቆርጥም። 9 ተቃዋሚዎቻችን መሸሻ
መድረሻ አሳጥተው እንደ አውሬ ያድኑ
ናል። እግዚአብሔር ግን አምባ መጠጊያ
ሆኖ ይጠብቀናል። አሽቀንጥረው ይጥሉ
ናል፤ነገር ግን ከወደቅንበት ተነሥተን ጉዞ
አችንን እንቀጥላለን። 10 በኢየሱስ ላይ የደረ
ሰው ሞት በእኛም ሕይወት ላይ ዘወትር
እንዳንዣበበ ቢሆንም፥ በውስጣችን የሚኖ
ረው ሕያው ክርስቶስ ሕይወቱን በሰውነታ
ችን እንዲገለጥ ያደርጋል።
11 የኢየሱስ ሕይወት ሟች በሆነው ሥጋ
ችን እንዲገለጥ፥ ስለ ኢየሱስ ስንል ዘወትር
በሞት አፋፍ ላይ እንገኛለን። 12 ስለዚህ
እኛ ወንጌሉን በማስተማራችን በሞት
አፋፍ ላይ ስንገኝ፥ እናንተ ግን የዘላለምን
ሕይወት ታገኙበታላችሁ።
13 በቅዱሳት መጻሕፍት፥ «አመንኩ ስለ
ዚህም ተናገርኩ» ተብሎ እንደተጻፈ፥ከማና
ቸውም ክፉ ነገር እንደሚጠብቀን በፈጣሪ
ያችን በመታመን፥ስለ እምነታችን ሳንፈራ
እንመሰክራለን። 14 ጌታ ኢየሱስን ከሞት
ያስነሣው እግዚአብሔር፥እኛንም ከኢየሱስ
ጋር ከሞት እንደሚያስነሣንና ከእናንተ ጋር
በፊቱ እንደሚያቀርበን እናውቃለን።
15 ይህን ያህል መከራ መቀበላችን ስለ እናን
ተው ጥቅም መሆኑን እንዳትዘነጉ የእግዚአ
ብሔር ጸጋ እየተትረፈረፈ ለብዙ ሰዎች
በደረሰ መጠን፥ ለእግዚአብሔር የሚቀርበ
ውም ክብርና ምስጋና በዚያው መጠን የበዛ
ይሆናል።
16 ከዚህ የተነሣም ተስፋ አንቆርጥም።
ስለዚህ የሚታየው ውጫዊው ሰውነታችን
ቢጐሳቆልም፥ውስጣዊው ሰውነታችን ዕለት
ዕለት በጌታ ይታደሳል። 17 የምንቀበለው
መከራ የሚደርስብንም ችግር በጣም ቀላ
ልና ጊዜያዊ ሲሆን፥ዘላለማዊ የሆነውን የእ
ግዚአብሔርን በረከት እንደሚያበዛልን እና
ምናለን። 18 ስለዚህም ዙሪያችንን የከበበ
ውን ይህን የሚታየውን መከራና ችግር ሳን
መለከት፥ ወደ ፊት በሰማይ በሚጠብቀን፥
አሁን ግን በማይታየው ተድላና ደስታ ላይ
እናተኩራለን። ይህ የሚታየው መከራችን
በቶሎ ያልፋል፤ አሁን የማይታየው፥ ነገር
ግን በሰማይ የሚጠብቀን ደስታ ለዘላለም
የሚቆይ ነው።

## ምዕራፍ 5

1 ይህ እንደ ድንኳን ጊዜያዊ የሆነው
ሥጋችን ሲፈርስና ሲበሰብስ፥ በሰው እጅ
ሳይሆን በእግዚአብሔር እጅ የተሠራ ዘላለ
ማዊ መኖሪያ በሰማይ እንዳለን እናውቃ
ለን። 2 ያች ዕለት ከመቼው ደርሳ፥ያን አዲ
ሱን ሰማያዊ አካል ለብሰነው በማለት በዚህ
ምድራዊ ሰውነታችን ውስጥ ሆነን ዛሬ እን
ጨነቃለን። 3 በዚያን ጊዜም ሰማያዊውን
አካል ስለምንለብስ ራቁታችንን ሆነን አንገ
ኝም። 4 በዚህ ምድራዊ በሆነው አካላችን
መኖር እየከበደን እንቃትታለን። ሆኖም፥
ሞተን ፈርሰን በሰብሰን እንቀራለን ብለን
አናስብም። እኛ የምንናፍቀው ይህ ሟች፥
ፈራሽና በሰባሽ የሆነው አካላችን፥የማይሞ
ተውን የማይፈርሰውንና የማይበሰብሰውን
ዘላለማዊ አካል ከመቼ መቼ ለብሶልን በማ
ለት ነው። 5 ለዚህም ዓላማ ያዘጋጀን እግዚ
አብሔር ሲሆን፥ ይህ ሁሉ እንደሚፈጸም
መንፈስ ቅዱስን ማረጋገጫ አድርጎ ሰጥቶ
ናል።
6 ስለዚህ ምን ጊዜም የምንኖረው በተስ
ፋና በእምነት ነው። በዚህ ሥጋዊ አካል
ተወስነን የምንኖርበትን ጊዜ፥በጌታ ከምናገ
ኘው ከዘላለማዊው ቤታችን ተለይተን እንደ
ምንኖር አድርገን እንቆጥረዋለን። 7 ሆኖም
ሕይወታችን የሚመራው በእምነት እንጂ
በሚታዩ ነገሮች አይደለም። 8 ከዚህ የተነ
ሣም ከጌታ ጋር ለመኖር ስለምንናፍቅ
ሞትን አንፈራም። 9 በዚህ ዓለም በሕይወት
ብንኖርም ሆነ፥ከእርሱ ጋር ለመኖር ከዚህ
ዓለም በሞት ብንለይ፥ዓላማችን ጌታን ማስ
ደሰት ብቻ ነው። 10 እያንዳንዳችን በዚች
ምድር በኖርንበት ዘመን ላደረግነው
ክፉም ሆነ በጎ ሥራ የሚገባንን ዋጋ
ለመቀበል በክርስቶስ የፍርድ ወንበር ፊት

እንቀርባለን።
11 እግዚአብሔርን መፍራት ምን ማለት
እንደሆነ ስለምናውቅ፥ሌሎችም ሰዎች ወደ
እርሱ እንዲመለሱ እንመክራቸዋለን። እግዚ
አብሔር የልባችንን አሳብ ያውቀዋል። እና
ንተም እንደምታውቁን ተስፋ አደርጋለሁ።
12 ይህን የምንናገረው ራሳችንን በእናንተ
ፊት ለማዋደድ አይደለም። ነገር ግን ከልብ
በሆነ ነገር ሳይሆን ከአንገት በላይ ለሚመ
ኩት ሰዎች መልስ መስጠት እንድትችሉና
በእኛም እንድትመኩ በማለት ነው። 13 እብ
ዶች ብንሆን ለእግዚአብሔር ስንል ነው።
ባለ አእምሮዎች ብንሆን ለእናንተው ጥቅም
መሆኑን እንድታውቁልን እንወዳለን።
14 ምንም ነገር ብናደርግ፥የራሳችንን ጥቅም
ፈልገን ሳይሆን የክርስቶስ ፍቅር ልባችንን
ስለሚገዛው ብቻ ነው። ክርስቶስ ለሰዎች
ሁሉ ሲል መሞቱን ካመንን፥እኛም የሞቱ
ተካፋዮች መሆናችንን ማመን ይኖርብናል።
15 ክርስቶስ ስለ ሁላችን ሞቷል። ይህንንም
ማድረጉ ፥ በሕይወት የሚኖሩ ሁሉ ለራሳ
ቸው ደስታ ብቻ ሳይሆን ለእነርሱ ሲል
መሥዋዕት ሆኖ ለሞተውና ከሞት ለተነ
ሣው ለእርሱ እንዲኖሩ ለማድረግ ነው።
16 ስለዚህ ከእንግዲህ ክርስቲያኖችን በዓለም
መለኪያ አንለካቸውም። እኔ ከዚህ በፊት
ክርስቶስን እንደ ማንኛውም ተራ ሰው አድ
ርጌ እገምተው ነበር። ዛሬ ግን አላደርገ
ውም። 17 ማንም ሰው በክርስቶስ ሲያምን
አዲስ ፍጥረት ይሆናል። አሮጌው ሕይወት
አልፎ ሁሉም ነገር ታድሷልና።
18 ይህም ሁሉ የሆነው ጠላቶቹ የነበርን
ውን እኛን፥በክርስቶስ ወዳጆቹ ባደረገን በእ
ግዚአብሔር ነው። ሌሎችም ሰዎች እንደ
እኛ ከእግዚአብሔር ጋር እንዲታረቁና ወዳ
ጆቹ እንዲሆኑ ፥ የማስታረቅን አገልግሎት
ለእኛ ሰጥቷል። 19 ይህንን የማስታረቅ አገል
ግሎት አደራ ስለተቀበልንም፥እግዚአብሔር
በክርስቶስ፥ሰዎችን ሁሉ ወዳጆቹ እንደሚያ
ደርጋቸውና በደላቸውን እንደማይቆጥርባ
ቸው እንሰብካለን። 20 እኛ የክርስቶስ አምባ
ሳደሮች ነን። ስለዚህ እግዚአብሔር በእኛ
አማካይነት ያናግራችኋል። ራሱ ክርስቶስ
ከእግዚአብሔር ጋር እንድትታረቁ እንደሚ
ለምናችሁ፥እኛም ከእግዚአብሔር ጋር እን
ድትታረቁልን እንለምናችኋለን። 21 የጽድቁ
ተካፋዮች እንድንሆን፥እግዚአብሔር ራሱ፥
አንዳችም ኃጢአት ያልተገኘበትን ክርስቶ
ስን፥የእኛን ኃጢአት እንዲሸከምና እንዲሞ
ትልን አደረገው።

## ምዕራፍ 6

1 እንደ እግዚአብሔር የሥራ ባልደረቦች
የተቀበላችሁትን ጸጋ በከንቱ እንዳታስቀሩት
እንለምናችኋለን። 2 እግዚአብሔር፥ «ጩኸ
ትህ ወደ እኔ ስለ ደረሰ በወቅቱ ሰማሁህ፤
ደኅንነትም በሚያስፈልግህ ቀን ረዳሁህ»
ሲል ተናግሮአል። ስለዚህ በአሁኑ ጊዜ እግ
ዚአብሔር ጩኸታችሁን ይሰማል። በዛሬው
ዕለት ሊያድናችሁም ዝግጁ ነው።
3 ሰዎች አገልግሎታችንን እንዳይነቅፉ
ብን፥ማንንም እንዳናሰናክል እንጠነቀቃለን።
4 በምናደርገውም ነገር ሁሉ የእግዚአብ
ሔር አገልጋዮች መሆናችንን እናስመሰክራ
ለን። ስለዚህ ማናቸውንም ዓይነት መከራ፥
ችግርና ጭንቀት ሁሉ በትዕግሥት እንሸከ
ማለን። 5 ተደብድበናል፤ወህኒ ቤት ተንገላተ
ናል። ሕዝብ ተገልብጦ ወጥቶ ሁከትና
ረብሻ አንሥቶብናል፤ከሥራ ብዛት የተነሣ
እንቅልፍ ባይናችን ሳይዞር ሌቱን አንግተ
ናል። የምንመገብበትን ጊዜም እስከ መር
ሳት ደርሰናል። 6 ነገር ግን በመንፈሳዊ ንጽ
ሕና፥በእውቀት፥በትዕግሥት፥በቸርነት፥በመ
ንፈስ ቅዱስ የተሞላን በመሆናችን ግብዝ
ነት በሌለው ፍቅር ፥ 7 የእግዚአብሔርን
እውነት በመናገራችን ምክንያት፥የእግዚአ
ብሔር ኃይል በምናደርገው ሁሉ ረድቶ
ናል። ለመከላከልና ለማጥቃት የሚረዳንን
የእግዚአብሔርን የጽድቅ መሣሪያ በማግኘ
ታችንም የእግዚአብሔር አገልጋዮች መሆና
ችንን አስመስክረናል።
8 መከበርንም መዋረድንም ለምደነዋል።
መመስገንም መሰደብም ለእኛ አዲስ ነገር
አይደለም። እውነትን እየተናገርን ውሸተ
ኞች ተብለናልና።
9 ለዚህ ዓለም ሰዎች ባይተዋር ብንሆ
ንም በእግዚአብሔር ዘንድ የታወቅን ነን።
ሞት በየዕለቱ ቢያንዣብብብንም እንደምታ
ዩት በሕይወት አለን። ብዙ ጉዳት ቢደርስ
ብንም ሕይወታችን አላለፈም። 10 ልባችን
ቢቆስልም ሁልጊዜ ደስ እንዳለን ነው።
ድሆች መስለን ብንታይም ብዙዎቹን በመን
ፈሳዊ ነገር አበልጽገናቸዋል። ምንም የሌ
ለን ሆነን ሳለ፥ሁሉም ነገር የእኛ ነው።
11 በቆሮንቶስ የምትኖሩ ወዳጆቻችን
ሆይ ፥ ልቤ ለእናንተ ወለል ብሎ የተከፈተ
ስለሆነ ትክክለኛውንና እውነተኛውን ነገር
በግልጽ ነግሬአችኋለሁ። 12 በእናንተና በእኔ
መካከል ላለው ፍቅር መቀዝቀዝ ምክንያት
የሆንኩት እኔ ሳልሆን፥የፍቅራችሁ ውሱን

መሆን ነው። 13 አሁን የማናግራችሁ ልክ
እንደ ልጆቼ አድርጌ ነው። እስቲ እኛ ላሳ
የናችሁ ፍቅር እናንተም ልባችሁን ከፍታ
ችሁ አጸፋውን መልሱልንና ደስ ይበለን።
14 ጌታን ከማይወዱና ከማያምኑ ሰዎች
ጋር ለክርስቲያን የማያመች ምንም ዓይነት
ግንኙነት አይኑራችሁ። የእግዚአብሔር
ሰዎች ከኃጢአተኞች ጋር አንድነት ሊኖራ
ቸው እንዴት ይችላል? ብርሃንና ጨለማስ
እንዴት አብረው ሊኖሩ ይችላሉ? 15 ክርስ
ቶስና ሰይጣንስ እንዴት ሊስማሙ ይች
ላሉ? የሚያምንስ ከማያምን ጋር ምን አን
ድነት አለው? 16 የእግዚአብሔር ቤተ መቅ
ደስ ከጣዖት ጋር ምን ግንኙነት አለው?
እኛ የሕያው እግዚአብሔር ቤተ መቅደሱ
ነን። ስለዚህም እግዚአብሔር፥ «በእነርሱ
ውስጥ አድራለሁ። በመካከላቸውም እመላለ
ሳለሁ። አምላካቸው እሆናለሁ፤ እነርሱም
ሕዝቤ ይሆናሉ» ብሏል። 17 ሁሉን የሚ
ችል ጌታም፥ «ከመካከላቸው ውጡ። ለእ
ኔም የተለያችሁ ሁኑ። እርኩስ ሥራቸው
ንም ተጸየፉ፤እኔም እቀበላችኋለሁ። 18 አባ
ታችሁ እሆናለሁ፤ እናንተም ወንዶችና
ሴቶች ልጆቼ ትሆናላችሁ» ብሎ ተናግሮ
አል።

## ምዕራፍ 7

1 ስለዚህ ወዳጆቼ ሆይ፥ ይህን ያህል
ተስፋ ከተሰጠን ነፍሳችንንና ሥጋችንን
ከሚያረክስ ከማናቸውም ነገር ራሳችንን
ጠብቀን እግዚአብሔርን በመፍራትና በቅድ
ስና እንኑር። 2 እስቲ በልባችሁ ውስጥ ስፈ
ቦታ ስጡን። ለመሆኑ ከእናንተ መካከል የበ
ደልነው ማንን ነው? የማንንስ ሕይወት
ጐዳን? ማንን አታለልን? ወይስ ከማን
ጥቅም ፈለግን? 3 ይህን የምለው በማንኛች
ሁም ላይ ለመፍረድ አይደለም። ከዚህ
በፊት እንደነገርኳችሁ፥ በጣም እወዳችኋ
ለሁ። ስለዚህ በሕይወትም ሆነ በሞት ከእና
ንተ አልለይም። 4 በእናንተ ላይ ከፍ ያለ
እምነትና ትምክህት ስላለኝ፥በሚደርስብኝ
መከራ ሁሉ እጽናናለሁ፤ለደስታዬም ወሰን
የለውም።
5 መቄዶንያ እንደ ደረስን ለሥጋችን
ምንም ዕረፍት አልነበረንም። በየደረስንበት
ሥፍራ ሁሉ መከራና ችግር አጋጥሞናል።
ከውጭ ጸብ፥ከውስጥ ደግሞ ሥጋት አልተለ
የንም ነበር። 6 ነገር ግን ተስፋ የቆረጡትን
የሚያጽናና አምላክ፥ቲቶን ወደ እኛ እንዲ
መጣ ስላደረገው በዚህ ለመጽናናት በቃን።
7 ይልቁንም እንዴት እንደረዳችሁትና እንዳ
ጽናናችሁት፥እኔንም እንደ ናፈቃችሁና በደ
ረሰብኝ ነገር ሁሉ እንዳዘናችሁ፥ስለ ታማኝ
ነታችሁና ስለ ፍቅራችሁ ሁሉ ገልጾ ስለ
ነገረኝ እጅግ በጣም ደስ አለኝ።
8 በጻፍኩላችሁ መልእክት ማዘናችሁ
ይሰማኛል። ሆኖም፥ «ለምን እንደዚህ ያለ
ውን ነገር ጻፍኩላቸው» ብዬ አልተጸጸት
ኩም። እርግጥ ነው መልእክቴ ያሳዘናችሁ
መሆኑን በማሰብ ለጊዜው እኔም በነገሩ
ቅር ሳልሰኝ አልቀረሁም። 9 ሆኖም ኀዘና
ችሁ ንስሐ እንድትገቡ የረዳችሁ መሆኑን
በመስማቴ ደስ ብሎኛል። እንደ እግዚአብ
ሔር ፈቃድ ስላዘናችሁ፥በእኛ ምንም አል
ተጐዳችሁም። 10 በእግዚአብሔር ፈቃድ
የመጣ ኀዘን ለደኅንነት ከሚያበቃ ንስሐ
ያደርሳልና። ስለዚህ ይህ ለምን ሆነ ማለ
ትና መጸጸት አንችልም። የዚህ ዓለም
ኀዘን ወደ ንስሐ ሳይሆን ወደ ሞት የሚ
ያደርስ ነው።
11 ለንስሐ በማዘናችሁ ምክንያት እግዚአ
ብሔር ያደረገላችሁን በጎ ነገር እስቲ አስ
ቡት። የሠራችሁትን በደል በጥሞና እንድ
ታሰላስሉትና ከኃጢአት ንጹሐን እንድት
ሆኑ ረድቶአችኋል። የኃጢአት ምሬት እን
ዲያስቆጣችሁ፥ ከበደል እንድትርቁ፥ ኃጢ
አት ማድረግን እንድትፈሩ፥ ለእኔ ናፍቆት
እንዲኖራችሁ፥ መንፈሳዊ ቅንዓት እንዲያድ
ርባችሁ፥በእውነት እንድትፈርዱ፥ጥፋተኛ
ውን በመቅጣት ንጹሐን መሆናችሁን እን
ድታስመሰክሩ አድርጎችኋል።
12 ስለዚህ ያንን ደብዳቤ የጻፍኩበት
ዋናው ምክንያት ስለ በደለኛውና ስለተበደ
ለው ሰው በማሰብ ብቻ አልነበረም። ነገር
ግን ለእኛ የቱን ያህል እንደምትጨነቁ በእ
ግዚአብሔር ፊት ራሳችሁን እንድታዩ በማ
ለትም ጭምር ነበር።
13 በዚህ ሁሉ እጅግ ተጽናንተናል።
መጽናናት ብቻ ሳይሆን፥የቲቶን አእምሮ
በማሳረፍ ደስ ስላሰኛችሁት እኛም የበለጠ
ደስ ብሎናል። 14 ስለ እናንተም ለቲቶ የነገ
ርኩት በሙሉ ልብ ነበር። እናንተም አላሳ
ፈራችሁኝም። ከዚህ ቀደም ለእናንተ የነገር
ኳችሁ ቃል እውነት እንደነበር ሁሉ፥አሁን
ደግሞ ስለ እናንተ ለቲቶ ከሙሉ ልቤ የተ
ናገርኩት፥ እውነት መሆኑ ተረጋግጧል።
15 ስለዚህ በአክብሮት እንዴት እንደተቀበላ
ችሁትና ፈቃዱን ሁሉ እንዴት እንደፈጸማ
ችሁለት እያስታወሰ፥ለእናንተ ያለው ፍቅር
እየበረታና እየጨመረ ሄዷል። 16 በማናቸ

ውም ነገር ልተማመንባችሁ የምችል
መሆኔ ደስታ ይሰጠኛል።

## ምዕራፍ 8

1 ወንድሞች ሆይ፥ እግዚአብሔር በመቄ
ዶንያ ላሉ አብያተ ክርስቲያን ስለሰጣቸው
ጸጋ ልንገራችሁ።
2 የደረሰባቸው መከራና ፈተና ብዙ ሆኖ
ሳለ ጥርሳቸውን ነክሰው ስላሳለፉት ዛሬ
በጣም ደስተኞች ናቸው። ምንም እንኳ
ድሆች ቢሆኑም የሰጡት ስጦታ ልግስና
የተሞላበት ነበር። 3 በአቅማቸው መጠን
ብቻ ሳይሆን መስጠት ከሚችሉት በላይ
ሰጥተዋል። ከአቅማቸው በላይ መስጠታቸ
ውም ማንም ሰው ገፋፍቶአቸው ሳይሆን፥
በገዛ ራሳቸው ፈቃድ ተነሣሥተው ያደረ
ጉት ለመሆኑ እኔ ምስክር ነኝ። 4 በኢየሩሳ
ሌም ለሚገኙት ክርስቲያኖችም በሚደረ
ገው የእርዳታ አስተዋጽኦ ለመሳተፍ ብዙ
ጊዜ ይለምኑን ነበር። 5 ያደረጉት ሁሉ አስ
ቀድመን ካሰብነውና ከጠበቅነው በላይ ሆኖ
አግኝተነዋል። በመጀመሪያ ራሳቸውን
ለጌታ ሰጡ፤ ቀጥሎም እንደ እግዚአብሔር
ፈቃድ ታዛዦች ለመሆን ራሳቸውን ለእኛ
አስገዙ። 6 ስለዚህ ይህንን ሥራ የጀመረው
ቲቶ፥ ወደ እናንተ መጥቶ በርኅራኄና በፍ
ቅር ተነሣሥታችሁ የምታደርጉትን ይህን
እርዳታ በማስተባበር ከፍጻሜ እንድታደር
ሱት እንዲረዳችሁ ለምነነዋል። 7 እናንተ
በሁሉ ነገር የተሟላችሁ ናችሁ። በእምነ
ትም ሆነ በሰባኪዎቻችሁ ብስለት፥ በእውቀ
ትም በኩል፥ ሰዎችን ለመርዳት ባላችሁ
ትጋት፥ እኛንም በመውደድ የሚስተካከላ
ችሁ ባለመኖሩ፥ በዚህ በሚደረገው እርዳታ
በኩል ደግሞ ከሌሎቹ ግንባር ቀደም እንድ
ትሆኑ አደራ እንላችኋለን። 8 በበኩሌ ይህን
አድርጉ ብዬ ትእዛዝ ለመስጠት ሳይሆን፥
ሌሎች አብያተ ክርስቲያን እርዳታ ለማድ
ረግ ካላቸው ጉጉት አንጻር የእናንተ ፍቅር
ምን ያህል እውነተኛ መሆኑን ለማረጋገጥ
ነው።
9 የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስን ፍቅርና
ልግስና በሚገባ ታውቁታላችሁ። እርሱ ሀብ
ታም ሆኖ ሳለ፥ እናንተን ለማበልጸግ ሲል
ድሀ ሆነ። ድሀ የሆነውም በእርሱ ድህነት
እናንተ ሀብታሞች እንድትሆኑ ነው።
10 ስለዚህ ጉዳይ የምሰጣችሁ ምክር እን
ደሚከተለው ነው። የእርዳታ እጃችሁን
መዘርጋት ብቻ ሳይሆን፥ የእርዳታው ሥራ
እንዲጀመር ባለፈው ዓመት አሳቡን ያቀረባ
ችሁት እናንተው ናችሁ። 11 ስለዚህ የጀመ
ራችሁትን በጎ ሥራ ከፍጻሜ ከማድረስ ወደ
ኋላ አትበሉ። ያላችሁን ነገር ለመስጠት
አስቀድሞ እንዳሰባችሁት ሁሉ አሁንም
ጉዳዩን ከፍጻሜ ለማድረስ አታመንቱ።
12 ለመስጠት ፈቃደኝነት ካላችሁ፥ እግዚአ
ብሔር ከእናንተ የሚፈልገው ያላችሁን
እንጂ የሌላችሁን እንድትሰጡ አይደለም።
13 ይህንን ስል ራሳችሁን ጎድታችሁ
ሌሎችን ከችግር አውጧቸው ማለቴ ሳይ
ሆን፥ እርስ በርሳችሁ እኩል ተሳሰቡ ለማ
ለት ነው። 14 በአሁኑ ጊዜ እናንተ ባላችሁ
ገንዘብ በችግራቸው ልትደርሱላቸው ይገ
ባል። እነርሱም በተራቸው ባላቸው ገንዘብ
እናንተን የሚረዱበት ጊዜ ይኖራል። አንዱ
የሌላውን ውለታ የሚመልሰው በዚህ ዓይ
ነት መንገድ በመተሳሰብ ነው። 15 ስለዚህ
በቅዱሳት መጻሕፍት፥ «ከመጠን በላይ የሰ
በሰበ አልተረፈውም፤ ጥቂት ያለውም አልቸ
ገረውም» ተብሎ ተጽፏል።
16 እኔ ለእናንተ የማስበውን ያህል
ቲቶም ለእናንተ እንዲያስብ ያደረገው አም
ላክ የተመሰገነ ይሁን። 17 ቲቶ በራሱ
ፈቃድ ተነሣሥቶ ሊያያችሁ እጅግ አድርጎ
ናፍቋችሁ ስለነበር፥ ወደ እናንተ እንዲሄድ
አሳብ ባቀረብኩለት ጊዜ ደስታውን አልቻለ
ውም። 18 በአብያተ ክርስቲያን ሁሉ ወንጌ
ልን በማስተማር በጣም የታወቀውንና የተ
መሰገነውን ወንድም ከቲቶ ጋር ስንልክላ
ችሁ ደስ እያለን ነው። 19 ይህ ወንድም፥
በኢየሩሳሌም ለሚገኙት ክርስቲያኖች የተ
ዋጣውን የእርዳታ ገንዘብ ለማድረስ፥ ከእኛ
ጋር ወደ ኢየሩሳሌም እንዲሄድም ጭምር
ተመርጦአል። እንደዚህ ያለው አድራጎት
እርስ በእርስ ለመረዳዳት ፈቃደኞች መሆና
ችንን ያሳያል፤ የጌታንም ስም እንዲከበር
ያደርገዋል። 20 ለኢየሩሳሌም ክርስቲያኖች
ልናደርስ በተሰበሰበው ገንዘብ ምክንያት
ማንም ከመሬት ተነሥቶ ያልሆነ ስም እንዳ
ይሰጠን እንጠነቀቃለን። 21 በጌታ ፊት ብቻ
ሳይሆን በሰዎችም ፊት ትክክለኛ የሆነውን
ነገር ማድረጉ ተገቢ መሆኑን እናምናለንና።
22 በተጨማሪም፥ ብዙ ጊዜ ተፈትኖ ሰዎ
ችን ለመርዳት በጎ ፈቃድ ያለው መሆኑ
የተመሰከረለትን ሌላውን ወንድማችንን፥ ከእ
ነርሱ ጋር ልከነዋል።
23 ቲቶ ማን እንደሆነ ለሚጠይቃችሁ
ሁሉ፥ እናንተን ለመርዳት አብሮኝ የሚደ
ክም የሥራ ባልደረባዬ መሆኑን ግለጡለት።
አብረውት የሚመጡት ወንድሞችም

ቢሆኑ፣በአብያተ ክርስቲያን ተወክለው የተ
ላኩና ለክርስቶስ ክብር የቆሙ ናቸው።
24 ስለዚህ በእናንተ የምንመካባችሁና
የምንታመንባችሁ የቱን ያህል እውነት
መሆኑ በአብያተ ክርስቲያን እንዲታወቅ፣
ለእነዚህ ወንድሞች ፍቅራችሁን ግለጡላ
ቸው።

## ምዕራፍ 9

1 ለክርስቲያን ወንድሞቻችን እርዳታ
መላክ ተገቢ ስለመሆኑ እዚህ ላይ ማንሣቱ
አስፈላጊ መስሎ አይታየኝም። 2 ምክንያ
ቱም የእርዳታ እጃችሁን ለመዘርጋት ፈቃደ
ኞች እንደሆናችሁ አውቃለሁ። «በአካይያ
የሚኖሩት ክርስቲያኖች ከአምና ጀምሮ የእ
ርዳታ መዋጮ ለማድረግ ተዘጋጅተዋል»
ብዬ ስለ እናንተ በመቄዶንያ ለሚገኙት
ክርስቲያኖች አፌን ሞልቼ ነግሬአቸው
ነበር። እነርሱም እናንተን በማየት ይህንኑ
የመሰለ እርዳታ ለማድረግ በመሽቀዳደም
ላይ ይገኛሉ። 3 አሁን እነዚህን ወንድሞች
ወደ እናንተ የላክሁአቸው እናንተን እያመ
ሰገንኩ የተናገርኩት ሁሉ፣እንዲያው ወሬ
ብቻ ሆኖ እንዳይቀር በማለት ነው። ስለ
እናንተ የነገርናቸው ሁሉ እውነት ሆኖ እን
ዲገኝ፣እርዳታው በአስቸኳይ ይጠናቀቅ።
4 ምናልባት የመቄዶንያ ሰዎች ከእኔ ጋር
ወደ እናንተ መጥተው የእርዳታውን ገንዘብ
ሳታዘጋጁ ቢያገኙዋችሁ፣ለእናንተም ለእ
ኔም ሐፍረት ነውና አደራ አስቡበት።
5 እነዚህን ወንድሞች ቀደም አድርጌ
ወደ እናንተ መላኬም፣ቃል የገባችሁትን
የገንዘብ መዋጮ አጠናቀው እንዲጠብቁኝ
በማለት ነው። ገንዘቡም ተዘጋጅቶ መጠበቁ
ራሱ አስተዋፅኦውን ያደረጋችሁት ሌላ ሰው
ገፋፍቶአችሁ ሳይሆን፣ራሳችሁ በገዛ ፈቃዳ
ችሁ ተነሣሥታችሁ ያደረጋችሁት መሆኑን
ያረጋግጣል። 6 «በጥቂት የሚዘራ በጥቂቱ
ይሰበስባል። አብዝቶ የዘራም አብዝቶ ይሰበ
ስባል» የተባለውን አስታውሱ። 7 እያንዳንዱ
ሰው ለመስጠት የሚፈልገውን ራሱ ወስኖ
ይስጥ እንጂ «እከሌ ይኸን ያህል ያውጣ፤
እከሌ ይኸን ያህል ይስጥ» በማለት ማንንም
አታስገድዱ። ሰጭውም፣ «ለምን ይህን
ያህል አወጣሁ?» ብሎ በመጸጸት አይስጥ።
እግዚአብሔር ደስ ብሎት የሚሰጠውን
ሰው ይወዳልና። 8 ወደውና አስበው ለሰጡ
ትም እግዚአብሔር በረከቱን አትረፍርፎ
ይሰጣቸዋል። የሚሰጣቸውም የሚያስፈልጋ
ቸውን ብቻ ሳይሆን፣ለሌሎች የሚቸሩት
ንም እንዲተርፋቸው አድርጎ ነው።
9 «ጻድቅ ሰው እጁ የቻለውን ያህል ለድ
ሆች ይቸራል። ይህም በጎ ሥራው ለዘላለም
አይዘነጋም» ተብሎ በቅዱሳት መጻሕፍት
የተጻፈው ቃል ይፈጸማል።
10 አራሽ ዘር ዘርቶ በገፍ አምርቶ እንዲ
መገብ የሚያደርግ አምላክ፣ለእናንተም የም
ትዘሩትን ዘር በማበርከት፣ለችግረኞችም እን
ድትተርፉ ያበቃችኋል።
11 ችሮታችሁ በእኛ አማካይነት የሚደር
ሳቸው ችግረኞች እግዚአብሔርን ያመሰግ
ኑት ዘንድ፣ምን ጊዜም እጃችሁ እርጥብ
እንዲሆን የሚያስፈልጋችሁን ሁሉ ይሰጣች
ኋል። 12 በዚህም የልግስና ተግባር በአንድ
ጊዜ ሁለት ነገሮችን ትፈጽማላችሁ። በአ
ንድ በኩል ችግረኞች ይረዱበታል። በሌላ
በኩል ደግሞ፣የእግዚአብሔር ስም በብዙ
መንገድ ይመሰገንበታል። 13 በተጨማሪም፣
እርዳታችሁ ለሚደርሳቸው ሰዎችም ሆነ
ለሌሎች፣ማንነታችሁን ታስመሰክራላችሁ።
በአንደበታችሁ ለምትመሰክሩት የክርስቶስ
ወንጌል ስትታዘዙ የሚያዩዋችሁ ሁሉ፣እም
ነታችሁ በተግባር ተፈትኖ የወጣለት ስለ
ሆነ እግዚአብሔርን ያመሰግኑታል።
14 ድንቅ የሆነው የእግዚአብሔር ጸጋ በእና
ንተ አድሮ በመገለጡም ጥልቅ በሆነ ተመ
ስጦ ይጸልዩላችኋል።
15 በቃላት ሊገለጥ ስለማይችለው ስለ
ታላቅ ስጦታው፣እግዚአብሔር የተመሰገነ
ይሁን።

## ምዕራፍ 10

1 «ይህ ጳውሎስ እኛ ዘንድ በሚመጣበት
ጊዜ ድምፁን ከፍ አድርጎ መናገር እንኳ
አይሆንለትም። ከዚህ በሚሄድበት ጊዜ ግን
የሚጽፍልን መልእክቶች በድፍረት የተ
ሞሉ ናቸው» ብለው ከእናንተ የሚገምቱኝ
ጥቂቶች ቢኖሩም እንኳ፣እኔ ጳውሎስ በክር
ስቶስ ገርነትና ትዕግሥት እለምናችኋለሁ።
2 ወደ እናንተ በምመጣበት ጊዜ ሳል
ወድ በግድ በሥልጣኔ እንድጫናችሁ እንዳ
ታደርጉኝ። በሥጋዊ አስተሳሰብ እንደምን
መራ አድርገው ለሚቆጥሩን ሰዎች ግን
ሥልጣኔን ማሳየት አያዳግተኝም። 3 በዓለም
ውስጥ እንደሌሎች ሰዎች የምንኖር ቢሆ
ንም፣የምንዋጋው ጦርነት መንፈሳዊ ነው።
4 በዚህ ጦርነት ውስጥ የምንጠቀምባቸው
መሣሪያዎች ሰው ሠራሽ አይደሉም። ነገር
ግን፣የጠላታችንን የዲያብሎስን ምሽግ ለመ
ደምሰስ የሚችሉ መለኮታዊ ኃይል ያላቸው

ናቸው። 5 በእነዚህም መሣሪያዎች፣በእግዚ
አብሔር እውቀት ላይ የሚሠነዘረውን ክርክ
ርና ከንቱ ትምክህት ፍርስርሱን በማው
ጣት ፣ ሰብአዊ አስተሳሰብ ሁሉ ለክርስቶስ
እንዲገዛ እናደርጋለን። 6 እናንተ ለክርስቶስ
ያላችሁን ታዛዥነት ካረጋገጥን በኋላ፣ለማይ
ታዘዙት ተገቢ ቅጣታቸውን እንዲቀበሉ
ለማድረግ ዝግጁዎች እንሆናለን።

7 ቁመናዬን አያችሁ እንጂ ፣ ማንነቴን
በሚገባ ያወቃችሁ አልመሰለኝም። የክርስ
ቶስ ኃይል ፣ የክርስቶስ ሥልጣን የተሰጠኝ
እኔ ነኝ ብሎ የሚያስብ ሰው ቢኖር፣እኔም
እንደርሱ የክርስቶስ ኃይልና ሥልጣን የተሰ
ጠኝ መሆኔን መገንዘብ ይኖርበታል።
8 ይህን በማለቴም በእናንተ ላይ ባለኝ ሥል
ጣን የተመካሁ መስሎ ይታያችሁ ይሆ
ናል። የሆነ ሆኖ ይህ ሥልጣን መንፈሳዊ
ሕይወታችሁን የሚገነባ እንጂ የሚንድና
የሚያፈርስ አይደለም። ስለዚህም አላፍርበ
ትም። 9 በእናንተ ዘንድ ሥልጣኔ እንዲረጋ
ገጥ የማደርገው በደብዳቤ በማስፈራራት
ብቻ እንዳይመስላችሁ።

10 «የሚጽፋቸው መልእክቶች ከባድና
አስጨናቂ መስለው ይታዩ እንጂ ሰውነቱ
ኮሳሳ ንግግሩ ተራ ፣ አይደለም?» የሚሉ
አሉ። 11 እንደዚህ የሚሉኝ ሰዎች ፣ ፊት
ለፊት በምንገናኝበት ጊዜ በእኔና በመልእክ
ቶቼ መካከል ምንም ልዩነት አለመኖሩን
ሊገነዘቡ ይችላሉ።

12 ራሳቸውን በራሳቸው ከሚክቡ ሰዎች
ጋር ራሴን የማወዳድር አይደለሁም። ይህ
ራስን በራስ ብቻ መዝኖና አወዳድሮ፣ «ያለ
እኔ ማን አለ?» ማለት ትልቅ ሞኝነት
ነው።

13 እኛ ግን ሥልጣን ሳይኖረን ሥልጣን
አለን ብለን አንመካም። የእኛ መመካት
ግን ዳር ድንበር ስላለው ከዚያ አይወጣም።
ይህም እግዚአብሔር በሰጠን የአገልግሎት
በር ክልል የተወሰነ ነው። የአገልግሎት
ክልሉም እናንተን ያጠቃልላል። 14 የክርስ
ቶስን ወንጌል በመጀመሪያ የሰበክንላችሁ
እኛ ስለሆን፣ «የምንነግራችሁን ስሙ» ማለ
ታችንን ፣ እንደአምባ ገነንነት አድርጋችሁ
አትቁጠሩት። 15 እኛ ሌላው በደከመበት
የምንመካ አይደለንም። ይልቁንም እምነታ
ችሁ እንዲጠነክር የእኛም አገልግሎት
በዚሁ እግዚአብሔር በወሰነልን ክልል፣በእ
ናንተው መካከል እንዲስፋፋ ተስፋ እናደር
ጋለን።

16 ከዚያም፣በሌሎች የአገልግሎት ክልል
ድርሻ ውስጥ ሳንገባ፣በአካባቢያችሁ ባሉና
ከዚህ በፊት ወንጌል ባልተሰበከላቸው
ሌሎች ከተማዎች ቃሉን ለማስተማር እንች
ላለን። 17 ቅዱሳት መጻሕፍት ፣ «የሚመካ
በእግዚአብሔር ይመካ» ስለሚሉ ማንም
ሰው ይህን ሠራሁ ብሎ በራሱ መመካት
አይገባውም። 18 ቍምነገሩ ራስን በራስ
ማመስገኑ ሳይሆን በእግዚአብሔር ዘንድ
የተመሰገኑ ሆኖ መገኘት ነው።

## ምዕራፍ 11

1 አነጋገሬ የሞኝ አነጋገር ቢመስላች
ሁም በትዕግሥት ታዳምጡኛላችሁ የሚል
ተስፋ አለኝ። ደግሞም የልቤን ገልጬ እስ
ክናገር ድረስ ታገሱኝ። 2 እንዲት ንጽሕት
ድንግል ለአንድ ወንድ ብቻ እንደምት
ታጭ ፣ እኔም እንዲሁ እናንተን እንደ ንጽ
ሕት ድንግል ለክርስቶስ ለማቅረብ አጭቼአ
ችኋለሁ። ይህን ለማድረግ የቻልኩትም ስለ
እናንተ መንፈሳዊ ቅንዓት ስላደረብኝ ነው።
3 ነገር ግን፣እባብ ሔዋንን እንዳሳታት ሁሉ
እናንተንም ሰይጣን በተንኰሉ አጥምዶ እን
ዳያሳስታችሁና ፣ ለጌታ ያላችሁን መንፈሳዊ
ቅንዓት እንዳያስተዋችሁ እሠጋለሁ። 4 ምክ
ንያቱም አንድ ሰው መጥቶ እኛ የሰበክነ
ውን ሳይሆን ፣ ሌላ ኢየሱስ ቢሰብክላችሁ ፣
ወይም የተቀበላችሁትን መንፈስ ቅዱስ ሳይ
ሆን ‘ሌላ መንፈስ ወይም ሌላ የደኅንነት
መንገድ አለ’ ብሎ ቢሰብክላችሁ ያለ
ምንም ማመንታት በቀላሉ ትቀበላላችሁና።

5 ከእነዚህ ፣ ‘ታላላቅ ሐዋርያት’ ነን
ከሚሉት በምንም ዓይነት አላንስም። 6 ‘የን
ግግር ችሎታ የለውም’ ብባልም እንኳ፣የም
ናገረውን ነገር የማላውቅ አይደለሁም። ይህ
ንንም በብዙ ዓይነት መንገድ ግልጽ አድር
ገንላችኋል።

7 የጌታን የምሥራች ቃል ስሰብክላችሁ
አንዲት ሳንቲም እንኳ አላስከፈልኳችሁም።
ታዲያ እናንተ ከፍ እንድትሉ ስል ራሴን
ዝቅ ዝቅ ማድረጌ ኃጢአት ሆኖ ተገኘ?
8 እናንተን ያስተማርኩትና በነፃ ሳገለግላ
ችሁ የኖርኩት ሌሎች አብያተ ክርስቲያን
የሚልኩልኝን እርዳታ እየተቀበልኩ ነው።
እንደ እውነቱ ከሆነ እናንተን ለማገልገል
ስል ፣ ሌሎቹን ዘርፌአቸዋለሁ። 9 አብሬአ
ችሁ በኖርኩበትም ጊዜ ገንዘብ በጣም ሲያ
ስፈልገኝ ማንንም አላስቸገርኩም። ችግሬን
የተወጣሁት ከመቄዶንያ የመጡ ወንድሞች
ባመጡልኝ እርዳታ ነበር። ከዚህ በፊት

ሽክም አልሆንኩባችሁም፤ወደ ፊትም አል
ሆንባችሁም። 10 ይህን ስናገር ፣ የክርስቶስ
እውነት በእኔ ውስጥ ስላለ፣ትምክህቴን በአ
ካይያ ውስጥ ከሚኖሩት ማንም ሊገታው
አይችልም። 11 ታዲያ እንዲህ ማለቴ ስለማ
ልወዳችሁ ነውን? አይደለም። እንደምወዳ
ችሁ እግዚአብሔር ያውቃል። 12 አሁንም
ሆነ ወደፊት ይህን የማደርገው ፣ ‘እኛም
እንደ እነጳውሎስ የእግዚአብሔርን ሥራ
እንሠራለን’ እያሉ የሚመጻደቁትን ‘ሐዋር
ያት ነን’ ባዮች አፋቸውን ለማስያዝ ነው።
13 እነዚህ ሰዎች ‘የክርስቶስ ሐዋርያት
ነን’ በማለት አስመስለው ይቅረቡ እንጂ
እውነተኞች ሐዋርያት አይደሉም።
14 በዚህ ደግሞ መደነቅ አያስፈልግም።
ምክንያቱም ሰይጣን ራሱ ለማታለል የብር
ሃን መልአክን መስሎ ይገለጥ የለ? 15 ስለ
ዚህ የሰይጣንም አገልጋዮች የብርሃን አገል
ጋዮችን ተመስለው ቢያታልሉ ምን ያስደን
ቃል? በመጨረሻ ግን ላደረጉት ለያንዳንዱ
ክፉ ሥራቸው ተገቢ ቅጣት ይቀበላሉ።
16 ማንም እንደ ሞኝ አድርጎ እንዳይቆጥ
ረኝ እንደገና ላሳስባችሁ እወዳለሁ። «ሞኝ
ነህ» የምትሉኝ ከሆነ እኔም እንደ ሌሎቹ
በጥቂቱ እንድመካ እንደሞኝ ተቀበሉኝ።
17 በእንዲህ ዓይነቱ በራስ መተማመን ላይ
በተመሠረተ ትምክህት የምናገረው ጌታ
እንደሚፈልገው ሳይሆን ፣ እንደሞኝ ሆኜ
ነው። 18 እነዚያ ፣ ‘ያለ እኛ ማን ሐዋርያ
አለ!’ ብለው እንደሚመኩ እኔም ልመካ
ብዬ ነው። 19 እኛ አስተዋዮች ነን ትላላ
ችሁ። ግን አንድ አላዋቂ ተንሥቶ፤ 20 ባሪ
ያው ቢያደርጋችሁ፣አብሉኝ አጠጡኝ ቢላ
ችሁ፣በዚያም በዚህ ብሎ ያላችሁን ቢወስ
ድባችሁ፣ትከሻውን ቢያሳብጥባችሁ፣ደረቱን
ቢነፋባችሁ፣ ወይም በጥፊ ጆሮ ግንዳችሁን
ቢያጮለው በትዕግሥት ትቀበላላችሁ።
21 እኛ የክርስቶስ ሐዋርያት ግን፣በእናንተ
ላይ እንዲህ ለማድረግ አንጀታችን አይጨክ
ንም። ይህንን መናገር ቢያሳፍረኝም እንኳ
እውነቱን ልደብቀው አልፈልግም። እነዚያ
የሚመኩበት ነገር ቢኖር ፣ አሁንም እንደ
ሞኝ ቁጠሩኝና፣እኔም ልመካ እችላለሁ።
ከማንም አላንስም።
22 ከሚመኩበት አንዱ ‘ዕብራውያን ነን’
ማለታቸው ነው። ታዲያስ? እኔስ ዕብራዊ
አይደለሁም? የተመረጠው የእግዚአብሔር
ወገን ‘እሥራኤላውያን ነን’ ብለው ይመ
ካሉ። እኔም እኮ እሥራኤላዊ ነኝ። ‘የአብ
ርሃም ዘር ነን’ ይላሉ። እኔም የአብርሃም
ዘር ነኝ።
23 የክርስቶስ አገልጋዮች ናቸውን?
እንደ እብድ አትቁጠሩኝና ከእነርሱ የበለጠ
ክርስቶስን እንዳገለገልኩ ስንቱን ተናግሬ
እዘልቀዋለሁ። በበኩሌ ከማንም የበለጠ ደክ
ሜአለሁ። ክርስቶስን በማገልገሌ ምክንያት
ብዙ ጊዜ ታሥሬአለሁ፤ብዙ ጊዜ ተገርፌአ
ለሁ ፤ ብዙ ጊዜም ለሞት አደጋ ተጋልጫ
ለሁ። 24 አይሁድ አምስት ጊዜ ይዘው ፣
ሰላሣ ዘጠኝ ጅራፍ ገርፈውኛል። 25 ሦስት
ጊዜ በሽመል ተደብድቤአለሁ። አንዴ በድ
ንጋይ ተወግሬአለሁ። ሦስት ጊዜ የምጓዝ
በት መርከቤ ተሰብሮብኛል። አንድ ጊዜማ
በጥልቅ ባሕር ውኃ ላይ ውዬ አድሬአለሁ።
26 ብዙ ጊዜ የወንጌልን ቃል ለመስበክ
ስጓዝ ልዩ ልዩ ችግር አጋጥሞኛል። የወንዝ
ሙላት አደጋ ደርሶብኛል። ወንበዴዎች
አደጋ ጥለውብኛል። ከአይሁዳውያንና ከአ
ሕዛብም አደጋ ደርሶብኛል። በየከተማዎች፣
በየበረሃው እንዲሁም በባሕር ስጓዝ አደጋ
ደርሶብኛል። ክርስቲያኖች ሳይሆኑ ‘ክርስቲ
ያኖች ነን’ ከሚሉ አስመሳዮች ችግር ደርሶ
ብኛል። 27 በሥራ ብዛት ደክሜአለሁ። ብዙ
ጊዜም እንቅልፍ አጥቻለሁ። ተርቤያለሁ፣
ተጠምቻለሁ፤መጠለያና ልብስ አጥቼ ተቸ
ግሬያለሁ።
28 ሌላም ያልዘረዘርኩት ብዙ ብዙ
ችግር ገጥሞኛል። ይሁን እንጂ ይህ ሁሉ
መከራና ችግር ቢደርስብኝም ፣ ከሁሉም
በላይ አስብ እጨነቅ የነበረው ስለ አብያተ
ክርስቲያን ደኅንነት ነበር። 29 ከደከመው
ጋር ፣ የድካሙ ተካፋይ ሆኛለሁ። አንድ
ሰው በመንፈሳዊ ሕይወቱ ሲሰናከል ስለ
እርሱ በኀዘን ተቆራምጃለሁ ፣ በቅንዓትም
ተቃጥያለሁ።
30 ትምክህት አስፈላጊ ቢሆን እንኳ፣እኔ
የምመካው ምን ያህል ደካማ መሆኔን በሚ
ያመለክቱት ነገሮች ነው። 31 ለዘላለም የተ
መሰገነው የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ
አባት እግዚአብሔር እውነት እንደምናገር
ምስክሬ ነው። 32 ደማስቆ በነበርኩበት ጊዜ
ንጉሡ አርስጦስዮስ አስተዳዳሪ አድርጎ የሾ
መው ሰው፣ሊያስይዘኝ ፈልጐ በከተማይቱ
በሮች ላይ ወታደሮች አቁሞ ያስጠብቅ
ነበር። 33 ነገር ግን ክርስቲያኖች በቅርጫት
ውስጥ አድርገውኝ ቅርጫቱን በገመድ
ካሠሩ በኋላ፣በግንቡ ቀዳዳ አሾልከው ወደ
መሬት አወረዱኝ። እኔም በዚህ ዓይነት ከከ
ተማይቱ ወጥቼ ከአገር አስተዳዳሪው እጅ
ለማምለጥ በቃሁ።

## ምዕራፍ 12

1 መመካት ጥቅም ባይኖረውም፥ መመ
ካት ካስፈለገ ከጌታ ስለተቀበልኋቸው ራእ
ይና መገለጥ ልንገራችሁ።
2-3 ከአሥራ አራት ዓመት በፊት እስከ
ሦስተኛው ሰማይ ድረስ ተነጠቅሁ። ‘ይህ
የሆነው በመንፈስ ነው? ወይስ በአካለ
ሥጋ?’ ብላችሁ አትጠይቁኝ። ምክንያቱም
እኔ መነጠቄን እንጂ በመንፈስ ይሁን በአ
ካል አላውቅም። ይህን የሚያውቅ እግዚአ
ብሔር ብቻ ነው። የሆነ ሆኖ በገነት ነበ
ርኩ። 4 ከዚያም የሰው አንደበት ሊገልጠው
የማይችለውን እፁብ ድንቅ ነገር ሰማሁ።
ሆኖም የሰማሁትን ይኸ ነው ብዬ እንድና
ገር አልተፈቀደልኝም። 5 ስለዚህ መመካት
ካስፈለገ በዚህ ሁሉ ልመካበት እችላለሁ።
ነገር ግን እኔ የምመካው ደካማ ሆኜ ሳለ፥
እግዚአብሔር እኔን ደካማውን ሰው ለክብሩ
መገልገያ መሣሪያ አድርጎ ስለተጠቀመብኝ
ብቻ ነው። 6 የምናገረው እውነት በመሆኑ
ብመካም፥እንደ ሞኝ ልቆጠር አይገባኝም።
ነገር ግን ማንም ሰው ስለ እኔ ከሚያየውና
ከአንደበቴ ከሚሰማው በላይ ከፍ አድርጎ
እንዲመለከተኝ ስለማልፈልግ አልመካም።
7 እነዚህን ከፍተኛ መንፈሳዊ ምሥጢ
ራት ከማየቴ የተነሣ በትዕቢት እንዳልወ
ጠር ሥጋዬን እንደ እሾህ የሚወጋ ሥቃይ
ተሰጠኝ። ይህም የሰይጣን መልእክተኛ
ሆኖ ሥጋዬን እየወጋ በማሠቃየት በትዕቢት
እንዳልወጠር ያደርገኛል። 8 ሦስት ጊዜ
ጌታን፥ «እባክህን እንደ እሾህ እየወጋ የሚ
ያሠቃየኝን ይህን ሥቃይ አስወግድልኝ»
ብዬም ለመንኩት። 9 እርሱ ግን፥ «የሚያስ
ፈልግህ ነገር ቢኖር ጸጋዬ ብቻ ነው። አንተ
በምትደክምበትም ጊዜ የእኔ ኃይል በበለጠ
በውስጥህ ይገለጣል» ሲል መለሰልኝ። ስለ
ዚህ የክርስቶስ ኃይል በእኔ አድሮ እንዲ
ሠራ ደስ እያለኝ በድካሜ እመካለሁ።
10 ለክርስቶስ ክብር እስከሆነ ድረስ እንደ
እሾህ በሚወጋኝ ሥቃይ እደሰታለሁ። ስድ
ቡንም ችግሩንም፥ ስደቱንና መከራውንም
ስለ ክርስቶስ እችለዋለሁ። ምክንያቱም በድ
ካሜ ከእርሱ ብርታትን አገኛለሁና።
11 ይህ ትምክህት እንኳ የሚገባ ስላል
ሆነ እንደሞኝ ያስቆጥረኛል። ታዲያ እኮ
ይህን ሁሉ እንድናገር ያደረጋችሁኝ እናን
ተው ናችሁ። እንዲህ ያለውን ነገር ስለ እኔ
መጻፍና መመስከር የሚገባችሁ እናንተ
እንጂ እኔ አልነበርኩም። የእኔ ማንነት
ይህን ያህል ያልታወቀ ቢሆንም፥ ‘ታላላቅ
ሐዋርያት’ ከሚባሉት በምንም አላንስም።
12 እናንተን ለማስተማር ከእግዚአብሔር
የተላክሁ እውነተኛ ሐዋርያ መሆኔን በመካ
ከላችሁ በነበርኩበት ጊዜ በትዕግሥት የፈጸ
ምኳቸው ሥራዎች ያስረዳሉ። እነዚህም
ሥራዎች ፤ ምልክቶች፥ ተአምራትና ድንቅ
ድንቅ ነገሮች ናቸው። 13 ሸክም እንዳልሆን
ባችሁ በማለት «ቀለብ ስፈሩልኝ ማረፊያ
አዘጋጁልኝ» ብዬ ካለማስቸገሬ በስተቀር፥
ለመሆኑ ለሌሎቹ አብያተ ክርስቲያን አድ
ርጌ ለእናንተ ሳላደርግ የቀረሁት ምን ነገር
አለ? ይህም እንደ ጥፋት ሆኖ ከተቆጠረ
ብኝ ይቅርታ አድርጉልኝ።
14 ለሦስተኛ ጊዜ ወደ እናንተ ለመም
ጣት ተዘጋጅቻለሁ። ገንዘብ እንድትሰጡኝ
ስለማላስቸግራችሁ በምንም አልከብድባች
ሁም። ምክንያቱም የምፈልገው፥እናንተን
እንጂ ገንዘባችሁን አይደለም። እናንተ
ልጆቼ ናችሁ። ወላጆች ለልጆቻቸው ገን
ዘብ ያከማቻሉ እንጂ፥ልጆች ለወላጆቻቸው
አያከማቹላቸውም። 15 ስለ እናንተ፥እንኳን
ገንዘቤን ሕይወቴን ጭምር አሳልፌ ብሰጥ
ቅር አይለኝም። ታዲያ እኔ የማፈቅራችሁ
ይህን ያህል ሲሆን የእናንተ ፍቅር ለምን
ቀዘቀዘብኝ?
16 «አዎን፥እርግጥ ነው፥እርሱን በመቀ
በል በማስተናገድና በመሸኘት ብዙ ወጭ
አላደረግንም። በዚያም በዚህ ብሎ ግን ሳያ
ምታታን አልቀረም» የሚሉኝ ከመካከላ
ችሁ አይታጡ ይሆናል።
17 ማለቱንስ በሉ። ግን ከላክኋቸው
ሰዎች፥ በአንዱ አማካይነት እንኳ ዘረፍኳ
ችሁ? 18 ቲቶን ከአንድ ክርስቲያን ወንድም
ጋር ወደ እናንተ ልኬው ነበር ፤ ታዲያ
ቲቶስ ዘረፋችሁ? እኔና እርሱስ በአንድ
ዓላማ አላገለገልናችሁም? በአንድ መንፈ
ስና አካሄድስ አብረናችሁ አልቆየንምን?
19 ወዳጆቼ ሆይ፥ምናልባት እስከ አሁን
ድረስ ራሴን ለመከላከል የምናገር ይመስላ
ችሁ ይሆናል። አይደለም። የክርስቶስ አገል
ጋይ እንደ መሆኔ መጠን፥በእግዚአብሔር
ፊት ይህንን የምነግራችሁ መንፈሳዊ ሕይወ
ታችሁ እንዲዳብር በማለት ነው። 20 በምመ
ጣበት ጊዜ እንዳሰብኩት ሳይሆን ተለውጣ
ችሁ እንዳላገኛችሁ እሠጋለሁ። እናንተም
እኔን ከጠበቃችሁኝ የተለየሁ ሆኜ ታገኙኝ
ይሆናል። ምናልባትም ክርክር፥ ቅናት፥
ቁጣ፥ራስ ወዳድነት፥ስድብ፥ሐሜት ትዕቢ
ትና ብጥብጥ በመካከላችሁ ይኖር ይሆን?

በማለት እፈራለሁ። 21 ወደ እናንተ ተመ
ልሼ ስመጣ አምላኬ ምናልባት በእናንተ
ፊት ያዋርደኝ ይሆን? ብዬም እፈራለሁ።
ከእናንተ ብዙዎቹ ከዚህ በፊት ስላደረጉት
ርኩሰት፣ ዝሙትና መዳራት ተጸጽተው
ንስሐ ሳይገቡ አገኛቸው ይሆናል። ፍርሃ
ቴም ሥጋቴም በኃጢአታቸው ተጸጽተው
ንስሐ ሳይገቡ እንደዚሁ ያገኘኋቸው እንደ
ሆን ነው። ነገሩ እንደዚህ ከሆነ መቼም
ከባድ ኀዘን ላይ መውደቄ የማይቀር ነው።

## ምዕራፍ 13

1 ወደ እናንተ የምመጣው ለሦስተኛ
ጊዜ መሆኑ ነው። በቅዱሳት መጻሕፍት፣
«ማናቸውም ነገር በሁለት ወይም በሦስት
ምስክሮች ቃል ይጸናል» ተብሎ ተጽፏል።
2 ሁለተኛ ወደ እናንተ መጥቼ በነበረበት
ጊዜ ማስጠንቀቂያ ሰጥቻችሁ ነበር። ከዚህ
ሆኜ በድጋሚ የማስጠነቅቃችሁ፣ አሁን
ስመጣ ከዚህ በፊት ኃጢአት ለሠሩትም
ሆነ ለሌሎች የማልራራላቸው መሆኑን እን
ድታውቁት ነው።

3 ክርስቶስ በእኔ አድሮ እንደሚናገር በቂ
ማስረጃ እንደምትሹ አውቃለሁ። እናንተ
ራሳችሁ ክርስቶስ በእናንተ መካከል በድ
ካም ሳይሆን በኃይል እንደሚሠራ አይታች
ኋል። 4 እርሱ በለበሰው ሥጋ ምክንያት
በድካም በመስቀል ተሰቅሎ ቢሞትም፣
አሁን በእግዚአብሔር ኃይል በሕይወት
ይኖራል። እኛም እንደዚሁ በሥጋ ደካሞች
ብንሆንም፣ በእግዚአብሔር ኃይል ከእርሱ
ጋር ሕያው ሆነን እየኖርን እናንተን እናገለ
ግላለን።

5 እስቲ በክርስትና እምነት ውስጥ
መሆን አለመሆናችሁን ለማወቅ ራሳችሁን
መርምሩ። በሕይወታችሁ ደክማችሁ ካል
ሆነ በቀር፣ ኢየሱስ ክርስቶስ ያለማቋረጥ በእ
ናንተ አድሮ የሚኖርና የሚሠራ መሆኑ
አይሰማችሁምን? «ክርስቲያኖች ነን» የም
ትሉትስ በእርግጥ ናችሁ? 6 እኔ ግን ፈተና
ውን አልፌ የጌታ ወገን መሆኔ መረጋገጡን
ታውቃላችሁ ብዬ እገምታለሁ።

7 እኛ ያስተማርናችሁ ‘እውነት ነው
አይደለም’፣ ለማለት ሳይሆን፣ መልካም ማድ
ረግ እንድትችሉ ስለምንፈልግ ክፉ ነገር
ከማድረግ እግዚአብሔር እንዲጠብቃችሁ
እንጸልይላችኋለን። እኛ ብንናቅ ግድ የለ
ንም። እናንተ ግን ክፉ ከማድረግ ይልቅ
መልካም እንድታደርጉ እንፈልጋለን።
8 እኛ ስለ እውነት እንሠራለን እንጂ የእው
ነት ተቃዋሚዎች አይደለንም። 9 እናንተ
ብርቱዎችና ጠንካሮች ከሆናችሁ እኛ ደካ
ሞችና የተናቅን ብንሆንም ግድ የለንም።
ምኞታችንና ጸሎታችንም ሁሉ በክርስትና
እምነታችሁ እንድትጠነክሩ ነው።

10 ገና በሩቅ ሆኜ ይህንን መልእክት የጻ
ፍኩላችሁ፣ በምመጣበት ጊዜ ሥልጣኔን
በጭካኔ ማሳየት ስለማልፈልግ፣ ማናቸውንም
ነገር ከአሁኑ አውቃችሁ እንድታስተካክሉ
ላሳስባችሁ በማለት ነው። ጌታ ሥልጣንን
የሰጠኝ በቅጣት እንድጐዳችሁ ሳይሆን፣
መንፈሳዊ ሕይወታችሁ የሚዳብርበትን
ነገር እንዳደርግ ነው።

11 ወንድሞቼ ሆይ፣ በተረፈ ደኅና ሁኑ።
በመንፈሳዊ ሕይወታችሁ በርቱ፣ ጠንክሩ።
የመከርኳችሁንም ሁሉ አትርሱ። እርስ በእ
ርሳችሁ ተስማምታችሁና ተግባብታችሁ
በሰላም ኑሩ። የፍቅርና የሰላም አምላክም
ከእናንተ ጋር ይሆናል።

12 እርስ በእርሳችሁም በተቀደሰ መሳ
ሳም ሰላም ተባባሉ። 13 በዚህ ያሉት ክርስ
ቲያኖች ሁሉ ሰላምታ ያቀርቡላችኋል።
14 የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ጸጋ፣ የእግዚ
አብሔር ፍቅር፣ የመንፈስ ቅዱስም አንድ
ነት ከሁላችሁ ጋር ይሁን።

የናንተው
ጳውሎስ